# መጽሐፈ ጤፉት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል
ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ በግሸን ደብረ ከርቤ
ቅድስት ማርያም መቀመጡንና ስለሌሎች ምንታውያን
ታሪኮች የሚናገር መጽሐፍ



ተርጓሚ

መሪጌታ የማነ ብርሃን አዱሴ


የመጀመሪያ ዕትም

የግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ደብር

ሰበካ ጉባኤ፡ መጋቢት ፲፱፻፺፮ ዓ/ም



©፲፱፻፺፮ የግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ደብር ሰበካ ጉባኤ



መጽሐፈ ጤፉት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል
ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ በግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም
መቀመጡንና ስለሌሎች ምንታውያን ታሪኮች የሚናገር
መጽሐፍ



መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

ይሕን መጽሐፍ መልሶ የማሳተምና የማከፋፈል እና
የማሰራጨት መብት የግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም
ደብር ሰበካ ጉባኤነው።


ተርጓሚ

መሪጌታ የማነ ብርሃን አዱሴ



ምስለ ፍቁር ወልዳ በግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ብቻ ከሚገኘው ከመጽሐፈ ጤፉት የተወሰደ የ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሥዕል



በግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም የምትገኘው የእመቤታችን ‹‹ወእንዘ ትፈትል ሥዕል›› ማለትም እመቤታችን የቤተ መቅደስ መጋረጃ የሚሆን ሐርና ወርቅ እያስማማች ስትፈትል መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንዳበሠራት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት
አዲስ አበባ



ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ
የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ
የቅዱስ ሲኖዶስ አባል



ሊቀ ሊቃውንት ተክለ ማርቆስ ብርሃኑ
የግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ደብር አስተዳዳሪ

## መጽሐፈ ጤፉት

**ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም መቀመጡንና ስለሌሎች ጥንታውያን ታሪኮች የሚናገር መጽሐፍ**

## መግቢያ

አባታችን አዳም ለአምላኩ ባለመታዘዝ የበለስ እንጨት ዛፍ ፍሬ በልቶ ከገነት ቢባረርም አምላካችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእንጨት በተሠራ መስቀል ላይ ተሰቅሎ አዳነን፡፡ ስለ መስቀል ታሪክ መናገር ማለት ስለ ሰው ልጅ የድኅነት ታሪክ መናገር ማለት ነው፡፡ መስቀሉ የመዳናችን ምልክት ነው፡፡ መስቀሉ የሕይወት ምልክት፣ የድል አድራጊነት ምልክት፣ የዕርቅና የሰላም፣ የተስፋና የልምላሜ፣ የመስዋዕትነትና የኃይል ምልክት ነው፡፡ መስቀሉ ከሁሉ በላይ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የዘለዓለማዊ ሕይወትና የእውነተኛ እምነት ምልክት ነው፡፡

መስቀሉ ዕርቅ የተፈጸመበት አደባባይ፣ አማናዊው የሐዲስ ኪዳን መስዋዕት የተሰዋበት መንበር፣ የሰላምና

የፍቅር ንጉሥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ንጉሥ ሆኖ የነገሠበት ዙፋን ነው፣ ከሰማይ የወረደ ሕብስት ለዓለም ሁሉ ለዘለዓለም የተሰጠበት ክቡር፣ ልዩ፣ ቅዱስ በሰው ደም ሳይሆን በተዋሕዶ በከበረ በመድኃኒታችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተቀደሰ ነው። በዚህ መጽሐፍ የምናገኘው ታሪክ ስለዚህ ክቡር መስቀል ክብርና ወደ ሀገራችን መጥቶ በግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ደብር በመቀመጥ ሀገራችንን የንዋየ ሐዲስ ማለትም የሐዲስ ኪዳን ቅዱስ ሀብት መገኛ ያደረጋትን የቅዱስ መስቀሉን ታሪክ ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ መስቀሉ በጻፈው ስብከት ‹‹መስቀሉ ለአይሁድ ፈተና ነው፣ ለአህዛብ ሞኝነት ነው ለእኛ ግን የድኅነታች ማስታወሻ ሰነድ ነው። ስለ መስቀሉ ስናስብ ስለ ክርስቶስ ሕማም እናስባለን፣ መስቀሉ የቤተ ክርስቲያን ድኅነት ነው፣ መስቀሉ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ ያወጣን ነው፣ መስቀሉ የዕርቅ ምልክት ነው፣ የኃጥአን የድኅነት ተስፋ ነው፣ እኛ የተቀበልነው የመጀመሪያ በረከት መገኛ ነው፣ በመስቀሉ ወደ እግዚአብሔር ቀረብን፣ መስቀሉ ከአጋንንት ኃይል ነፃ አወጣን፣ በመስቀሉ ጠብን አሳደድን፣ ጥላቻን



አስወገድን፣ በመስቀሉ ከሞትና ከጥፋት ዳንን ስለዚህ ዘላለማዊትን አገኘን ብልየትን አጠፋን። የመስቀሉ ኃይል እንደምን ይገርማል።›› ብሏል።

ጌታችን ካረገ በኋላ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የአበውን ተስፋና የነቢያትን ትንቢት ፍጻሜ፣ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመልንን የድኅነት ሥራ ያላመኑ አይሁድ በክህደታቸው መጽናት ብቻ ሳይሆን ክርስቲያኖችን ማሳደድን፣ በክርስቶስ ስም ማመንን፣ መመስከርንና ማስተማርን መቃወም አላቋረጡም።

እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ ያሉትን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተመሉ አገልጋዮችን በድንጋይ ወግረው ገድለዋል (የሐዋ 7፡ 59፣ 12:2)። ዋና ጥረታቸው የኦሪትን ሥርዓት ማጽናትና የሐዲስን ሥርዓት ማጥፋት ቢሆንም ክርስቲያን ሐዋርያት ግን በእጃቸው ብቻ ሳይሆን በልብሳቸውና በጥላቸው ድንቅ ተአምራት በማድረግ የክርስትናን ትምህርት ማስፋፋታቸውን አላቋረጡም። (14:8)

በሐዋርያት ዘመን ተአምራትን በማድረግ የክርስትናን እውነተኛ ትምህርትና የመድኀኒታችንን የጌትነት ክብር ከሚገልጹት ነገሮች አንዱ ጌታችን የተሰቀለበት መስቀል ነበር። በጌታችን ደም የተቀደሰው መስቀል ብዙ ተአምራትን ሲያደርግ ቅንዓት አላስቀምጣቸው ያለው አይሁድም "በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነው" (ዘዳ 21:22-23) የሚለውን በመጥቀስ የተሰቀለበትን እንጨት እንቅበረው በማለት በተንኮል መከሩ። መክረውም መስቀሉን ቀበሩት። በላዩም ላይ በአዋጅ የከተማ ቆሻሻ እንዲደፋበት አደረጉ።

ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ ‹‹የንጉሥ ቆስጠንጢኖስን የሕይወት ታሪክ›› በጻፈበት መጽሐፉ ላይ በኋላ ዘመን የተነሡ የሮም ነገሥታትም ሳይቀሩ በጌታ መቃብር ላይ የጣኦት ቤት መሥራታቸውን ጠቅሷል።

በመሠረቱ ክርስቲያኖች ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ በግሪክና በሮም ነገሥታት እንደወንጀለኛ ይታ ስለነበር፣ በነፃነት ማምለክ፣ ማስተማር፣ ትንሣኤውንም መመስከር የማይችሉ፣ በተገኙበት የሚገደሉ፣ በፈ ውሃና በሚንቀለቀል እሳት የሚቃጠሉ፣ ለሚያስፈሩ



ለተራቡ አራዊት የሚሰጡ ሕዝቦች ነበሩ። እነሱም ስለ ሃይማኖታቸውን ብዙ ሰማእትነትንና መከራ ይቀበሉ ስለነበርጌታችን የተሰቀለበትን መስቀል በክብር ጠብቀው ለማቆየት አልቻሉም። ይሁን እንጅ ስለ መስቀሉ መናገርና መመስከር አላቋረጡም፣ በመስቀል ላይ የተፈጸመውን ድኅነት፣ በቃል፣ በሕይወትና፣ በልዩ ልዩ ሥነ ጥበብ ሲገልጹም ኖረዋል።

ሐዋርያው በመስቀሉ የተገኘውን ድኅነት እና ሰላም ሲገልጽ "ከባላጋራን የተነሣ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዝ የተጻፈውን የእዳ ጽሕፈት ደመሰሰው።እርሱንም በመስቀል ቸንክሮ ከመንገድ አስወግዶታል" (ቆላ 2:14)፣ ዳግመኛም በመስቀሉ የተፈጸልንን ዕውነተኛ ድኅነትና ዘለዓለማዊ ሰላም ሲገልጽ "ሁሉንም በርሱ ይቅር ይለው ዘንድ በመስቀሉ ባፈሰሰው ደሙም በምድርና በሰማያት ላሉ ሰላምአደረገ" ቆላ1፡ 20 በማለት ከአምላካችን ጋር የነበረን መልካም ግንኙነት ወደ ቀድሞው ቦታው መመለሱን፣ አዳም ወደ ቀደመ ክብሩ መግባቱን ከመስቀሉ ጋር በማገናኘት ሲያስተምሩ ቆይተዋል። በተለይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አይሁድና አሕዛብ ስለመስቀሉ መስማትና

ማሰብን እንዳማይቀበሉት ሲገልጽ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው"። 1ኛቆሮ 1፡18 ብሏል።

ይህ የሚያሳየው ምንም እንኳ አይሁድ መስቀሉን ቢቀብሩትም፣ በላዩም ቆሻሻ ቢደፉበትም ሐዋርያት ስለ መስቀሉ ክብርና በመስቀሉ ስለተገኘው ድኅነት መመስከር፣ ማስተማር አለማቋረጣቸውን፣ የመስቀሉ ፍቅር ከውስጣቸው የማይወጣ፣ ከደማቸውና ከሥጋቸው የተዋሐደ፣ በቆዳቸው ላይ በማይፋቅ ቀለም የተቀረጸ መሆኑን ነው። አይሁድ በክፋታቸው አሕዛብ በሥጋዊ ኃይላቸው ሲመኩ ለክርስቲያኖች ግን ትምክህታቸው መስቀሉ ነበር።

‹‹ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት እኔም ለዓለም ከተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ›› ገላ 6፡14። እንዳለ።

በዚህ ሁኔታ መስቀሉ አይሁድ እንደቀበሩት አሕዛብ በላዩ ላይ የጣዖት ቤት እንዳነጹበት ክርስቲያኖች ግን ሳይረሱት ለሦስት መቶ ዓመታት ተቀብሮ ቆይቷል።



በኋላ ግን አሁንም የነፃነት ምልክትና መገኛ የሆነው ቅዱስ መስቀል ለክርስቲያኖች ዘመነ ሰቆቃ ፍጻሜም ምክንያትና ኃይል ሆነ።

ከሦስት መቶ ዓመት በኋላ ንጉሥቆስጠንጢኖስ በሮምና በግሪክ ነግሠው ዓለምን አስጨንቀው ፍትሕ አጥፍተው፣ክርስቲያኖችን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ታትረው ይሠሩ የነበሩ ዲዮቅልጥያኖስንና መክስምያኖስን ለመግጠም ተነሣ። በዚህ አስፈሪና እጅግ ከባድ በሆነ ጦርነት ውስጥ ደግሞ መጽናኛና ኃይል የሚሆን ሕልምን አየ፣ ሕልሙም የመስቀል ምክልት የያዘ መልአክ መስቀሉን ለንጉሡ እያሳየ‹‹በዚህ ምልክት ጠላቶችህን ድል ንሣ›› የሚል ነበር። ከዚህ ቀደም ንጉሡ ይህንን ምልክት አያውቀውምነበር። እሱ የሚያውቀው ከሱ በፊት የነበሩ የሮም ነገሥታት መስቀሉን ወንጀለኛ ይሰቅሉበት ስለነበር የሞት ምልክት መሆኑን ነው እንጅ ሞት ድል ተነሥቶበት የሕይወት ምልክት መሆኑን አያውቅም ነበር። እናቱ እሌኒ ስለ ክርስትና ትምህርት እያስተማረች ያሳደገችው ቢሆንም የክርስትናን ምሥጢር ተቀብሎ አልተጠመቀም ነበር፡ ፡ እግዚአብሔርም እርሱ የሚድንበትንና ሌሎቹንም

የሚያድንበትን ምልክት ሰጠው፡፡ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠኻቸው›› እንዳለ፡፡ በመቀጠልም ንጉሡ በተሰጠው ምልክት ጠላቶቹን ሁሉ ድል ነሣ፡፡

በ313 ዓ/ም በሚላን ሆኖ የነፃነት አዋጅ አወጀ፡፡ መስቀሉ የፍትሕ ምንጭ ሆነ፣ ከአሁን በኋላ ክርስቲያኖች እንዳይሰደዱ ሃይማኖታቸውንም በግልጽና በነፃነት እንዲያስተምሩ፣ በነፃነት እንዲያመልኩ አወጀ፡፡ ‹‹አብያተ ክርስቲያናት ታነፁ አብያተ ጣዖታት ተዘጉ፡፡›› ይህን ውለታ ለመክፈል ንግሥት እሌኒ ከቀድሞ ጀምሮ በነበራት ስእለት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ በጎለጎታ የተሠራን ቤተ ጣዖት አፈረሰች፣ ቤተ ክርስቲያንም አሠራች፣ በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያን ሊቃውንትን፣ ሊቀ ጳጳሱን መቃርዮስንና አረጋዊው ኪራኮስን በመጠየቅ መስቀሉን ከተቀበረበት አወጣች፡፡

እንደ ታሪኩ አቀራረብ ንግሥት እሌኒ መስከረም ፲፯ ቀን ቁፋሮውን ጀምራ መጋቢት ፲ ቀን፫፻፳፮ ዓ/ም መስቀሉን አወጣች፡፡በኋላም ለመስቀሉ መታሰቢያ ቤተክርስቲያን ተሠርቶ ቅዳሴ ቤቱ መስከረም ፲፯ ቀን ፫፻፴፮ ዓ/ም



ተከበረ፡፡ እነዚህ በዓላት በመላው ዓለም ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይከበራሉ፡፡ ንግሥት እሌኒም ቅዱስ መስቀሉን ሊቀ ጳጳሱ መቃርዮስ በኢየሩሳሌም ባሠራችው ቤተ መቅደስ እንዲያስቀመጥ አድርጋ ወደ ሀገረ መንግሥቷ ቆስጥንጥንያ ተመለሰች፡፡

ከዚያም መስቀሉ በኢየሩሳሌም ተቀመጠ፣ ብዙ ዓመታትንም ኖረ፣ በርካታ ክርስቲያኖች ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ወደ ኢየሩሳሌም ከሚሄዱባቸው ምክንያቶችም አንዱ መስቀሉን ለማክበር ነበር፡፡ እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ በሰላም ቆየ፡፡


በ614 ዓ/ም የፋርሱ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ወረረ፣ ብዙ ጥፋትም አደረሰ፣ መስቀሉንም ማርኮ ወደ ፋርስ ወሰደው፡፡ በ627 ዓ/ም ክርስቲያኑ የሮም ንጉሥ ሕርቃል በክርስቲያኖች ጥያቄ ፋርስን ወግቶ መስቀሉን ወደ ኢየሩሳሌም መለሰው፡፡ ቆይቶም ኢየሩሳሌም በዓረቦች እጅ ስትወድቅ ክርስቲያኖች መስቀሉን ደበቁት፡፡ ይሁን እንጅ መላው ኢየሩሳሌም፣ ፍልስጥኤም፣ ምሥራቃዊው ሮም፣ ሰሜን አፍሪቃ ሁሉ በዓረቦች ቁጥጥር ሥር ስለሆኑ መስቀሉን ደብቀው ማስቀመጥ አልቻሉምና

ወደ እስክንድርያ አመጡት። ከእስክንድርያም በዚህ መጽሐፍ እንደተጻፈው በእግዚአብሔር ፈቃድና በነገሥታቱ ጥሪት ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ መጣ።

## የጌታችንና የመድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መስቀል የተቀመጠባት የግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም

ግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በአምባሰል ወረዳ ከደሴ ከተማ 82 ኪ/ሜ ርቃ ከፍ ብሎ በሚታይ መስቀለኛ ተራራ ላይ ትገኛለች። በአቅራቢያዋም ከሚገኙ በርካታ ታሪካውያንና ጥንታውያን መካናት መካከልም ጥንታዊው የደብረ ሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ገዳም፣ የድጓ ምስክር የነበረው ደብረ እግዚአብሔር፣ የቅኔ ትምህርት ምንጭ የሆነው ዋድላ/ደላንታ፣የ19ኛው ክፍለ ዘመን የሃይማኖት ውሳኔ የተደረገበት የቦሩ ሜዳ ሥላሴ፣ የውጫሌ ውል የተፈረመበት የውጫሌ ከተማ፣ የመቅደላ አምባ፣ የበሽሎ ወንዝ ሸለቆና ሌሎችም ናቸው።





የግሸን ደብረ ከርቤ ተራራ ከላይ ወደታች ሲታይ

ግሸን ደብረ ከርቤ የሚለውን ስያሜ ከማግኘቷ በፊት በልዩ ልዩ ታሪካዊና ምሥጢራዊ ምክንያቶች ደብረ ነገሥት፣ ደብረ ነጐድጓድ፣ ደብረ እግዚአብሔር በሚባሉ ስሞች ትጠራ ነበር። ግሸን ደብረ ከርቤ መጀመሪያ የተመሠረተችው በዘመነ አክሱም በዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ነበር።

ዐፄ ካሌብ በየመን የነበሩ ክርስቲያኖች በአይሁድ መሪ ዱን አናሚስ እየደረሰባቸው ከነበረው መከራ ለመታደግ ወደ ናግራን ዘምተው ድል አድርገው መንግሥት

አጽንተው ሲመለሱ በዚያ ይኖሩ የነበሩ አባ ፈቃደ ክርስቶስ የሚባሉት መነኩስ አብረው ተመልሰዋል።

አባ ፈቃደ ክርስቶስም ከናግራን ሲመለሱ ሁለት ጽላቶችን ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት የበሽሎ ወንዝን ተሻግረው ወደ ግሸን ተራራ ጫፍ ለመውጣት የአምባውን ዙሪያ ሲመለከቱ በገደሉ ላይ ንብ ሰፎ ማሩ ሲንጠባጠብ አይተው የአምላክን ስጦታ ለማድነቅ በጥንታዉያን ግእዝና ዓረብኛ ቋንቋዎች ቦታውን "አምባ" "አሰል" (አምባሰል) ብለው ጠሩት። ትርጉሙም "የማር አምባ" ማለትነው። እስከ አሁንም አካባቢው አምባሰል እየተባለ ይጠራል።



በግሸን ደብረ ከርቤ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን




አባ ፈቃደ ክርስቶስም ይዘዋቸው የመጡትን ሁለት ጽላቶች ወደ አምባው በማስገባት ሁለት ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ደብሩን መሥርተዋል።

ይኽንኑ ታሪክ በመከተልም ይመስላል በጉዲት ጦርነት የስደት ዘመን የእክሱሙ ንጉሥ ድል ነዓድ በዘጠነኛው ክፍል ዘመን ከአምባሰል ባሻገር ከሐይቅ ባሕር አጠገብ ባለው ተራራ ላይ ደብረ እግዚአብሔርን መሥርቶ ኖሯል። ከዚህም በኋላ መንግሥት ከደብረ እግዚአብሔር በመራ ተክለሃይማኖት አማካኝነት ወደ ላስታ ሲሻገር የደብረ ከርቤ ክብር በላስታ ዘመንም አልተቋረጠም።

በቅዱስ ላሊበላ ዘመን እንደተፈለፈሉ የሚነገርላቸው ጅምር ዋሻዎች አሁንም በደብረ ከርቤ ግሸን ማርያም ይገኛሉ።

በዚህ ዘመን ደብረ ከርቤ የነገሥታት መናኸሪያ የሊቃውንት መገኛ የቤተ ክርስቲያን የሐዲስ ኪዳን ሥርዓት መፈጸሚያ ቅድስት ቦታ ነበረች።

በመጨረሻም በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መስቀል መቀመጫ ሆናለች።



በግሸን ደብረ ከርቤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ያረፈበት የእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን



## ስለ መጽሐፈ ጤፉት

መጽሐፈ ጤፉት ስመ መንግሥታቸው ቆስጠንጢኖስ ተብሎ በሚታወቁት በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ራሳቸው ከጻፏቸው፣ በዘመናቸው በነበሩ ካህናት ደብተራ ካጻፏቸውና ካስተረጐሟቸው የእምነት፣ የቀኖናና የታሪክ መጻሕፍት ለየት የሚያደርገው መጽሐፉ በዘመናቸው የተሠራውን ትልቅ የውጭ ግንኙነት ሥራ ዘግቦ መያዙ ነው። ጤፉት የተባለበትም ምክንያት ሥነ ጽሕፈቱእንደ ጤፍ ደቃቅ በመሆኑ ነው። መጽሐፉ ቀደም ሲል በሀገራችን ስለ መስቀሉ የሚታወቁ ዓለም አቀፍ ታሪኮችንና እና ሌሎች ቀኖናዊ መረጃዎችን የያዘ፣ በግሸን ደብረ ከርቤ ብቻ የሚገኝ፣ ለብዙ ዘመናት በዚያው ተጠብቆ የቆየ፣ ከ፭፻ ዓመታት በላይ በደብሩ ሊቃውንት እየተተረጎመ ለምእመናን ሲነገር የኖረ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፈ ጤፉት ዛሬ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያገኘውን የመስቀል ደመራ በዓል አከባበር ከመሠረቱ ጀምሮ የሚያዘክር፣ ከዚያም መስቀሉ በመካከለኛው ምሥራቅና በእስክንድርያ ከአንድ ሺህ ዓመታት በላይ የነበረውን

ቆይታ በኋላም በዐሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በዳግማዊ ዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ከእስክንድርያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበትን፣ በመጨረሻም በዳግማዊ ዐፄ ዳዊት ልጅ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት አባታቸው በክብር ካስቀመጡበት ከስናር የጦር ከተማ አንስተው ከአምባሰል ተራሮች ከፍ ብላ ወደምትገኘው ግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም አምጥተው ያስቀመጡበትን ታሪክ በቅደም ተከተል ይተርካል። በተጨማሪም በወቅቱ የነበሩትን የሊቃነ ጳጳሳቱን የአባ ገብርኤልንና የአባ ሚካኤልን፣ የኤጴስ ቆጶሱን የአባ



ዮሐንስን ቃለ ቡራኬ፣ ቃለ ምዕዳንና ሥርዓት፣ የደብሩን ቀደምት ሊቃውንት እና ሹማምንት ምስክርነት በሚገባ



ይተርካል። መጽሐፉ ልዩ የሚያደርገው በዘመኑ የነበሩትን ታላላቅ ነገሥታት የዐፄ አምደ ጽዮንን፣ የዳግማዊ ዐፄ ዳዊትን፣ እና የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት፣ የውጭ ግንኙነት፣ ሥርዓተ መንግሥት በዘመኑ ቋንቋና አደረጃጀት ሳይበረዝና ሳይከለስ በመዘገብ የታሪክ ምንጭ ነው።

በተጨማሪም መስቀሉ በደብረ ከርቤ ግሸን ማርያም ከመቀመጡ በፊት ቦታው የነበረውን ታሪክና አገልግሎት ይተርካል። በቦታው ስለነበረው ማኅበራዊ አስተዳደር የሹማምንትና የመኳንንት አደረጃጀት መሠረታዊ መረጃ ይሰጣል።

በመጽሐፉ መልእክት ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥም ስለቦታው መንፈሳዊ ክብር፣ ቃል ኪዳን፣ በመንፈሳዊና ዓለማዊ መሪዎች ሊሰጠው የሚገባውን ክብር ይገልጻል። የወቅቱን ሥነ ጽሑፍና የሥነ ጥበብ ደረጃም በሚገባ ያሳውቃል። በአጠቃላይ ከብዙ በጥቂቱ መጽሐፈ ጤፉት በርካታ መንፈሳዊ፣ ሥነ ጥበባዊ፣ አስተዳደራዊና ማኅበራዊ መረጃዎችን የሚሰጥ መጽሐፍ ነው።

## ስለ መጽሐፈ ጤፉት የአማርኛ ትርጉም፣ ኅትመትና ሥርጭት

መጽሐፉ ከተጻፈበት ከዐሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በግእዝ ቋንቋ ብቻ ይታወቅ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ቦታው የታላላቅ መምህራን መገኛ በመሆኑ ይኸ መጽሐፍ በቅዱሳት መጻሕፍት እንዳሉት የታሪክ መጻሕፍት እንደ ነገሥትና መሳፍንት በነጠላ ትርጉም ሳይሆን በአንድምታ ትርጉም መልክ በቃል ሲነገር የኖረ ሲሆን በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ከደብሩ ሊቃውንት አንዱ የሆኑት መሪጌታ የማነ ብርሃን አዲሴ በሌሎች ትርጓሜ መጻሕፍት ያላቸውን ሰፊ እና ጥልቅ ዕውቀት ወደ መጽሐፈ ጤፉትም በመተርጎም ይህን ታሪክ እንደመጽሐፍ አዋቂ ብቻ ሳይሆን እንደዘመናዊ ከፍተኛ ደረጃ የታሪክ ተመራማሪም ከሌሎች መጻሕፍት ጋር በማጣቀስ አብራርተው ለትውልድ ያቆዩ ባለውለታ አባት ናቸው፡፡

እኚህ ሊቅ የአባቶቻቸውን ፈለግ በመከተል በየዓመቱ ከመስከረም ፲፯-፳፩፣ በጥር ፳፩ እና በመጋቢት ፲ ግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያምንለመሳለም ለሚመጣው



ሕዝብ የመስቀሉን አመጣጥና ቃል ኪዳን ሲያስሙ ቆይተዋል፡፡ በኋላም በእቴጌ መነን ጥያቄ ለኅትመት በሚበቃ መንገድ አዘጋጅተውት የነበረ ሲሆን የደብሩ ሊቃውንት እንዲታተም አስበው ረቂቁን በዘመናዊ መሣሪያ አጽፈውት ነበር፡፡ ኋላም ወደ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ሊቃውንት ጉባኤ አስተያየት እንዲሰጥበት ቀርቦ ነበር፡፡

የመጽሐፉ ትርጉም በሰዋስው ፍች የተወሰነ አይደለም፡፡ የግእዙን ዘር ሰዋስው ከተረጐሙ በኋላ እንደአስፈላጊነቱ ታሪኩን ከሚመለከቱት የቅዱሳት መጻሕፍት ማጣቀሻዎችና በቤተ ክርስቲያኒቱ የሚታወቁ የታሪክ መዛግብትን (እንደ ስንክሣርና የቅዱሳን መላእክት ድርሳናት) እንደ ማብራሪያ ይጠቀማሉ፡፡ ስለዚህ በአቀራረቡ እስከአሁን ከምናውቃቸው የታሪክ አተረጓጎሞች ለየት ያለ አቀራረብን ይከተላል፡፡

በይዘት ደረጃ መላውን የመጽሐፈ ጤፉት በአንድ ላይ ለማካተት ካለው የአቅም ውሱንነት አንጻር ለጊዜው የምእመናንና የታሪክ ተመራማሪዎችን ፍላጎት ለማርካት በሌሎች መዛግብት የማይገኘውን የመስቀሉን ወደ

ኢትዮጵያ የመምጣት ታሪክ እና በወቅቱ የተከናወኑትን ድርጊቶች የሚገልጸውን ክፍል አቅርበናል። ወደ ፊት አቅም በፈቀደ መጠን አጠቃላይ የመጽሐፉን ይዘት ያካተተ የግእዝና አማርኛ ትርጉም ለማቅረብ የደብሩ ሊቃውንት እየደከሙ ይገኛሉ።

እግዚአብሔር ለሥራው ጊዜ አለውና መጽሐፉን ለማሳተም ቀደም ባሉት ጊዜያት ብዙ ጥረቶች የተደረጉ ሲሆን የክቡር መስቀሉ ታሪክ "ክብረ መስቀል"በተባለው መጽሔት ከአሁን በ፲፱፻፷፬ዓ/ም ታትሞ ነበር ። ነገር ግን የተዘጋጀው መጽሔት መጠነኛ በመሆኑና ለአንባቢያን ታሪኩ በሰፊው ተብራርቶ እንዲቀርብ አሁን በዚህ ወቅት እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ የመጽሐፉን መሠረታዊ ክፍል፣ ማለትም የመስቀሉን ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥና በደብረ ከርቤ ግሸን ቅድስት ማርያም የተቀመጠበትን ታሪክ ለማቅረብ የተፈለገው፤

- የመስቀል በዓል ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ትኩረት
  ተሰጥቶት በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ የባህልና የትምህርት ድርጅት አማካኝነትበ፳፻ወ፮ ዓ/ም የሰው ልጅ ዐለም አቀፍ ቅርስ ተብሎ መመዝገቡ፣
- በዚሁ ዓለም አቀፍ ዕውቅናምየግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያምን ደብር ጨምሮ በሀገራችንተያያዥነት ያላቸው ሌሎች መሠረታዊ ታሪኮች ሁሉ ዕውቅና ያገኙ በመሆኑ
- የመስቀሉ ታሪክና ክብር፣ ለቦታውን የተሰጠውን ቃል ኪዳን ለማወቅ በምእመናንና ተመራማሪዎች ዘንድ ያለው ፍላጎት እያደገ በመምጣቱ፣

ከዚህ ጊዜ የበለጠ መልክም አጋጣሚ እንደሌለ በማሰብ ይህ መጽሐፍ ለኅትመት እንዲበቃ አድርገናል።

ይህን መጽሐፍ ወደ አማርኛ ቋንቋ ለመተርጎምና ለኅትመት እንዲበቃ ለማድረግ ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ሊቅ መሪጌታ የማነ ብርሃን አዲሴ እና ሌሎችም በርካታ የደብሩ ሊቃውንት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የደብሩ ሰበካ ጉባኤ አባላት፣ አገልጋይ ካህናትና መዘምራን እንዲሁም የደብሩ ወጣቶች ሁሉ የየበኩላቸውን አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ ለግሽን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ደብር መምህር ኾነው ከተሾሙ ጊዜ ጀምሮ ትውልድ የማይረሳው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት ሊቀ ሊቃውንት ተክለ ማርቆስ ብርሃኑ ዋናው ናቸው።

ሊቀ ሊቃውንት ተክለ ማርቆስ ብርሃኑ የደብሩን ልማት በማሳደግ፣ በየጊዜው ወደቦታው የመስቀሉን በረከትና ክብር፣ የቦታውን ቃል ኪዳን ለማግኘት ከመላው ዓለምና ከመላው ኢትዮጵያ የሚመጡ መንፈሳዊ ተጓዦችን በአግባቡ እንዲስተናገዱ በማስቻልቦታዋ የበለጠ ታውቃና ተከብራ እንድትኖር አድርገዋል። አሁን ደግሞ ይኽ ታላቅ ታሪካዊመጽሐፍ የቀድሞ የትርጉም ይዘቱን እንደጠበቀና የቦታውን ትውፊት እንደያዘ በግእዝና በአማርኛ እንዲዘጋጅና እንዲታተም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የሀገረ ስብከታችን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስም ለመጽሐፉ ዝግጅት/ኅትመት መመሪያና ቡራኬ ከመስጠት ጀምሮ ያደረጉት የክትትል ድጋፍ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው።



በአጠቃላይ ይኽን መጽሐፍ ከዐሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከ፭፻፶ ዓመታት በፊት በልዩ ሁኔታ ያዘጋጁትን፣እስከ አሁን ጠብቀው ያቆዩ የደብሩ ሊቃውንትን፣ በአሁኑ ዘመን በአማርኛ እየተረጐሙ በቃል ለትውልድ ሲያስተምሩበት የቆዩት መምህራንን፣ አሁን ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለመላው አንባቢ እንዲደርስ ያደረጉ ሊቃውንትን፣ የሰበካ ጉባኤ አባላትን፣ የደብሩ ወጣቶችን፣ ለመጽሐፉም ኅትመት ስኬታማነት የተራዱንን ሁሉ የእግዚአብሔር ቸርነትና ምኅረት፣ የእመቤታችን ጸሎት፣ የቅዱስ መስቀሉ በረከት ይድረሳቸው። አሜን።

የግሽን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ደብር ሰበካ ጉባኤ፡

ደቡብ ወሎ ፣አምባሰል።

መጋቢት ፳፻፪ ዓ/ም

## ምዕራፍ ፩

## ምዕራፍ ፩

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ሕያው ዘከመ ተረከበ መስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ መንግሥቱ ለዳግማዊ ዳዊት ዘተሰምየ መስዔ ረሲዓን ወጥቅመ አድማስ።

በአብ ስም አምነን አብን ወላዲ ብለን በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መንፈስ ቅዱስን ሠራዒ ብለን ለአጠይቆ አካላት ሦስት ስለአልን በባሕርይ በሕልውና ፩ አምላክ ብለን አምነን እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ መስዔ ረሲዓን ጥቅመ አድማስ በተባሉት በዳግማዊ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክቡር መስቀል እንደተረከቡ።

ወዘከመ መጽአ ውስተ ብሔረ ኢትዮጵያ በ መዋዕለ መንግሥተ ወልዱ ዘርዓ ያዕቆብ።

ልጃቸው ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በነገሡበት ዘመንም ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣ።



ወቦአ ውስተ ደብረ ነገሥት ዘሀገረ አምባሰል።

ወጥቶም በአምባሰል ውስጥ በምትገኝ ደብረ ነገሥት በምትባል ተራራ ገብቶ እንደ ተቀመጠ እንናገራለን።

ወይእቲ ደብረ ከርቤ ዘዓተባ በደሙ ቅዱስ ለክርስቶስ ሊቀ መላእክት ዑራኤል።

ይህችም ደብረ ነገሥት የምትባለው መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል በጌታችን በክርስቶስ ቅዱስ ደም ቀብቶ ያከበራት ዛሬ ደብረ ከርቤ እየተባለች የምትጠራው ናት።

ወአልአለ ክብራ እምክብረ ኵሉን አድባራት።

ክብሯንም ከአድባራት በላይ አድርጐ አከበራት ከ፮ቱ ዕለታት ለይቶ ሰንበትን እንደ አከበረ ይህችንም ቦታ አክብሯታልና።

ወሰመያ ደብረ ከርቤ።

ስሟንም ደብረ ከርቤ ብሎ ጠራት።

| | |
|---|---|
| ስምዑ ወለብው ዘከመ ኮነ ምክንያተ ምጽአቱ። | መስቀሉ የመጣበትን ምክንያት ጠንቅቀን አብራርተን እንነግራችኋለንና ጆሮአችሁን ከፍታችሁ ልቡናችሁን አንቅታችሁ ስሙ፤ |
| በ፷፻ ወበ፰፻ ፳ወ፰ ዓመት እምፍጥረተ ዓለም። | ዓለም በተፈጠረ በስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ስምንት ዓመት |
| በ፲፻ ወ፫፻ ፳ወ፰ ዓመት እምልደተ መድኃኒነ | ጌታ በተወለደ በሺህ ሦስት መቶ ሃያ ስምንት ዓመት። |
| በ፲፻ ወበ፶ወ፭ ዓመተ ሰማዕታት ንጉሐን ነገሠ ሰይፈ አርዓድ ወልደ ዓምደ ጽዮን ንጉሥ | በሺህ አምሳ አምስት ዓመተ ሰማዕታት የዓፄ ዓምደ ጽዮን ልጅ ዓፄ ሠይፈ አርዓድ ነገሠ። |
| ወበመዋዕሊሁ አሠሮ ንጉሠ ተንባላት ዘስሙ | በሳቸው ዘመን ነግሦ የነበረው የአሕዛብ ንጉሥ |



| | |
|---|---|
| መርዋን እልጋዲን ለሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤል ዘሀገረ እስክንድርያ። | መርዋን እልጋዲን የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤልን አሠራቸው። |
| ወውእቱ እምኍልቈሙ ለ፵ወ፯። | እሳቸውም ቀደም ብለው በእስክንድርያ ተሹመው ለነበሩ ለሊቃነ ጳጳሳቱ ዓርባ ሰባተኛ ሆነው የተሾሙ ናቸው። |
| ወይቤሎ አምጽእ ሊተ ንዋየ ብዙኃ። | ብዙ ገንዘብ ለእኔ ገብር ብሎ አሠራቸው። |
| ወወርቀ ዘሀሎ ውስተ እዴከ። | በእጅህ ያለውንም ወርቅ አምጣ ብሎ። |
| ወይቤሎ አባ ሚካኤል ሊቀ ጳጳሳት "አልብየ ወኢምንትኒ እምንዋየ ወርቅ ወብሩር ዘእሁበከ። | አባ ሚካኤልም "እኔ ለአንተ የምገብረው ምንም ገንዘብ የለኝም" አሉት። |

| | |
|---|---|
| ወርቅሰ ዘሀሎ ውስተ እዴየ ቀዳሚ አምኃሁ ለአቡነ አዳም እምዘሀሎ ውስተ ገነት። | በእጄ ያለው ወርቅ ግን መጀመሪያ በገነት ሳለ ለአባታችን ለአዳም ከጌታ ዘንድ የተሰጠ ነው። |
| ወበደኃሪ መዋዕል አምጽኡ ሎቱ ሰብአ ሰገል ዘንተ ወርቀ አምኃ ለእግዚእነ። | በኋለኛው ዘመንም ጌታ ሰው በሆነ ጊዜ ይህንኑ ወርቅ ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ አድርገው ያመጡለትና የገበሩለት ነው ። |
| ወበጽሐ እስከ ዘመነ አበውየ ወአነሂ ነሣእክዎ እምኔሆሙ። | ከዚያም ሲወርድ ሲዋረድ ከእኔ በፊት ከነበሩ ሊቃነ ጳጳሳት ደርሶ ከእነሱ ያገኘሁትና በአደራነት የተረከብኩት ነው። |
| ወበእንተዝ ኢይደልወኒ አሀብከ ዘንተ እስመ ክቡር ውእቱ። | ስለዚህ ክቡር ነውና ይህን ልሰጥህ አይገባኝም። |



| | |
|---|---|
| ወሊተኒ ሐሣረ ይከውነኒ በቅድመ እግዚእየ። | ለአንተ ለማይገባህ ይህን ክቡር ወርቅ ብሰጥ በፈጣሪዬ ፊት ያስወቅሰኛልና አሉት። |
| ወበምክንያተ ዝንቱ አሠሮ። | ለእኔ ካልገበርክስ ብሎ በዚህ ምክንያት አሠራቸው። |
| ወሶበ ሰምዓ ንጉሠ ኢትዮጵያ ሰይፈ አርዓድ ከመ ኰነንዎ መኳንንተ ተንባላት ለዝንቱ አብ ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤል ወሞቅሕዎ። | ዓፄ ሠይፈ አርዓድም የአሕዛብ ንጉሥ አባ ሚካኤልን አገዛዝ እንደ አጸናባቸውና እንደ አሠራቸው በሰሙ ጊዜ። |
| ቀንዓ ቅንዓተ መንፈሳዊተ በእንተ ዘኮኑ እስክንድርያ ወኢትዮጵያ አሐተ ሃይማኖተ። | እስክንድርያና ኢትዮጵያ በሃይማኖት አንድ ስለሆኑ የአሕዛብ ንጉሥ ይህን ያህል ይታበያልን ብለው በመንፈሳዊ ቅንዓት ቀኑ። |
| ወወረደ ብሔረ ግብፅ | ቀንተውም አልቀሩም |

| | |
|---|---|
| ዘምስለ ብዙኃ ሠራዊት፡፡ | ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ግብፅ ዘመቱ፡፡ |
| ወአመዝበረ አህጉራተ ብዙኃተ፡፡ | ወርደውም ብዙ አገር አጠፉ ማርከውም ወሰዱ፡ |
| ወሶበ ሰምዓ ንጉሠ ተንባላት ምጽአቶ ለንጉሠ ኢትዮጵያ፡፡ | ያም የአሕዛብ ንጉሥ የዓፄ ሠይፈ አርዓድን መምጣት በሰማ ጊዜ፡፡ |
| ወመልእክቶ ዘይብል ሶበ በጽሐ መጽሐፈ መልእክትየ ኀቤከ ፍትሖ ለሊቀ ጳጳሳት ወእመ አኮሰ ኢይከውን ፍቅር ማዕከሌነ ወማዕከሌከ፡፡ | ይህ ደብዳቤ እንደደረሰህ ሊቀ ጳጳሳቱን ፍታ፡፡ ባትፈታቸው ግን በእኛና በአንተ መካከል ፍቅር አይገኝም የሚል ጽፈው የላኩት ደብዳቤ በደረሰው ጊዜ፡፡ |
| ወፈትሖ ለሊቀ ጳጳሳት፡፡ | ደብዳቤውን አይቶ ሊቀ ጳጳሳቱን ከእሥራታቸው ፈታቸው፡፡ |



| | |
|---|---|
| ወአክበሮ ክብረ ዓቢየ፡፡ | በታላቅ ክብር አክብሮ አኖራቸው፡፡ |
| ወፈነወ ሎቱኒ አምኃ ብዙኃ ወርቀ ወብሩረ፡፡ | ይህን ከሠራ በኋላ ለሳቸውም እጅ መንሻ ብዙ ወርቅ ብዙ ብር ላከላቸው፡፡ |
| ወንጉሠ ኢትዮጵያ ሰይፈ አርዓድ ፈነወ ለሊቀ ጳጳሳት ብዙኃ ወርቀ ከመ ያንብሮ ዘምስለ ወርቅ አምኃሁ ለእግዚእነ ወከመ ይኩኖ ለበረከት፡፡ | የኢትዮጵያ ንጉሥ ዓፄ ሰይፈ አርዓድም ለበረከት ይሆናቸው ዘንድ የጌታችን እጅ መንሻ ከሆነው ወርቅ ጋር እንዲያስቀምጡት ለሊቀ ጳጳሳቱ ብዙ ወርቅ ሰደዱላቸው፡፡ |
| ወእምዝ ገብአ ብሔሮ በሰላም | ዓፄ ሰይፈ አርዓድም ሊቀ ጳጳሳቱን ከእሥራት አስፈትተው ከአስማሙ በኋላ ወደ ሀገራቸው በሰላም ተመለሱ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ወሞተ በ፷ወ፰ ዓመተ መንግሥቱ:: | ተመልሰውም በነገሡ በሃያ ስምንት ዓመት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ። |
| ወእምድኅሬሁ ነግሠ ውድም አስፌሬ ወልዱ ፲ ዓመተ:: | ከሳቸውም በኋላ ልጃቸው ውድም አስፌሬ ዐሥር ዓመት ነገሡ:: |

## ምዕራፍ ፪ | ምዕራፍ ፪

| | |
|---|---|
| ወእምዝ በ፶፻ወ፰፻፷ወ፮ ዓመት እምፍጥረተ ዓለም:: | ከዚህ በኋላ ዓለም ከተፈጠረ በስድስት ሺህ ስምንት መቶ ስድሳ ስድስት ዓመት:: |
| በ፲፻ወ፫፻ ፷ወ፮ እምዓመተ ልደቱ ለመድኅኒነ | ጌታ በተወለደ በሺህ ሦስት መቶ ስድሳ ስድስት ዓመት:: |
| በ፲፻ ፷ወ፮ እምዓመተ ሰማዕታት ንጉሐን ነግሠ ዳግማዊ ዳዊት:: | በሽህ ስድሳ ስድስት ዓመተ ሰማዕታት ዳግማዊ ዳዊት ነገሡ:: |



| | |
|---|---|
| ወአስተራትዓ ሃይማኖተ:: | የተዋሕዶ ሃይማኖት በበለጠ እንዲስፋፋ አደረጉ:: |
| ወአቀመ ተዝካረ በዓላ ለእግዝእትነ ማርያም ። | የእመቤታችን ድንግል ማርያምን በዓል በየወሩ እንዲከበር አደረጉ:: |
| ወአጽሐፈ መጽሐፈ ድርሳናቲሃ ወተአምራቲሃ ወአሠርገዎን በወርቅ ወበብሩር:: | ተአምሯን ድርሳኗን በወርቅ በብር በልዩ ልዩ ቀለም አስጊጠው አጻፉ:: |
| ወሥዕለ ዚአሃኒ ያሥዕል በወርቅ ወበዕንቍ:: | የእመቤታችንን ሥዕልም በወርቅ በዕንቍ ያሥሉ ነበር:: ከዚህም ለማስረጃ ያህል በወርቅ ቀለም ያጻፉት ተአምረ ማርያም በወርቅ ቀለም ያሣሏት የእመቤታችን ሥዕል ብዙ ገቢረ ተአምራት የምታደርግ በደብረ ከርቤ ትገኛለች:: |

| | |
|---|---|
| ወበመዋዕሊሁ መጽአ መስቀለ ክርስቶስ ውስተ ሀገረ ኢትዮጵያ። | በዘመነ መንግሥታቸውም የጌታችን መስቀል ወደሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ መጣ። |
| ወምክንያተ ምጽአቱስ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተ ሀገረ ኢትዮጵያ። | የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ የመጣበትም ምክንያትም ይህ ነው። |
| ወሶበ ሰምዓ ንጉሠ ምስር ከመ ሞተ ሰይፈ አርዓድ አቡሁ ለዳግማዊ ዳዊት። | ዓፄ ሰይፈ አርዓድ ከሞቱ በኋላ የምስሩ ንጉሥ ሞታቸውን በሰማ ጊዜ። |
| አሠሮ ዳግመ ለሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤል። | እሱ ከሞተማ ብሎ አባ ሚካኤልን ዳግመኛ አሠራቸው። |
| ወለአኩ ሰብአ ሮም ወቍስጥንጥንያ ወሶርያ ወአርመን ወግብፅ ኀበ ንጉሠ ኢትዮጵያ ዳግማዊ ዳዊት። | በዚህን ጊዜ የሮም፣ የቍስጥንጥንያ፣ የሶርያ፣ የአርመን፣ የግብፅ ክርስቲያኖች በአንድ ሆነው ከኢትዮጵያው |



| | |
|---|---|
| | ንጉሥ ከዓፄ ዳዊት ዘንድ መልእክት ላኩ። |
| እንዘ ይብሉ። | እንዲህ ብለው። |
| እስመ ተንሥኡ ላዕሌነ መኳንንተ ተንባላት ከመ ያጽርእዎ ለሃይማኖተ ክርስቶስ። | የክርስቶስን ሃይማኖት ለማጥፋት የእሕዛብ ነገሥታት |
| ወከመ ኢንጸውዕ ስሞ ክቡረ። | ክቡር ምስጉን የሚሆን ስሙንም እንዳንጠራ። |
| ወከመ ኢንሰግድ ለመስቀል ክቡር። | ክቡር ለሚሆን ለመስቀሉም እንዳንሰግድ ወደ እኛ ሃይማኖት ግቡ ብለው ተነሥተውብናልና። |
| ንስዕለከ ከመ ትትራድአነ ወታድኅነነ እምንጉሠ ተንባላት ወእም መኳንንቲሁ። | መጥተህ ከእሕዛቡ ንጉሥና በሥራ ተባባሪዎቹ ከሆኑት ከመኳንንቱ ታድነን ዘንድ እንለምንሃለን ብለው ላኩበት። |

| | |
|---|---|
| ወሶበ ሰምዓ ንጉሠ ኢትዮጵያ መፍቀሬ እግዚአብሔር ዳግማዊ ዳዊት:: | የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆኑ ዓፄ ዳዊትም ይህን በሰሙ ጊዜ:: |
| ተከዘ ወኃዘነ ብዙኃ:: | የአሕዛብ ንጉሥ በእኔ ዘመን ይህን ያህል ይታበያልን ብለው ፈጽመው አዘኑ:: |
| ወቀንዓ ቀንዓተ መንፈሳዊተ:: | ከዚህ በኋላ መንፈሳዊ ቅንዓት አድሮባቸው:: |
| ወተንሥአ ይሖር ብሔረ ግብፅ ከመ ይጽብዖ ለንጉሠ ምስር ወለመኳንንቲሁ:: | "እኔ ከአባቴ ብበልጥ እንጂ አንሳለሁን" ብለው ከምስሩ ንጉሥ ጋር ለመዋጋት ግብፅ ሊዘምቱ ተነሡ:: |
| ወበእንተ ዘአሠሮ ለሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ አባ ሚካኤል:: | የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤልን ስለአሠራቸው:: |



| | |
|---|---|
| ወበእንተ ዘኀደገ ኪዳነ ዘተካየደ ምስለ አቡሁ ሰይፈ አርዓድ:: | መጀመሪያ ከአባታቸው ከዓፄ ሰይፈ አርዓድ ጋር ሁለተኛ በክርስቲያን ላይ ከፍቅር በቀር ጸብ ላያነሣ ተማምለው የነበረውን መሐላ በማፍረሱ:: |
| ወኮኑ ሠራዊቱ እለ ወረዱ ምስሌሁ ብሔረ ግብፅ ፲፼ አፍራሰ ወ፲፼ አብቅልተ ወ፲፼ አግማለ:: | ከሳቸውም ጋር ግብፅ የወረደው የሠራዊታቸው ብዛት ዐሥር እልፍ ፈረሰኛ ዐሥር እልፍ ባለበቅሎ ዐሥር እልፍ ባለግመል ሆኑ:: |
| ወሶበ በጽሐ ኀበ ካርቱም:: | ከሀገረ መንግሥታቸው ተነሥተው ካርቱም ሲደርሱ፣ |
| ወጠነ ከመ ይሚጦ ለፈለገ ዓባይ ከመ ይክልአሙ ማየ ፈለገ ዓባይ ዘይሰመይ ግዮን ለሰብአ ግብፅ:: | ግዮን የሚባለውን የዓባይን ውሀ መልሰው ወደ ካርቱም በረሐ ሰደዱት:: |

| | |
|---|---|
| እስመ አልቦሙ ማይ ወኢክረምት ዘእንበለ ፈለገ ኢትዮጵያ ዘውእቱ ግባይ፡፡ | የግብፅ ሰዎች ግባይ ከተባለው ከኢትዮጵያ ወንዝ በቀር ወሀ የላቸውምና፡፡ |
| ወሶበ ሰምዐ ንጉሠ ምስር አህመድ ወልደ መርዋን እልጋዲን ወመኳንንቲሁ ተንባላት፡፡ | የምስሩ ንጉሥ የመርዋን እልጋዲን ልጅ አህመድ እና መኳንንቱም ይህን በሰሙ ጊዜ፡፡ |
| እእመሩ ከመ ዝንቱ ኵሉ ዘኮነ በእንተ ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤል፡፡ | ይህ የሆነው ሊቀ ጳጳሳቱን አባ ሚካኤልን በማሠራቸው እንደሆነ ዐወቁ ተረዱት፡፡ |
| ደንገጸ ወፈትሖ እመ - ዋቅሕቲሁ፡፡ | ደንግጦም አባ ሚካኤልን ከእሥራታቸው ፈታቸው ፡፡ |
| ወአክበሮ ክብረ ዓቢየ፡፡ | ፍጹም ክብር አከበራቸው፡፡ |
| ወከማሁ ለኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን፡፡ | ከሞት የተረፉትን ምእመናንም ከግዞት ነፃ አወጣቸው፡፡ |



| | |
|---|---|
| ወእምዝ ሰአሎ ንጉሠ ምስር ለዝንቱ አብ ክቡር አባ ሚካኤል፡፡ | ዓፄ ዳዊት የፈጸሙትን የቆራጥነት ሥራ ከሰማ በኋላ የምስሩ ንጉሥ ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤልን ይለመናቸው ጀመር፡፡ |
| ወለኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን ዘኢየሩሳሌም ወሶርያ ወአርማንያ ወሮም ወቍስጥንጥንያ፡፡ | በኢየሩሳሌም፣ በሶርያ በአርማንያ፣ በሮም በቍስጥንጥንያ፣ ያሉ ምእመናንንም ይለምን ጀመር፡፡ |
| ከመ ይፈንው መልእክተ ኀበ ንጉሠ ኢትዮጵያ መፍቀሬ እግዚአብሔር ዳግማዊ ዳዊት፡፡ | የእግዚአብሔር ወዳጅ ወደሚሆኑ ወደ ዓፄ ዳዊት ዘንድ ላኩልኝ ለምኑልኝ ብሎ መልእክት ይልኩ ዘንድ፡፡ |
| ወከመ ይሰአልዎ ይትመየጥ ብሐሮ በሰላም፡፡ | በፍቅር በሰላም ሆኖ ወደ ሀገሩ ይመለስ ዘንድ ለምኑልኝ ብሎ ይለምናቸው ጀመር፡፡ |

ወመሐለ ሎሙኒ ከመ ኢይሥዓር ሃይማኖቶሙ ወከመ ኢይወልጥ ሥርዓታቲሆሙ። ወከመ ኢያንስእ ጸብዓ ላዕሊሆሙ ዳግመ።

እኔም ሃይማኖታችሁን ለውጡ የፈጣሪአችሁን ስም አትጥሩ ሕጋችሁን ሥርዓታችሁን ለውጡ ብየ አልጣላችሁም። ዳግመኛም ከፍቅር በቀር ጸብ ክርክር አላነሣም ብሎ በሃይማኖቱ ማለላቸው።

ወሰሚዖሙ እሙንቱ ተፈሥሑ ወሰብሕዎ። ለእግዚአብሔር በእንተ ዘአድኀኖሙ እምኵነኔ ተንባላት።

እነዚህም ምእመናኑ ይህን መሐላ በሰሙ ጊዜ በዓፄ ዳዊት አድሮ ከአሕዛብ አገዛዝ ነፃ ስለአወጣቸው እግዚአብሔርን ፈጽመው አመሰገኑት።

ወለአኩ ወፈነውዎ ለዝንቱ አብ ክቡር አባ ሚካኤል ምስለ ብዙኃን መኳንንተ ግብፅ ወምስሌሆሙ ፲ወ፪፼ ዲናረ ወርቅ አምኃሁ ለንጉሠ ኢትዮጵያ።

ምእመናኑም መክረው ደብዳቤ ጽፈው ሊቀ ጳጳሳቱን አባ ሚካኤልን መኳንንቱም ዐሥራ ሁለት እልፍ ወቄት ወርቅ እጅ መንሻ አስይዘው ወደ ዓፄ ዳዊት ላኩ።



ምስለ መጽሐፈ መልእክት ዘይብል እግዚአብሔር ይባርክ ላዕሌከ ወላዕለ መኳንንቲከ ወላዕለ ሠራዊትከ ወመሳፍንቲከ እስመ ናሁ አድኃነነ እግዚአብሔር እማዕሠረ መዋቅሕት ወእምኵነኔ ተንባላት በእንቲአከ።

እግዚአብሔር በአንተ አድሮ ከአሕዛብ አገዛዝና ከግዞት ነፃ አውጥቶናልና እግዚአብሔር መንግሥትህን ያስፋ፣ ሠራዊትህን ያብዛ መኳንንትህንና መሳፍንትህን ይጠብቅ የሚል የምርቃን ደብዳቤ ጭምር ላኩ።

ወይእዜኒ ተመየጥ ኀበ ብሔርከ በዳህና ወበሰላም።

አሁንም ወደ ሀገርህ በፍቅር በደስታ ተመለስ።

ወእግዚአብሔር ይዕሢከ በመንግሥተ ሰማያት ህየንተ ዘፃመውከ በእንቲአነ።

ለእኛ ብለህ ስለ ደከምከውም ድካም ሁሉ ዋጋህን እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ዕጽፍ ድርብ አድርጐ ይከፈልህ

ወሰበ ሰምዓ ንጉሠ ኢትዮጵያ ዳግማዊ ዳዊት

ዓፄ ዳዊትም ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ሚካኤል

| | |
|---|---|
| ምጽአቶ ለሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤል። | ከእሥራታቸው ተፈትተው ወደሳቸው እንደመጡ በሰሙ ጊዜ። |
| ወረደ ምስለ ኀዳጣን ሠራዊቱ እስከ ምድረ እስዋን። | ምርጥ የሆኑ ጥቂት የጦር አበጋዞቻቸውን ይዘው እሰዋን ድረስ ወረዱ። |
| ዘውእቱ ወሰን ማዕከለ ኢትዮጵያ ወግብፅ። | ይኸ እስዋን የተባለው የኢትዮጵያና የግብፅ ወሰን ድካ የነበረው ነው። |
| ወተራከበ በህየ ምስለ ሊቀ ጳጳሳት ወምስለ መኳንንተ ግብፅ። | ከዚህም ቦታ ሲደርሱ ሰኔ ፲ ቀን ከሊቀ ጳጳሳቱ እና ከመኳንንቱ ጋር ተገናኙ። |
| ወወሀብዎ መጽሐፈ መልእክቶሙ ለእሉ ዘተናገርነ ቀዳሚ። | አስቀድመን የተናገርናቸው ምእመናን የጻፉላቸውን ደብዳቤ ሰጧቸው። |
| ወአቅረቡ ሎቱ አምኃ ፲ወ፪፻ ዲናረ ወርቅ። | ያመጡትን ዐሥራ ሁለት እልፍ ወቄት ወርቅ እጅ መንሻ አቀረቡላቸው። |



| | |
|---|---|
| ውእቱኒ ሰብሖ ለእግዚአብሔር በእንተ ዘአድኃኖሙ ለክርስቲያን እምኵነኔ ተንባላት በእንቲአሁ። | ዓፄ ዳዊትም ይህን አይተው እግዚአብሔር በእሳቸው አድሮ ወዳጆቹ ምእመናንን ከአሕዛብ አገዛዝ ነፃ ስለአወጣቸው ፈጣሪያቸው አመሰገኑ። |
| ወለአከ ኀበ ንጉሠ ምስር ወመኳንንተ ተንባላት። | ከዚህ በኋላ ዓፄ ዳዊት ወደ ምስሩ ንጉሥና ወደ መኳንንቶቹ መልስ ጻፉ። |
| እንዘ ይብል። | እንዲህ ብለው። |
| ሠናየ ገበርክሙ በእንተ ዘገበርክሙ ዕርቀ ምስለ ክርስቲያን አኃዊክሙ። | በተፈጥሮ ወንድሞቻችሁ ከሚሆኑ ከክርስቲያን ጋር መታረቃችሁ በጐ አደረጋችሁ። |
| ወእምይእዜሰ አጽንዑ መሐላክሙ። ወኢታንሥኡ ጸብዓ ምስለ ክርስቲያን። | ከእንግዲህም በኋላ ዕርቃችሁን አጽኑ፣ መሐላችሁን አታፍርሱ ሃይማኖታችሁን ለውጡ እያላችሁ ጸብ አታንሡ። |

| | |
|---|---|
| ወእምሰ ኢገበርክሙ ዘንተ እም አማሰንኩ ሀገረክሙ ወብሔረክሙ። | ከወንድሞቻችሁ ከክርስቲያን ጋር ባትታረቁ ኖሮ ሀገራችሁን ባጠፋሁትም ነበር። |
| ወእምጸናዕኩ ለተቃትሎትክሙ። | እናንተን ለማጥፋት ያለኝን ሐሳብ አልለውጥም ነበር። |
| ወእምዝ ሰአልዎ ከመ ይሚጥ ሎሙ ፈለገ ዓባይ ከመ ይስተዩ ሰብአ ግብፅ እምኔሁ። | ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱንና መኳንንቱ የዓባይን ወሀ መልሰው እንዲሰዱላቸው ለመኑአቸው። |
| ውእቱኒ አበየ ተመጥወ እምኃ ፲ወ፪፻ ዲናረ ወርቅ። | ዓፄ ዳዊትም ውሀውን አልመልስም ይህንም እጅ መንሻ ወርቅ አልቀበልም ብለው መለሱት። |
| እንዘ ይብል ወርቅሰ ወብሩር ኢይበቊዕ ለመድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ። | እንዲህ ብለው ወርቅና ብር የእኛን ነፍስ ለማዳን አይረባም አይጠቅምም አያድንም። |



| | |
|---|---|
| አላ ለእከ ኀበ ኵሎሙ ክርስቲያን ዘኢየሩሳሌም ወሮም ወሶርያ ወአርማንያ። | ኢየሩሳሌም፣ ሮም ሶርያና አርማንያ ወደ አሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ላኩ እንጂ። |
| እንዘ ይብል። | እንዲህ ብለው። |
| አንሰ ኢይትዌከፍ አምኃክሙ ወርቀ ወብሩረ። | እኔ የላካችሁትን እጅ መንሻ ወርቅና ብር አልቀበልም። |
| አላ መዲጥየ ፈነኩ ለክሙ። | መልሼ ሰድጃላችሁአለሁ እንጅ። |
| እስመ ኢያድኃነነ እግዚአብሔር በወርቅ ወብሩር አላ አድኃነነ በደመ መስቀሉ። | እግዚአብሔር በመስቀል ተሰቅሎ በከበረ ደሙ ፈሳሽነት አዳነን እንጂ በወርቅ በብር አላዳነንምና። |
| ወእንሰ እፈቅድ ከመ ትፈጽሙ ፈቃደ ልብየ | እኔ ግን በልቤ ያሰብኩትን ሐሳብ ትፈጽሙልኝ ዘንድ ነው እንጂ። |

ወከመ ተሀቡኒ መስቀሎ ለክርስቶስ ዘተከዕወ ደሙ ቅዱስ ላዕሌሁ ዘሀሎ በኀበ እዴሁ ለሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ።

በክበረ ደሙ ፈሳሽነት የከበረየጌታችን የክርስቶስ መስቀል በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት እጅ ያለውን ትሰጡኝ ዘንድ ነው እንጂ።

ወሰበ ሰምዑ መልእክቶ ለንጉሠ ኢትዮጵያ መፍቀሬ እግዚአብሔር ዳዊት ኵሎሙ ክርስቲያን

እነሱም እግዚአብሔርን የሚወድ የኢትዮጵያ ንጉሥ የዓፄ ዳዊትን መልእክት በሰሙ ጊዜ።

መከሩ ምክረ ዓቢየ ምስለ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ።

ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ጋር ታላቅ ምክርን መከሩ።

ከመ ይፈንው ሎቱ መስቀሎ ለክርስቶስ ክቡር።

ክቡር የሚሆን የጌታችን የክርስቶስን መስቀል ይሰዱላቸው ዘንድ መከሩ።

እንዘ ይብሉ።

እንዲህ ብለው።

ይደልዎ ከመ ንፈኑ ሎቱ እስመ ውእቱ ኢኃሠሠ ወርቀ ወብሩረ።

መንፈሳዊ ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን ወርቅ ብር አይሻምና ልንሰድለት ይገባዋል ብለው መከሩ።

አላ ቀንዓ ቅንዓተ መንፈሳዊተ ለሀገረ መንግሥቱ ኢትዮጵያ።

እሱም መንፈሳዊ ቅንዓቱ የሀገሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሚድኑበት እንጂ።

በዘይድኅኑ ሰብአ ኢትዮጵያ በዝንቱ መስቀል ክቡር ዘእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እም - አባር ወእምኃጢአ ዝናም ወእምኵሉ ደዌ ወመቅሠፍት ሕማም ወመንሱት።

የኢትዮጵያ ሰዎች በዚሁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ከረኃብ ከድርቅ ከዝናብ እጦት ከመዓት ልዩ ልዩ ከሆነ ከፍጹም ጥፋት ይድኑበት ዘንድ ነውና ይገባዋል አሉ።

ወንጉሠ ምስርሰ አህመድ ወመኳንንተ ተንባላት ተሐውኩ ብዙኃ በምክንያተ ዝንቱ።

በዚህ ምክንያት የአሕዛቡ ንጉሥ አህመድንና መኳንንቱ ፈጽመው ታወኩ።

ወመፍቀሬ እግዚአብሔር ዳዊት ለአከ ኀቤሆሙ።

ዓፄ ዳዊት ግን ወደ እነሱ መልእክት ላኩባቸው።

እንዘ ይብል።

እንዲህ ብለው።

አንስ ኢይመይጥ ማየ ዓባይ ፈለግ ዘብሔርየ ኣላ አኃድጋ ለሀገርከሙ ትትመዘበር በኃጢአ ማይ

መስቀሉን ካልሰጣችሁኝ ሀገራችሁ በድርቅ ፈጽማ ትጥፋ እንጂ የሀገሬን ወሀ አልመልስም ብለው ላኩ።

ወሰሚያሙ እሙንቱ ቃሎ መከሩ ምክረ ሠናየ በዘመከሩ ክርስቲያን

እነሱም ዓፄ ዳዊት የላኩትን ቁርጥ ሐሳብ ሰምተው ምእመናኑ እንደ መከሩት ይውሰድ ብለው በጐ ምክርን መከሩ።

ወእምዝ ኀቢሮሙ ፈነው ሎቱ ክርስቲያን ወተንባላት መስቀሎ ለክርስቶስ።

ከዚህ በኋላ አሕዛብም ክርስቲያኖቹም አንድ ሆነው ተስማምተው ከነሱ ዘንድ የነበረው የጌታችንን መስቀል ሰደዱላቸው።

ወሥዕላተ እግዝእትነ ማርያም ሰብዐ ዘሠዓሎን ሉቃስ ወንጌላዊ።

መስቀሉን ብቻ ሳይሆን ሉቃስ የሣላቸውን ሰባቱን የእመቤታችንን ሥዕሎች።



ወሥዕለ ኵርዓተ ርእሱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሠዓሎ ዮሐንስ ወንጌላዊ።

ዮሐንስ ወንጌላዊ የሣለውን የጌታችንን የኵርዓተ ርእሱን ሥዕል።

ህየንተ ዘሜጠ ሎሙ ፲ወ፪፻ ዲናረ ወርቅ ዘአምጽኡ ሎቱ።

እጅ መንሻ ብለው የላኩለትን ዐሥራ ሁለት ወቄት ወርቅ መልሶ ስለሰደደላቸው።

ወወሀብዎ እሉንተ ንዋያተ ክቡራት አባ ሚካኤል ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ወመኳንንተ ግብፅ።

እነሱም ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ሚካኤልና መኳንንቱ ሆነው ይህን መስቀሉንና ሥዕላቱን እጅ መንሻ አድርገው ሰጧቸው።

ውእቱኒ መፍቀሬ እግዚአብሔር ዳግማዊ ዳዊት ተንሥአ በክብር ዓቢይ ወሰገደ ለመስቀለ እግዚእነ ወለሥዕላተ እግዝእትነ ወለኵርዓተ ርእስ።

እግዚአብሔርን የሚወዱ ዳግማዊ ዓፄ ዳዊትም በፍጹም ደስታና ክብር ተነሥተው ለጌታችን መስቀል፣ ለእመቤታችንና ኵርዓተ ርእሱ ሥዕሎች ሰገዱላቸው።

| | |
|---|---|
| ወእምዝ ተመጠዎሙ በእዴሁ እምድኅረ ፈጸመ አምኆቶሙ። | እጅ ነሥተው ካበቁ በኋላ በእጃቸው ተቀበሏቸው |
| ዝንቱ ኩሉ ኮነ አመ ፲ ለመስከረም። | ይህ ሁሉ ተፈጽሞ የተቀበሉበት መስከረም ፲ ቀን ነው። |
| ወኮነ ብርሃን በኢትዮጵያ ወበኩሉ አድያሚሃ | መስቀሉን በተቀበሉበት ጊዜ በኢትዮጵያና በአውራጃዎችዋ ሁሉ ብርሃን ሆነ። |
| ወተፈሥሑ ዓቢየ ፍሥሐ ሕዝብ ወአሕዛብ ዕድ ወአንስት አዕሩግ ወሕፃናት። | በዚህም ምክንያት ታላቁም ታናሹም ወንዱም ሴቱም ሕዝቡም አሕዛቡም በፍጹም ደስ ተሰኙ። |
| ወገብሩ በዓለ ዓቢየ በይእቲ ዕለት አመ ፲ ለመስከረም ንጉሥ ወሠራዊቱ ወሕዝቡ። | መስቀሉን በተቀበሉበት መስከረም ፲ ቀን ዓፄ ዳዊት ከሠራዊቶቻቸው ጋር ፈጽመው ደስ ተሰኙ በዓሉንም አከበሩ። |



| | |
|---|---|
| እንዘ ያሌዕሉ ቃላቲሆሙ። | ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አሰምተው እየጮሁ |
| ወይጠፍሑ በእደዊሆሙ። | በእጃቸው እያጨበጨቡ በዕልልታ። |
| ወያጽሕሱ በእገሪሆሙ። | በእግራቸው እየረገጡ በሆታ ካህናቱ በዝማሬ መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽንዕነ እያሉ ከፍ ባለ ደስታ በዓሉን አከበሩ። |
| ወገብረ ንጉሥ ምሳሐ ዓቢየ ዘአልቦ ትልቈ | ዓፄ ዳዊትም ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ሥፍር ቍጥር የሌለው ግብዣ አድርገው። |
| ወእስከ ይእዜ ያብዕልዎ ነገሥታተ ኢትዮጵያ ለዝንቱ በዓል። | ይህንም ልማድ ምክንያት አድርገው እስከ አሁን ድረስ የኢትዮጵያ ነገሥታት በዓሉን ያከብሩታል። |

ወሰመይዎ በዓለ ዓፄ መስቀል በከመ ተጽሕፈ በመጽሐፈ ስንክሳር:: [1]

በስንክሣር እንደ ተጻፈ ስሙንም የዓፄ መስቀል በዓል ብለው ሰየሙት::

ወእምዝ ኀደገ ሎሙ ፈለገ ዓባይ ዘውእቱ ግዮን ይሑር በቀዳሚ ሥርዓቱ ወይስተዩ ሰብአ ግብፅ እምኔሁ::

ይህን የፈለጉትን መስቀሉንና ሥዕላቱን ከተቀበሉ በኋላ እንደ ጥንቱ እንዲጠቀሙበትና እንዲጠጡ ግድቡን አስነሥተው የዓባይን ወሀ በጥንተ ልማዱ ይሄድላቸው ዘንድ ለቀቁላቸው::

---

[1] የሥንክሳርን ዓርኬውን ተመልከት:: ሐተታ ዓፄ ዳዊት ወደ ግብፅ ሲዘምቱ ከበረኃ ሲደርሱ አንድ ባሕታዊ እሱ ለብቻው አጽፉ፣ መጽሐፉና መቋሚያው ለብቻ ወድቀው አገኙ ይህ ምንድን ነው ብለው ቢጠይቁ እነዚህማ የሀገራችን ምእመናን ናቸው ጌታ ከተሰቀለበት ኢየሩሳሌም ሄደን እጅ እንነሣለን ከበረከተ መስቀሉ እንካፈላለን ብለው ሲሄዱ ከበረኃ ሲደርሱ በችግር በወሀ ጥም እያለቁ ከበረኃ ወድቀው ይቀራሉ ብለው ነገሯቸው:: እሳቸውም ሰምተው ይህንማ የወደዱትን ሳላመጣላቸው መቼ እመለሳለሁ:: ብለው በፍጹም ቆራጥነት አምጥተውልናል:: ከዚያም አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ለሚነሡ ነገሥታት ሁሉ ኃይል ጽንዕ ሁኗቸው ኑሯልና እንዲህ አለ::



ወእምዝ ጠብለሎ በልብሰ መንግሥቱ ለመስቀለ እግዚእነ ወለሥዕላተ እግዝእትነ ወለሥዕለ ኵርዓተ ርእስ ወለታቦተ ሚካኤል::

ዓፄ ዳዊትም የጌታችንን መስቀል የእመቤታችንን እና የኵርዓተ ርዕሱን ሥዕል፣ የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት በክብር ተቀብለው በልብሰ መንግሥታቸው አጐናጽፈው አስቀመጡ::

ወአዘዘ ይስግዱ ሎሙ::

ሕዝቡም ያከብሯቸው ዘንድ አዘዙ::

ወይጸልዩ ኀቤሆሙ በመዓልት ወበሌሊት::

ካህናቱም በቀንና በሌሊት ይጸልዩባቸው ዘንድ::

ወያዕርጉ ዕጣነ ወመሥዋዕተ ኀቤሆሙ በኵሉ ጊዜ::

በየጊዜው መሥዋዕት ይሠውባቸው ዕጣን ያሰርጉባቸው ዘንድ አዘዙ::

ወእምዝ ፈቀደ ከመ ይትመየጥ ሀገረ መንግሥቱ ኢትዮጵያ::

ይህን ከሠሩ በኋላ ወደ ሀገረ መንግሥታቸው ኢትዮጵያ ይመለሱ ዘንድ አሰቡ ተነሡ::

ወአዘዘ ከመ ይፁርዎሙ ለእሉ ንዋያት ክቡራን ጳጳሳት ወቀሳውንት።

በተነሡም ጊዜ ጳጳሳቱን ቀሳውስቱን መስቀሉንና ሥዕላቱን ተሸክመው ይነሡ ዘንድ አዘዙ ።

ወእንዘ የሐውሩ በጽሑ ኀበ ባሕር

ይህን አስይዘው ሲመጡ ከባሕር ደረሱ።

ወገብረ ሎሙ ተአምረ ቅዱስ ሚካኤል በባሕር።

ከባሕሩ ሲደርሱ ሞገድ ተነሣባቸው ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ ሞገዱን ጸጥ አርጐ አሻግሮአቸዋል።

ወበየብስኒ።

በጉዳናቸውም እባብና ዘንዶ የበዛበት ነበርና በተአምራት እያጠፋላቸው መጥተዋል።

እስመ ተወከፉ ታቦቶ ወነሥእዎ ምስለ መስቀሉ ክቡር።

በስሙ የተቀረጸውን ጽላት ክቡር ከሚሆን ከመስቀሉ ጋር ተቀብለው አስይዘው ይጓዙ ነበርና



ውእቱኒ ንጉሥ ወሠራዊቱ ወሕዝቡ ገብሩ ሎቱ በዓለ ዓቢየ አመ ፲ወ፪ ለመስከረም በእንተ ዘአድኃኖሙ በከመ ተጽሕፈ በመጽሐፈ ስንክሣር።[2]

ይህንንም ተአምራት ስለአደረገላቸው በስንክሣር እንደተጻፈ ንጉሡ ሕዝቡ ሠራዊቱም መኳንንቱም አንድ ሆነው መስከረም ፲፪ ቀን የቅዱስ ሚካኤልን በዓሉን አከበሩ።

ወበዓለ መስቀልኒ አመ ፲ወ፯ ለመስከረም ገብረ በዓለ ዓቢየ ፈድፋደ እምዘገብረ ቀዳሚ እስከ ፯ ዕለት።

የመስቀሉንም በዓል ቀደም ሲል መስከረም ፲፯ ቀን እስዋን ሁነው ከአከበሩት በዓል የበለጠ አድርገው እስከ ፯ ቀን ድረስ በዝማሬ አከበሩ።

---

[2] ስለዚህም ነገር ሲቀ ቅዱስ ያሬድ የቅዱስ ሚካኤል ታቦት ከመስቀሉ ጋር ከዚህ ቦታ መጥቶ እንዲቀመጥ ትንቢት ተገልጾለት አስቀድሞ ኀበ ደብር ቅዱስ ነሐውር ኀበ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ህየ ንስግድ ኵልነ ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ ብሎ ተናግሮ ነበርና ይህን ለመፈጸም ሲሉ እስመ ስሙ ይመርሆ ኀበ ግብሩ እንዲል አባታችን አቡነ ሚካኤል በስሙ ስለ ተጠሩ በስሙ ስለከበሩ የስማቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ይህን ታቦት በስተምዕራብ በኩል ቤተ ክርስቲያን አሠርተው አስቀምጠውታል ተአምራቱም እስከ አሁን ድረስ ሳይቋረጥ አለና እንዲህ አለ።

| | |
|---|---|
| ወእምዝ ርእየ በሕልሙ ዘይብል "ይነብር መስቀልየ በዲበ መስቀል"፡፡ | ከዚህ በኋላ "መስቀሌ በመስቀል ላይ ይቀመጣል" የሚል ሕልምን አዩ፡፡ |
| ወኮኖ ዕፁብ ዝንቱ ራዕይ፡፡ | መስቀሉን ይዠለሁ በመስቀል ላይ ይቀመጣል ያለኝ ራዕይ ምን ይሆን ብለው ያደንቁ ጀመር፡፡ |
| ወሶበ በጽሐ ሀገረ ስናር ለበጺሐ ሀገረ መንግሥቱ አዕረፈ በክብር ዓቢይ መፍቀሬ እግዚአብሔር ዳግማዊ ዳዊት፡፡ | ወደ ሀገረ መንግሥታቸው ለመግባት ጥቂት ሲቀራቸው ስናር ሲደርሱ እግዚአብሔር የሚወዱ ዳግማዊ ዳዊት በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ |
| እምድኅረ ዋከየት ሀገረ ኢትዮጵያ በብርሃነ ሃይማኖቱ፡፡ | ኢትዮጵያ በሳቸው የሃይማኖት ብርሃን ማለት በክብረ በመስቀሉ ብርሃን ከከበረች በኋላ፡፡ |
| ወእምድኅረ ዓቀመ | ለልጆቻቸው የመንግሥትን |



| | |
|---|---|
| ሥርዓታተ መንግሥት ለወሉዱ አመ ፱ ለጥቅምት፡፡ | ወግና ሥርዓት ጽፈው ከአዘጋጁ በኋላ መስቀሉን ተቀብለው ጥቅምት ፱ ቀን ከዚህ ዓለም በክብር አረፉ፡፡ |
| ወወረሰ መንግሥተ ሰማያት፡፡ | ለዘለዓለሙ የማታልፍ የመንግሥተ ሰማያዊት ክብርን አገኙ፡፡ |
| ወመዋዕለ መንግሥቱ ፵ ዓመት ወ፮ አውራህ ወ፱ ዕለት፡፡ | ዘመነ መንግሥታቸውም ይህን ዓለም እንደሰም አቅልጠው እንደገል ቀጥቅጠው የገዙበት ፵ ዓመትና ፮ ወር ከዘጠኝ ቀን ነው፡፡ |
| ወበመዋዕሊሁ ነበሩ አሉ ከዋክብት ብሩሃን፡፡ | በዘመነ መንግሥታቸውም ይህችን ዓለም በጸሎታቸው ጠብቀው በብርሃነ ሃይማኖታቸው ከጨለማ ወደ ብርሃን አውጥተዋት የነበሩ ቅዱሳን ነበሩ፡፡ |

| | |
|---|---|
| አቡነ ፊቅጦር ጳጳስ ዘተሰምየ ካልዕ ሰላማ። | እነዚህም ሁለተኛ ሰላማ እየተባሉ ሲጠሩ የነበሩ አቡነ ፊቅጦር። |
| ወአቡነ ሳሙኤል ዘወገግ። ወአቡነ ሳሙኤል ዘገዳመ ዋልድባ። | የወገጉ አቡነ ሳሙኤል። የዋልድባው ገዳም አቡነ ሳሙኤል። |
| ወአባ ጊዮርጊስ ዘገዳመ ማኅው ወሀገረ ሽግላ | በሽግላ ምትባል አገር ውስጥ የምትገኝ የማኅው ገዳም አባ ጊዮርጊስ ነበሩ። |
| ወተራከቡ እሉ በፈቃደ እግዚአብሔር ወገነዝዎ በክብር። | እነዚህም ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ካያሉበት ተገናኝተው ገንዘው ቀበሩቸው። |
| ወተቀብረ በደሴተ ዳጋ። | ዳጋ ከሚባለው ደሴት ተቀበሩ። |
| ወእሉሰ ንዋያት ተርፉ ውስተ ዕደ ተንባላት። | ዓፄ ዳዊት ከሞቱ በኋላ ቀደም ብለን የቆጠርናቸው |



| | |
|---|---|
| እስከ አመ ንግሠ ወልዱ ዘርዓ ያዕቆብ ርቱዓ ሃይማኖት። | መስቀሉና ሥዕላቱ። ልጃቸው ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ እስኪነግሡ ድረስ በእሕዛብ ሀገር ተቀምጦ ኖረ። |
| ወእምድኅረዝ ነግሡ ውሉዱ በበጊዜሁ። | ከዚህ በኋላ ልጆቻቸው በየጊዜው ነግሠዋል |

## ምዕራፍ ፫

## ምዕራፍ ፫

ወእምዝ ንጽሕፍ ዜናሁ ለዘርዓ ያዕቆብ ንጉሥ ርቱዓ ሃይማኖት ወልዱ ለዳግማዊ ዳዊት።

ሃይማኖታቸው የቀና የዳግማዊ ዳዊት ልጅ ዓጼ ዘርዓ ያዕቆብ የሠሩትን ሥራ እንናገራለን።

ዘከመ ነግሠ ወዘከመ አምጽአ መስቀለ ክርስቶስ ክቡረ።

እንደ ነገሡና ክቡር የሚሆን የጌታችንን መስቀልም እንዳመጡ፣

ወሰፍነገ፣

ሰፍነጉን፣

ወከለሜዳ፣

ከለሜዳውን

ወሀብለ ማዕሠረ ዕደዊሁ ወአክሊለ ሦክ

የግርንግሪት የታሠረበት ገመዱን። አክሊለ ሦኩን

ወዘተቀሥፈ ቦቱ ውስተ ሀገረ ኢትዮጵያ።

የተገረፈበት ጅራፉን ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ እንዳመጡና ያመጡበትን ምክንያት እንናገራለን።



ወአንበሮ ውስተ ደብረ ነገሥት እንተ ይእቲ ደብረ ከርቤ።[3]

ደብረ ከርቤ እየተባለች በምትጠራው በደብረ ነገሥት አስገብተው እንደ አስቀመጡት እንናገራለን።

በ፷፻ወ፱፻ ፳ወ፯ ዓመት እምፍጥረተ ዓለም።

ዓለም በተፈጠረ በስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት።

በ፲፻ወ፬፻ ፳ወ፯ ዓመት እምልደተ መድኃኒነ።

ጌታ በተወለደ በሺህ አራት መቶ ሃያ ሰባት ዓመት።

በ፲፻ ወ፩፻ ፳ወ፯ ዓመተ ሰማዕታት ነግሠ ዘርዓ ያዕቆብ ርቱዓ ሃይማኖት ወልደ ዳዊት ዳግማዊ።

በሺህ አንድ መቶ ሃያ ሰባት ዓመተ ሰማዕታት ሃይማኖታቸው የቀና የዳግማዊ ዳዊት ልጅ ዓጼ ዘርዓ ያዕቆብ ነገሡ።

---

[3] የዚህች ቦታ ስመ ተፋልሶ ፫ ጊዜ ነው ከዓጼ ካሌብ እስከ ዓጼ ይኩኖ አምላክ ደብረ ነጕድጓድ ከዓጼ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓጼ ዘርዓ ያዕቆብ ደብረ ነገሥት ከዓጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ መስቀሉ ስለተቀመጠበት ደብረ ከርቤ ተብላለች።

ወተቀብዓ ቅብዓ መንግሥት እምዘተርፈ እምይኩኖ አምላክ አበአቡሁ።

ከቅድመ አያታቸው ከዓፄ ይኩኖ አምላክ ከተረፈው የመንግሥት ቅብዓት ተቀብተው ነገሡ።

በከመ ነገሮ እግዚእነ ዘንተ ቀዳሚ ለአቡነ ተክለ ሃይማት።

ጌታ አስቀድሞ ትንቢቱን ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት እንደነገራቸው።

ወተሰምየ ስመ መንግሥቱ ቈስጠንጢኖስ።[4]

ስመ መንግሥታቸውም ቈስጠንጢኖስ ተባለ።

በመዋዕለ ሢመቱ ለአባ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ።

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አባ ዮሐንስ ተሾመውበት በነበረ ዘመን ተቀብተው ነገሡ።

ወእምእመ ነግሠ በ፬ ዓመት መጽኡ ፪ቱ ሊቃነ ጳጳሳት አበዊነ አባ ሚካኤል ወአባ ገብርኤል ።

በነገሡ በአራተኛው ዓመት አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳቱ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል[1]

ወአባ ዮሐንስ ኤጲስ ቆጶስ ዘደብረ ምጥማቅ

የደብረ ምጥማቁ ኤጲስ ቆጶስ አባ ዮሐንስ ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

ወ፪ሆሙ ኅቡራን ግዕዘ እሙንቱ።
ወድሙር ኵሉ ንዋዮሙ በከመ ሥርዓተ ሐዋርያት።

ሁለቱም ሃይማኖታቸው ግብራቸው አንድ ነውና። እንደ ሐዋርያት ሥርዓት ገንዘባቸውን በአንድ አድርገው ሲኖሩ ነበር

አባ ሚካኤል ይሁብ ክህነተ በምድረ አምሐራ ወአባ ገብርኤል ይሁብ ክህነተ በምድረ ሸዋ።

አባ ሚካኤል በምድረ አምሐራ አባ ገብርኤል በምድረ ሸዋ ክህነት ይሰጡ ነበር።

ውእቱስ መፍቀሬ እግዚአብሔር ዘርዓ ያዕቆብ

ስመ መንግሥታቸው ቈስጠንጢኖስ የተባለ

---

[4] ቈስጠንጢኖስ ኒቆስጥጥሉ በዘንቱ ትእምርት ትመውዕ ፀርከ የሚል ራዕይ በጽፍጽፍ ሰማይ ተጽፎ አይቷል እሳቸውም አንዝር መስቀልየ በዓብ መስቀል የሚል ራዕይን አይተዋልና። ቈስጠንጢኖስ ማለት ሐመልማል ትፍሥሕት ማለት ነው ሐመልማል ለዓይን ደስ ያሰኛል ጠል ሕይወት ይሰጣል እሳቸውም ለነፍስ ጠለ ምሕረትን የሚሰጥ መስቀሉን አምጥተውልናልና ትፍሥሕትም አለ ቈስጠንጢኖስ መክሰምያኖስን ድል ነሥቶ ሮም በገባ ጊዜ የሮም ምእመናን የመስቀሉን የጸሕሉን የጽዋውን የጽናውን ስብሪ ይዘው መስቀል መግረሬ ፀር መስቀል መዋዔ ፀር እያሉ ደስ ብሏቸው ተቀብለውታል። እሳቸውም የአሕዛብን ንጉሥ ድል አድርገው መስቀሉን ይዘው በመጡ ጊዜ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደስ ብሎት መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ እያሉ ተቀብለዋቸዋልና።

| | |
|---|---|
| ዘተሰምየ ቈስጠንጢኖስ ኮነ ፈድፋደ ያፈቅራ ለእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ ከመ አቡሁ ዳግማዊ ዳዊት። | የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆኑ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብም እንደ አባታቸው ዳግማዊ ዓፄ ዳዊት እመቤታችንን እጅግ ይወዷት ነበር። |
| ወአጽሐፈ ተአምራቲሃ ወመንክራቲሃ ብዙኃ እምኢየሩሳሌም ወግብፅ። | ከፍቅራቸውም ጽናት የተነሣ በኢየሩሳሌም እና በግብፅ ያደረገችውን ተአምራት አጽፈዋል። |
| ውእቱሂ ደረሰ ድርሳናተ ዘይትበሐል እግዚአብሔር ነግሠ። | እሳቸውም "እግዚአብሔር ነግሠ" የሚባል። |
| ወምዕላደ በእንተ ሃይማኖት ርትዕት። | ስለ ቀናች ሃይማኖት የሚናገር ምዕላድ። |
| ወበእንተ አክብሮ ሰንበታት ወበዓላት። | ስለ ሰንበታትና በዓላትም አከባበር ድርሳናትን ደርሰዋል። |



| | |
|---|---|
| ወለፀረ እግዝትነ ማርያም ሰደዶሙ እምሀገረ መንግሥቱ። | የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ክብር የሚቃወሙትንም ከሀገር አስወጥተዋቸው። |
| ወአጥፍአሙ በዘዘዚአሁ ኲነኔ። | ከነዚሁም በሚገባ ፍርድ የፈረዱባቸው አሉ። |
| ወእምዝ ይቤ ንጉሥነ ዘርዓ ያዕቆብ ዘተሰምየ ቈስጠንጢኖስ። | ከዚህም በኋላ ስመ መንግሥታቸው ቈስጠንጢኖስ የተባለ ንጉሣችን ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንዲህ አሉ። |
| እምአመ አንገሠኒ እግዚአብሔር በ፲ወ፭ ዓመት | እግዚአብሔር ባነገሠኝ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት። |
| ወእም አመ ተወለድኩ በ፶ ዓመት። | በተወለድኩ በሃምሣ ዓመት። |
| ራዕየ ርኢኩ ዘይብል "አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል"። | «መስቀሌን በመስቀል ላይ አስቀምጥ» የሚል ራዕይ አየሁ አሉ። |

ወእቤ ምንት ትእምርቱ ለዝንቱ ራዕይ እንዘ እብል ነበርኩ መጠነ ፩ ዓመት።

እኔም ይህ ሕልም ምን ይሆን እያልኩ አንድ ዓመት ያህል ይህን ሳወጣ ሳወርድ ኖርኩ።

በከመ ርእየ ቈስጠንጢኖስ ንጉሠ ቈስጥንጥንያ ራዕየ ዘይብል ኒቄስጣጣኑ።

የቈስጥንጥንያው ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ኒቄስጣጣኑ የሚል በጸፍጸፍ ሰማይ ተጽፎ እንደአየ።

ወኮኖ ዕፁበ ዝንቱ ራዕይ እስከ ፈከረ ሎቱ አውስግንዮስ ሕፅወ ጽዮሁ።

እሱም አውስግንዮስ የሚባል የአባቱ ጓደኛ እስኪተረጉምለት ድረስ ይህ ኒቄስጣጣኑ ብሎ የታየኝ ምን ይሆን እያለ ሲያደንቅ እንደ ኖረ።

እንዘ ይብል ዝንቱ ትእምርተ መስቀል ውእቱ

ኒቄስጣጣኑ የሚል ተጽፎ ማየትህ ይህ የመስቀል አምሳል ነው።

ወበዝ መስቀል ትመውዕ ፀሬከ ወጸላዕተከ

ይኸውም በዚህ መስቀል ጠላቶችን ድል ታደርጋለህ



ወትመውዕ ለመክስምያኖስ ዓላዊ።

ጠላትህ መክስምያኖስንም ድል ትነሣዋለህ ሲልህ ነው።

ወከማሁ ሊተኒ አስተርአየኒ።

እኔንም እንደእሱ አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል ብሎ አሳየኝ።

እስከ ተሰዕልኩ ምክንያተ ዝንቱ እምሐራን መጻሕፍት ወሊቃውንት ወእም መማክርተ መንግሥትየ ጠበብት።

ከተማሩት ከሊቃውንቱ ከምሑራኑ አዋቂዎች ከሆኑ ከመንግሥቴ አማካሪዎች ጠይቁ እስከምረዳ ድረስ አንድ ዓመት ኖርኩ።

ወእሙንቱኒ ይቤሉኒ እስመ መስቀለ ክርስቶስ አምኃሁ ለአቡከ ሀሉ በዕደ መኮንን ተንባላት ዘመካ መዲና።

እነሱም ይህማ ለአባትህ እጅ መንሻ ሆኖ የመጣው የጌታችን መስቀል በመካ መዲናው ሹም እጅ አለና ያን አምጣ ሲልህ ነው ብለው ነገሩኝ።

ወበእንተዝ ቀናዕኩ ቅንዓተ መንፈሳዊተ።

በዚህን ጊዜ መንፈሳዊ ቀንዓትን ቀናሁ።

| | |
|---|---|
| ወአስተጋባዕኩ ሠራዊትየ። | ምታ ነጋሪት ከተት ሠራዊት ብየ ሠራዊቴንም ሰበሰብኩ። |
| ወእምዝ ወረድኩ ምድረ አደሊዋ ከመ እግበር ጸብዓ ምስለ ጋፍሔር ሥዩመ ተንባላት ዘመካ መዲና።[5] | ከዚህም በኋላ ከመካ መዲናው የአሕዛብ ሹም ከጋፍሔር ጋር ለመዋጋት አደሊዋ ድረስ ዘመትኩ። |
| ወእንዘ ንጉሠ ምስር አሽሪፍ። | በዘመኑ የምስሩ ንጉሥ አሽሪፍ ሲሆን ጋፍሔር መካ መዲናን ይገዛ ያስተዳድር ነበር። |
| ውእቱኒ ይቤለኒ ኢትግበር ጸብዓ ምስሌየ። | እሱም ከእኔ ጋር ምን ያዋጋሃል አለኝ። |
| እስመ አነ እሁበከ ንዋየ አቡከ ዳዊት። | በእኔ እጅ የተያዘውንና ያለውን የአባትህን ገንዘብ። |

[5] የዓጼ ዘርዓ ያዕቆብ ሐተታ የሠራዊታቸው ብዛት ፊታውራሪው ሲዘራ የሄደ እንደሆነ ደጀኑ ቀረቀንዳው ሲወቃ ነበር የሚከተው።



| | |
|---|---|
| መስቀለ፣ | መስቀሉን፣ |
| ወሥዕላተ፣ | ሥዕላቱን እስጥሃለሁና ከእኔ ጋር አትዋጋ አለኝ። |
| ወዘንተ ብሂሎ ወሀበኒ አምኃየ። | ይህን ብሎ የዕጅ መንሻዬን |
| መስቀለ። | መስቀሉን። |
| ወሰፍነገ። | ሰፍነጉን። |
| ወከለሜዳ። | ከለሜዳውን። |
| ወሥዕላተ እግዝእትነ ማርያም። | ሉቃስ የሣላቸውን የእመቤታችንን ስዕሎች። |
| ወሥዕለ ኵርዓተ ርእስ። ወታቦተ ሚካኤል | ዮሐንስ ወንጌላዊ የሣለውን ኵርዓተ ርእሱን ሥዕልና የሚካኤልን ታቦት ሰጠኝ። |
| ወይቤለኒ ጋፍሔር ሥዩመ መካ መዲና። | የመካ መዲናው ሹም ጋፍሔር እንዲህ አለኝ። |

| | |
|---|---|
| ዘንተ አምኃከ ተወኪፈከ ሑር ብሔረከ በዳህና ወበሰላም። | ይህን የዕጅ መንሻ ተቀብለህ ወደ ሀገርህ በፍቅር ተመለሰስ አለኝ ። |
| ወእምዝ ተመይጥየ ተዘከርክዎ ለራዕይ ዘይብል አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል።[6] | ከዚያም ከተመለስኩ በኋላ መስቀሌን በመስቀል ላይ አስቀምጥ ብሉ ያሳየኝ ሕልም ይህ ነውን ብየ አሰብኩ። |
| ወነበርኩ ፫ ዓመተ እንዘ አዓይል ኩሉ አድባራተ ኢትዮጵያ በሐዘን ወበፈሪሃ እግዚአብሔር፡፡ | መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ አኑር ያለኝን ለመፈጸም መስቀለኛውን ቦታ በየት አገኘዋለሁ ብየ ፫ ዓመት የኢትዮጵያን ተራሮች ዞርኩ። |
| ወእብል በአይቴ አኀብሮ ለዝንቱ መስቀል ክቡር። | ይህን ክቡር መስቀል በየት አኖረዋለሁ እያልኩ። |

[6] ይህን የዕጅ መንሻ አድርጎ የሰጠኝን መስቀሉንና ሥዕሉን የተቀበልኩት መስከረም ሃያ አንድ ቀን ሽህ አራት መቶ ዐርባ ሦስት ዓመተ ምሕረት ነው



| | |
|---|---|
| ውብዙኃተ አብያተ ክርስቲያን ወጠንኩ ከመ እሕንጽ ወአንብሮ ለመስቀል ክቡር ውስቴቶን። | በየደረስኩበት ተራራ ላይ ይህን ክቡር የሆነ የጌታዬን መስቀል በውስጣቸው ለማስቀመጥ ብዙ ቤተ ክርስቲያን ማነጽ ጀመርኩ። |
| ወባሕቱ ይቤለኒ መልአክ ዘይተልወኒ ለለኩሉ መካን ኢይደሉ ዝንቱ መካን ለዝንቱ መስቀል ክቡር ከመ ይንበር ውስቴቱ። | ነገር ግን በየሄድኩበት የሚመራኝና የሚከተለኝ መልአክ (ቅዱስ ዑራኤል) ይህ ቦታ ለዚህ ክቡር መስቀል መቀመጫ ይሆን ዘንድ አልተፈቀደም አለኝ። |
| ወእምድኅረ ፫ ዓመት በጻሕኩ ምድረ አምባሰል በብዙሕ ፃሕቅ። | ከሦስት ዓመት በኋላ አምባሰል ከሚሠኘው ቦታ ደረስኩ። |
| ወርኢኩ ደብረ ዘአምባሳል መስቀል። | ቦታዋም በመስቀል አምሳል የተቀረፀች ተራራ ናት። |
| ወዖድክዋ ኩለንታሃ ፫ ጊዜ በታሕቴሃ። | እኔም ታቿን ዙሪዋን ሦስት ጊዜ ዞርኳት። |

| | |
|---|---|
| ወረከብክዋ ከመ ትእምርተ መስቀል ይእቲ። | በትእምርተ መስቀል አምሳል ተቀርጻ በፈቃደ እግዚአብሔር ታንጻ አገኘኋት። |
| ወእቤ ዝንቱ መካን ዘይቤለኒ አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል። | እኔም መስቀሌን በመስቀል ላይ አስቀምጥ ያለኝ ይህ ቦታ ነውን አልኩ። |
| ዘንተኒ ዜነውክዎሙ ለጳጳሳት እለ ሀለው ምስሌየ። | ይህንኑም አብረውኝ ላሉት ለጳጳሳቱ ለነ አባ ሚካኤል፣ |
| ወለካህናት። | ለሊቃውንቱ ካህናት፣ |
| ወለመኳንንት። | ለመኳንንቱ ነገርኳቸው አማከርኳቸው። |
| ወእሉኒ ይቤሉኒ በአማን ይደሉ ዝንቱ መካን ለዝንቱ መስቀል ክቡር። ከመ ይንበር ውስቴቱ። | ጳጳሳቱም መኳንንቱም አይተው በእውነት ለዚህ ክቡር መስቀል መቀመጫ የተገባ ቦታ ነው አሉኝ። |
| ወእምዝ ስዕነ በዊአታ ለአንቀጽ። | ከዚህም በኋላ ገደል ከመሆኑ የተነሣ ወደ አምባው ለመግባት አቃተን። |
| እስመ ኢኮነ ርቱዓ ፍኖተ ሙባሁ። | ብዙ የነገሥታት ሀብት ስለነበረበት ማንም ገብቶ እንዳይዘርፈው በማለት የመግቢያው በር ጭንቀኛ በመሆኑ ንጉሥ ሊገባበት በትንሽ ጊዜ አይችልምና። |
| ወበእንተዝ ኃደርነ ታሕቴሃ መንገለ ምሥራቅ። | ስለዚህም ከእግረ ደብሩ በምሥራቅ በኩል ካለው ሜዳ ሠፍረን አደርን። |
| ወበሌሊት አስተርአየኒ መልአክ ዘይዜንወኒ። | ከዚህ በኋላ የሚመራኝና የሚከተለኝ መልአክ (ቅዱስ ዑራኤል) ሌሊት በራዕይ ተገለጸልኝ። |
| ወይቤለኒ። | ተገልጾም እንዲህ አለኝ። |

| | |
|---|---|
| ዛቲ ይእቲ ደብር ዓባይ ዘትሰመይ ደብረ ነጐድጓድ። | ቀደም ሲል ደብረ ነጐድጓድ ጊላም ደብረ ነገሥት እየተባለች የምትጠራው ታላቋ ቦታ ይህች ናት። |
| ወእምይእዜሰ ትሰመይ ደብረ ከርቤ | ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት ግን ደብረ ከርቤ ትባላለች ። |
| ወይእቲ ሀገረ መንግሥት ወክህነት።[7] | ደብረ ነጐድጓድ የተባለችው የካህናትና የነገሥታት መኖሪያ ስለሆነች ነው። |
| ኢየዐርግ ኅቤሃ አዕጋረ ዕቡያን። | የትዕቢተኞች የመናፍቃን እግር አይረግጣትም። |
| ወአማጽያን። | ከሀዲያን ማለት አንድነቱን ሦስትነቱን የሚክዱ ሊኖሩባት አይችሉም። |
| ትሄይስ ወትከብር እምኵሎን አድባራት። | ከአድባራት ሁሉ ከፍ ያለች የከበረች ናት ። |

[7] ያዕቆብና ዮሐንስ ከቤተ መንግሥት ከቤተ ክህነት በመወለዳቸው ደቂቀ ነጐድጓድ እየተባሉ ሲጠሩ እንደ ነበረ።



| | |
|---|---|
| ወይእቲ ደብረ ከርቤ ደብረ መቅደሱ ለእግዚአብሔር አብ። | ይህችውም ደብረ ከርቤ ለእግዚአብሔር አብ እንደ ጽርሐ አርያም የሚሠለስባት የሚቀደስባት ቦታ ናት። |
| ወማኅደራ ለቅድስት ድንግል ማርያም። | ለእመቤታችንም እመ አምላክ እየተባለች የምትመሰገንባት ቦታ ናት። |
| ኢይሴሰል እምኔሃ መንፈስ ቅዱስ ኵሉ ጊዜ ለሐውፆታ። | የተጸለየውን ጸሎት የተሠዋውን መሥዋዕት በነጋ በነጋ በየጊዜው ለመቀበል መንፈስ ቅዱስ ከሷ አይለይምና፡፤ |
| ወዕርግ ሀየ አንቀጸ እንተ ምሥራቂሃ | ይህን ብሎ ከነገረኝ በኋላ በምሥራቅ በኩል ባለው በር ግባ አለኝ። |
| ወበሀየ ትረክብ ፪ተ አብያተ ክርስቲያን ንዑሳተ። | ከገባህም በኋላ ትንንሽ ሁለት አብያተ ክርስቲያን ተሠርተው ታገኛለህ። |

አሐቲ በስመ እግዚአብሔር አብ፡

ከሁለቱም አንዲቱ በእግዚአብሔር አብ ስም የተሠራች ናት።

ወአሐቲ በስማ ለቅድስት ማርያም፡

አንዲቱም በእመቤታችን ቅድስት ማርያም ስም የታነጸች ናት።

ወእሉሂ ዘአምጽኦሙ ፈቃደ ክርስቶስ ባሕታዊ እምሀገረ ናግራን በ፳፻ወበ፲ወ፬ ዓመት እምልደተ መድኃኒነ በመዋዕለ ካሌብ ንጉሠ ኢትዮጵያ።

እነዚህም በሁለቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ታቦቶች በአምስት መቶ ዐሥራ አራት ዓመተ ምሕረት በዓፄ ካሌብ ዘመን ፈቃደ ክርስቶስ የሚባል ባሕታዊ ከሀገረ ናግራን ያመጣቸው ናቸው።

ወምክንያተ ምጽአቶሙሰ ለታቦተ እግዚአብሔር አብ ወታቦተ ማርያም ድንግል።

የእግዚአብሔር አብና የእመቤታችን ድንግል ማርያም ታቦቶችም የመጡበት ምክንያት ግን፡



እንዘ ሀሎ ፈቃደ ክርስቶስ ባሕታዊ ውስተ ሀገረ ናግራን።

ፈቃደ ክርስቶስ የሚባል ባሕታዊ ሀገረ ናግራን ተቀምጦ ሳለ።

ተተክለ ዓምደ ብርሃን ዓቢይ ዘሥዑል ውስቴቱ ሥዕለ እግዝእትነ ማርያም ውስተ ይእቲ ሀገር።

ከዚህች ቦታ ላይ በመካከሉ የእመቤታችን ማርያም ሥዕል የተቀረጸበት ዓምደ ብርሃን ተተከሉ።

ወቀፀቦ እንዘ ያበርህ ከመ ፀሐይ። ወዕንዘ ያስምዕ ድምፀ ከመ ነጕድጓድ[7]

እንደ ፀሐይ እያበራ እንደነጐድጓድ ድምፅ እያሰማ ሲጠቅሰው በጸጋ ያይ ነበር፣ ይህችም ቦታ የቀራንዮ አምሳል እንደ መሆኗ እንደ ክረምት ነጐድጓድ ድምፅ እያሰማ ይጠቅሰው ነበር፣

ወበዕለተ አስተርአዮ ዝንቱ ዓምደ ብርሃን አስተርአየቶ እግዝእትነ ማርያም።

የብርሃን ዓምዱ በተገለጸለት ቀን እመቤታችን ድንግል ማርያም ተገልጻ ታየችው።

ወትቤሎ።

እንዲህ አለችው።

| | |
|---|---|
| ተንሥእ ወንሣእ ታቦተ እግዚአብሔር አብ ወታቦተ ዚአየ። | የእኔና የእግዚአብሔር አብን ታቦት ይዘህ ተነሥ። |
| ወሑር ኀበ አስተርአየከ ዓምደ ብርሃን | ተነሥተህም ይህ የብርሃን ዓምድ ተተክሎ ከጠቀስህ ቦታ ፈጥነህ ሂድ። |
| ወሀሎ ሀየ እስከ ይከውን ፈቃዱ ለእግዚአብሔር፡፡ | የእግዚአብሔር ፈቃዱ እስኪሆን ከዚያው ተቀመጥ አለችው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እስኪሆን አለች ታቦቶቹ በክብር የሚገለጹት በመስቀሉ ምክንያት ነውና። |
| እስመ ዛቲ ሀገር ዓባይ ይእቲ። | ይህችም ቦታ ከአድባራቱ ሁሉ ተለይታ የከበረች ናትና። |
| ወወሀበኒ ወልድየ ሶበ ሖርኩ ኢትዮጵያ ጊዜ ስደትየ ትኩነኒ ርስተ ለትውልደ ትውልድ። | በርግም ሄሮድስ ዘመን ተሰድጄ ኢትዮጵያ በሄድኩበት ጊዜ ለልጅ ልጅ መታሰቢያ ርስት ትሁንሽ ብሎ |



| | |
|---|---|
| ወይሰባሕ ስምየ ውስቴታ እስከ ለዓለም። | ስሜም እስከ ዕለተ ምጽአት ያለማቋረጥ ሲመሰገን ይኖርባት ዘንድ ሰጥቶኛልና ሂደህ ተቀመጥ አለችው። |
| ወባረካ በበረከተ መንፈስ ቅዱስ። | አንድነቱ ሦስትነቱ ሲነገርባት እንዲኖር በመንፈስ ቅዱስ ባረካት አከበራት። |
| ወአልዓለ ክብራ እምክብረ ኩሉን አድባራት። | ስሟም ከአድባራቱ ሁሉ በላይ ሆኖ በክብር እንዲታወቅ አደረጋት። |
| ወእምድኅረ ዜነወቶ ዘንተ ተሠወረት እምኔሁ | ይህን ቃል ተናግራ ካስረዳቸው በኋላ ከርሱ ተሠወረችው። |
| ወበእንተዝ መጽአ በፈቃዱ ለካሌብ ንጉሥ እንዘ ይመርሖ መልአከ እግዚአብሔር ቅዱስ ዑራኤል። | በዚህ ምክንያት በዓፄ ካሌብ ፈቃድ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ዑራኤል እየመራው ታቦቶቹን ይዞ መጣ። |

| | |
|---|---|
| ወምስሌሁ ፲ወ፪ መነኮሳት፡፡ | ከሱ ጋር ዐሥራ ሁለት መነኮሳት አስከትሎ ነበር፡፡ |
| ወቦአ ኀበ ዛቲ ደብር፡፡ | ከዚህች ቦታ ገባ፡፡ |
| ወነበረ ውስቴታ ብዙኃ መዋዕለ፡፡ | እመቤታችን እንዳዘዘችው ታቦቶቹን አክበሮ ቤተ ክርስቲያን ተክሎ ብዙ ዘመን ኖረ፡፡ |
| ወአዕረፈ በሰላም፡፡ | ከዚህም በኋላ በክብር ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡ |
| ወትረክብ አዕፅምቲሁ መትሕተ ቤተ ክርስቲያን ዘእግዚአብሔር አብ | አፅሙንም ዝቅ ብለህ ከእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ሥር ተቀብሮ ታገኘዋለህ፡፡ |
| ወበገቦ ይኤቲ ቤተ ክርስቲያን ህሎ ዓቢይ ነቅዕ፡፡ | በዚህችው ቤተ ክርስቲያን ጉን በስተምሥራቅ እ ትልቅ ምንጭ ውሀ ታገኛለህ፡፡ |



| | |
|---|---|
| ወአምጽአ መሬተ እም መቃብሪሁ ለወልደ እግዚአብሔር ወግበር ቦቱ፡፡ | ጌታ ከተሰቀለበት ከቀራንዮ ከተቀበረበት ከጎልጎታ አፈር አምጥተህ እርጭበት አፍስበት፡፡ |
| ወይከውን ለከ ምድረ ሐዲስ ከመ መካነ ቤታ ለጽዮን | አብርሃ ወአጽብሃ የአክሱም ጽዮንን ቤተ መቅድስ በሚያንፁበት ጊዜ መሬቱ የላላ እና ረግረግ ስለነበረ ጌታ ከገነት አረር አምጥቶ ረጭቶላቸው ደረቅና የለሰለሠ መሬት ሆኖላቸው እንደአነፁ ለእናንተም ደረቅና የለሰለሠ መሬት ይሆንልሀል አላቸው፡፡ |
| ወቅብሮ ለመስቀል ክቡር ላዕለ ውእቱ ነቅዕ በከመ ይደሉ ለልዕልናሁ ከመ ኢይማስን ዓለም ዘእንበለ ጊዜሁ በኀጢአተ ውሉድ ደኀራውያን | መስቀሉ በአፍአ ከተቀመጠ ዘንድ በኋላ በሚነሱ ትውልድ ክፋት እና ኀጢአት ይህ ዓለም ያለጊዜው እንዳይጠፋ ለእሱ ክብር እንደሚገባ አድርገህ ነቅው ካለበት ቦታ ላይ ሠውረህ አስቀምጠው |

ወሕንፀ ዲቤሁ ቤተ ክርስቲያን ሠናይተ በከመ አዘዘከ መንፈስ ቅዱስ

በላዩም ላይ መንፈስ ቅዱስ እደገለፀልህ መጠን ያማረ የተወደደ አድርገህ በእግዚአብሔር አብ ስም ቤተ ክርስቲያንን ሥራ

ወዘንተ ተናገሮ አንቅሃኒ እምንዋምየ ወተንሣእኩ ሶቤሃ በፍስሐ ዓቢይ።

ይህን ካስረዳኝ በኋላ መልአኩ ከእንቅልፌ ቀሰቀሰኝ እኔም በፍፁም ደስታ ደስ ተሰኝቼ ተነሣሁ

ወበጽባሀ አረጉ እንተ ምሥራቂሃ አመ ፳ወ፮ ለመስከረም በበአለ እግዝእትነ ማርያም ምስለ መስቀሉ ክቡር በ፲፻ወ በ፬፻ ፵ወ፮ ዓመተ ሥጋዌ

እኔም በነጋ ጊዜ ክቡር የሆነ የጌታዬን መስቀል ይዤ በአንድ ሽ አራት መቶ አርባ ስድስት ዓመተ ምህረት መስከረም ፳፮ ቀን የእመቤታችን በአል በሚከበርበት ዕለት በምሥራቅ በኩል ወደተራራው ገባሁ።

ወሐወጽክዋ ኩሎንታሃ ለዛቲ ደብር በትሕትና ዓቢይ

ገብቸም ፍፁም በሆነ ትህትና ቦታዋን እየተዘዋወርኩ ሁለንተናዋን አየኋት



ወረከብክዋ በከመ ዜነወኒ መልአክ

አይቸም መልአኩ እንደነገረኝ ፍፁም ትእምርተ መስቀል ሆና አገኘኋት

ወለታቦታትኒ ዘከመ አምፅኦን ፈቃደ ክርስቶስ ባህታዊ ወተከሉን ውስቴታ

ታቦቶቹንም ፈቃደ ክርስቶስ የተከላቸው መሆኑን መልአኩ እንደ ነገረኝ ሆነው አገኘኋቸው

ወተፈሣሕኩ አነኒ ወኵሎሙ እለምስሌየ

ጌታዬ አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል ብሎ ያዘዘኝ ሦስት ዓመት ሙሉ የዞርኩበት ምኞቴ ስለተፈፀመልኝ እኔም ሆነ ከእኔ ጋራ ያሉት ፈፅሞ ደስ ተሰኘን

ወገበርነ በአለ ዐቢየ በዛቲ ዕለተ በእንተ ተፍጻሜተ ፍስሐየ

የጌታዬ ትእዛዝና ፈቃድ ስለተፈፀመልኝ ወንዱ በሆታ ሴቱ በዕልልታ ሆነን ታላቅ በአልን ከእመቤታችን በአል ጋራ በፍፁም ደስታ አከበርን።

ወአንበርነ ውስተ ይእቲ ቤተ ክርስቲያን መስቀሎ ለወልደ እግዚአብሔር ዘተረክበ በትጋሁ ወበ ጥበአቱ ለአቡየ ዳግማዊ ዳዊት

በአባቴ ዳግማዊ ዳዊት ፍፁምትጋትእናቆራጥነት የተገኘ የጌታዬን የወልደ እግዚአብሔር መስቀልንም በእግዚአብሔር አብ ስም በተሠራው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቀመጥን።

ወእምድኅረዝ አምጻእኩ መሬተ እም መቃብሪሁ ለወልደ እግዚአብሔር ወእምኩሎን መካናት ቅድሳት በ፹ወ፰ አግማል ወበ፻ በቅላት

ከዚህ በኋላ መልእኩ እንዳዘዘኝ ከቀራንዮና ከጎልጎታ፣ በኪደተ እግሩ ካከበራቸው ቅዱሳት መካናት በሰማኒያ ስምንት ግመሎችና በመቶ አጋሰስ አፈሩን አስመጣሁ

በከመ አምጽአ አቡየ ዳግማዊ ዳዊት ቀዳሚ መሬተ እምኩሎን መካናት ቅዱሳት በ፲፻ወ፩፻ አግማል

አባቴ አፄ ዳዊት ከቅዱሳት መካናት በአንድ ሺ ስምንት መቶ ግመሎች አፈሩን አስመጥተው እንደነበር እሳቸውም የመልእኩን ትእዛዝና ቃል ለመፈፀምና የጌታቸውም በረከት እንዳ ይቀርብኝ ሲሉ እንዳመጡ።



ወአግበርኩ ውስቴቱ ለነቅዐ እምዝንቱ መሬት በከመ አዘዘኒ መልአክ

መልአኩ እርጭበት ብሎ እንዳዘዘኝ ከአመጣሁት አፈር ከምንጩ ላይ ረጨሁት

ወነጽፈ ውእቱ ነቅዐ ወኮነ ምድረ ይቡሰ

አፈሩን በረጨሁበት ጊዜ ምንጩ ደርቆ ደረቅ መሬት ሆነ

ወእምዝ አክረይኩ ግበ ላዕለ ውእቱ ምድር ፵ በእመተ ብእሲ ኑኆ ወግድሞ

ከዚሁ ነቅዑ ከነበረበት ቦታ ላይም በሰው ክንድ ቁመቱም ወርዱም ልክ በልክ አርባ በአርባ የሆነ ጉድጓድ አስቆፈርኩ

ወወደይኩ መሬተ ዘአምጻእኩ ውስቴቱ

ከአመጣሁት አፈርም ከውስጡ አስገብቸ አስደለደልኩ

ወሐነጽክዎ ለግብ ኑኆ ወግድሞ በሠናይ ሕንፃ

የጉድጓዱን ውስጥም ዙሪያውን ጽኑዕ በሆነና በአማረ ግንብ አስገነባሁ

ወሐነፅኩ ቤተ ክርስቲያን ንዕስተ ማዕከለ ውእቱ ግብ በዘይሴኒ ግብር በወርቅ ወበዕንቍ

በጉድጓዱ ውስጥ ለክቡር መስቀሉ፣ ከለሜዳው እና ለአጽመ ቅዱሳን ማረፊያ መቀመጫ ትሆን ዘንድ በአማረ በተወደደ በወርቅ በዕንቍ አስጊጬ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን አሠራሁ

ወአግበርኩ ሣፁነ ዘመንክር ግብርቱ ዘዕንቍ ወወደይናሁ ለመስቀል ክቡር ዘምስለ ሙዳዩ ዘቦቱ ፬ቱሰ ናሥል።

በመስቀሉ መጠን አሠራሩ ድንቅ የሆነ ሣጥን በዕንቍ አሠርቼ መስቀሉን ሲልኩልኝ በአራት ማዕዘን የሚያዝበት አራት ሰንሠለት የያዘው ሙዳይ ነበርና መስቀሉን ከነሙዳዩ ከዚሁ ሣጥን ውስጥ አስቀመጥኩ

ወበእሉ ሰናሥል ረሰይኖ ለመስቀል ውስተ ውእቱ ሣፁን ርቡበ

አቀማመጡንም በወርቅ ሰንሠለት በታች በላይ በቀኝ በግራ እንደክሣማ አስይዥ ረቦ እንዲኖር አደረገኩ

ወለዝንቱ ሣፁን በሣፁን ዘወርቅ

መስቀሉንም ከነሣጥኑ በሁለተኛ የወርቅ ሣጥን ውስጥ አስቀመጥኩ

ለሠፍነግሂ ወለከለሜዳ ወለሀብል ዘተቀሰፈ ቦቱ ወለአክሊለ ሶከሂ ውስተ ዝ ሣፁን

ስለክብራቸው እያንዳንዳቸውን በወርቅ ሙዳይ አድርገው ልከውልን ነበርና ከለሜዳውን ሰፍነጉን አክሊለ ሶኩን የተገረፈበት ጅራፉን የግርግሪት የታሰረበት ገመዱንም ከነሙዳየ በዚሁ ሣጥን ውስጥ አስቀመጥኩ

ምስለ ወርቅ አምኀሁ ለእግዚእነ እስመ ፈነው ለነ ከመ ይኩነነ ለበረከት

ለበረከት ይሁናችሁ ብለው ለጌታችን እጅ መንሻ ከቀረበው ትንሽ ወርቅ ልከውልን ነበርና ከዚሁ ጋር አስቀመጥኩ

ወለዝንቱ ካዕበ በሣፁን ዘብሩር

ይህን የወርቅ ሣጥን ደግሞ በሦስተኛው በብር ሣጥን ውስጥ

| | |
|---|---|
| ወለዝ ካዕበ በሣፁን ዘብርት ወለዝ ካዕበ በሣፁን ዘዓረር | ይህንንም የብሩን ሣጥን ደግሞ በናስ ሣጥን የናሱን ሣጥን በእርሳስ ሣጥን |
| ወለዝ ካዕበ በሣፁን ዘዕፅ ዘሥርግው በወርቅ | የርሳሱን ሣጥን በወርቅ ባጌጠ በእንጨት ሣጥን |
| ለአዕፅምተ ሐዋርያት ወሰማዕት ወኵሎሙ ቅዱሳንን አንበርናሙ ውስተ ዝንቱ ሣፁን ዘዕፅ ዘቅፉል በወርቅ:: | ዓጽመ ሐዋርያትን ዓፅመ ሰማዕታትን ዓፅመ ቅዱሳን ዓፅመ ቅዱሳት አንስትን ሁሉ በወርቅ ከተለበጠው ከዕንጨቱ ሣጥን ውስጥ አስቀመጥናቸው:: |
| ወይጸውሮሙ ለኵሎሙ:: | አሁን የቈጠርናቸውን ሁሉ ሰብስቦ አንድ አድርጐ የሚይዛቸው እሱ ነውና:: |
| ወለእሉኒ ኵሎሙ በሣፁን ዘሐዒን:: | እኒህን ሁሉ ከዕንጨቱ ሣጥን ጋር በብረት ሣጥን አድርገን ለመስቀሉ |



| | |
|---|---|
| | መቀመጫ ብየ ባሳነጽኳት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቀመጥኩ:: |
| ወለግብራቲሆሙኒ ድኅረ ንትናገሮ በጠማር ደኃራይ:: | የሣጥኖቹን አሠራር ግን ወደፊት እንናገረዋለን:: |
| ወእምድኅረዝ አግበርኩ አዕማደ ዘሐዒን ከመ ይኩኑ ርቡዓነ ማዕከለ ቤተ ክርስቲያን ዘታሕቱ ወላዕሉ:: | ከዚህ በኋላ የብረት መረባርብ አሠርቼ በኖራ እያስለበጥኩ በብረት እየአስጠረኩ ምድር ቤትና ፎቅ እንዲሆን በግንቡ ላይ አሸጋግሬ አስቀመጥኩ:: |
| ወበላዕሌሆን አግበርኩ መሬተ እንዘ አምጸእኩ እም መካናት ቅዱሳት:: | ከቅዱሳት መካናት የአስመጣሁትን አፈር በዚያ ላይ አስደለደልኩ:: |
| ወኮነት ምድረ ሠናይተ:: | ፈጽማ ደስ የምታሰኝ ዕድልት ብርሀት የሆነች ቦታ ሆነች:: |
| ወሐነፅክዋ ለቤተ እግዚአብሔር አብ በሠናይ ሕንፃ በወርቅ | ከዚህ በኋላ ዓፅመ ቅዱሳንን መሠረት አድርጌ የእግዚአብሔር አብን |

| | |
|---|---|
| ወበዕንቈ ወበመረግድ ወበባሕርይ በከመ አገበረኒ መንፈስ ቅዱስ። | ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ እንዳነሳሣኝ በወርቅ በዕንቁ አስጊጬ የአማረች የተወደደች አድርጌ ሠራሁ። |
| ወአሜሃ በኃይለ መስቀሉ ለክርስቶስ ዋከየት ኵላ ሀገረ ኢትዮጵያ።[8] | ያን ጊዜም ክቡር በሆነ በክርስቶስ መስቀል ኃይል መላዋ ኢትዮጵያ በብርሃን አጌጠች። |
| ዕውራን ርእዩ። | ዓይነ ሥጋቸው በጨለማ ዓይነ ሕሊናቸው በድንቁርና ተሸፍኖ የነበሩ ዕውቀት ብርሃን ገንዘብ አደረጉ። |
| ጽሙማን ሰምዑ። | ጽሙማን ሥጋ በተአምራት ጽሙማን ነፍስ በትምህርት ዕውቀትን ገንዘብ አደረጉ። |
| ሐንካሳን ሖሩ። | ሐንካሳን ሥጋ በተአምራት ሐንካሳን ነፍስ በትምህርት ድኅነትን ጕዳና አደረጉ። |

[8] ሊቀ ቅዱስ ያሬድ አስቀድሞ ትንቢት ተገልጾለት መስቀሉ እንደ ሚቀመጥባትና ሲናገር እንተ ተሐነፀት በስሙ ወተቀደሰት በደሙ ወተዓትበት በዕፀ መስቀሉ ጊዜ ኀቤሃ እስመ ኃይለ እግዚአብሔር ላዕሌሃ ብሎ ነበርና



| | |
|---|---|
| ወበሐማን ተናገሩ። | መናገር የማይችሉ በመስቀሉ ተአምራት ደኅነው ሕይወትን ገንዘብ አደረጉ። |
| አጋንንት ወጽኡ። | አጋንንት በመስቀሉ ተአምራት ከሕሙማን ተለዩ ሸሹ። |
| ወሙታን ተንሥኡ። | ሙታንም ተነሡ ። |
| ወብዙኀ ተአምር ወመንክር ተገብረ ቦቱ። | በዚህ በመስቀሉ የተፈጸመው ድንቅ ሥራ ብዙ ነው ለምእመናን ማስረጃ ያህል ይህን ጻፍንላችሁ እንጂ። |
| እስመ ላዕሌሁ ተሰቅለ ወልደ እግዚአብሔር ወከዓወ ደሞ ክቡረ። | ሰማዩን ምድሩን ባሕሩን የብሱን የፈጠረ አምላክ ተሰቅሎ የከበረ ደሙን አፍስሶበታልና። |
| ወአንበርኩ ሠላሰ አዕባነ ዘትእምርተ መስቀል በቅድመ ምሥዋዕ ከመ | በውስጥ ለሚገኘው መስቀሉ ላለበት ቤተ ክርስቲያን በር ምልክት እንዲሆን መስቀል |

| | |
|---|---|
| ይኩና ትእምርተ ለአንቀጸ ቤተ ክርስቲያን ዘታሕቱ። | ቅርፅ የተቀረፀ ሦስት ድንጋዮች በዋናው በር ፊት ለፊት አስቀመጥኩ። |
| ወእምዝ አዘዝኩ ከመ ኢይትቀበር ሰብእ እም ላዕለ እሉ አዕባን ዘእንበለ በአፍዓ። | እኒህን ድንጋዮች ከተከልኩ በኋላ ከነሱ በውጭ እንጅ ከነሱ በውስጥ ሰው እንዳይቀበር ጽኑ ትእዛዝ አዘዝኩ አዋጅ አደረኩ። |
| ወካዕበ አዘዝኩ ከመ ይንጽፉ ክርቤ ወምስከ በእንተ ዘሰመያ መልአክ ደብረ ክርቤ። | ዳግመኛም መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል ደብረ ክርቤ ትባል ብሎ እንደ ነገረኝ ሽቱ ያረፈረፉባት ሽቱ ያነጽፉባት ዘንድ አዘዝኩ። |
| ወይእቲ ደብርኒ አርዓያ መስቀል ይእቲ። | ይህችው ደብራችን ክቡር የሆነ ጌታችን ለተሰቀለበት መስቀል አምሳል ናት። |
| ወአዘዝኩ ከመ ይንበሩ ዲቤሃ እምአበዊነ እስራኤል እለ ተሐርዩ ለመንግሥት። | ቀደም ብሎ የነገሥታቱ ልጆች መቀመጫ በመሆኗ ደብረ ነገሥት ስትባል እንደ |



| | |
|---|---|
| | ነበረ አሁንም በዚሁ መሠረት ከአባቶች ከነገሥታቱ ልጆች ለመንግሥት የተመረጡት ሁሉ ከዚህች ቦታ ውስጥ ይቀመጡ ዘንድ አዘዝኩ። |
| ወበእንተዝ በጸጋ እግዚአብሔር ሰመይናሃ ደብረ ነገሥት | የነገሥታቱ ልጆች በውስጧ ተቀምጠው እንዲማሩባት ስለአዘዝኩ በጸጋ እግዚአብሔር እንደ ቀድሞው ደብረ ነገሥት ብለን ሰየምናት ጠራናት። |
| በእንተ ዘይትመሐፀኑ ባቲ ነገሥታተ ኢትዮጵያ መሳፍንት ወመኳንንት። | በመንግሥታቸው ያሉ ነገሥታቱና መሳፍንቱ በየዓመቱ እየመጡ እጅ ስለሚነሱባትና በረከት ስለሚአገኙባት። |
| ወካዕበ ካህናትኒ ሰመይዋ ደብረ ክርቤ። | ሁለተኛም እኛ ደብረ ነገሥት ብለን ሰይመናት ነበርና ጳጳሳቱ ካህናቱ ሽቱ ስለተረበረበባት ደብረ ክርቤ ብለው ሰየሟት። |

መካነ መስቀል ብሂል በከመ ይቤ ሰሎሞን በመንፈስ ቅዱስ ንዑ ንሑር ውስተ ደብረ ከርቤ።

ደብረ ከርቤም ማለት መካነ መስቀል ማለት ነው። ሰሎሞን ቀደም ብሎ ምእመናን ወደዚህ መጥተው እጅ መንሳት እንዲገባቸው ለማጠየቅ "ኑ ወደ ደብረ ከርቤ እንሂድ" ብሎ በመንፈሱ ተናግሯልና ደብረ ከርቤ አለ።[9]

በከመ ሰመያ መልአክ ቀዳሚ።

መልአኩ አስቀድሞ "ደብረ ከርቤ" ትባል ብሎ እንደተናገረ ደብረ ከርቤ ብለው ሰየሟት።

ቅድመሰ ይብልዋ ደብረ ነጐድጓድ።

ቀድሞ ግን ደብረ ነጐድጓድ ትባል ነበር።

[9] ከርቤ የተሰበረውን ይጠግናል የተለያየውን አንድ ያደርጋል ይህችም ቦታ ከጌታ በተሰጣት ቃል ኪዳን መሠረት በኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር አንድነት የተለዩት በዚህ ቦታ መጥተው ንስሐ ገብተው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው የሚማፀኑ ኃጢአታቸውን አስተስርያ ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቃ አንድነትን አሰጥታ ገነት መንግሥተ ሰማያት ታገባቸዋለችና ስለዚህ ደብረ ከርቤ አለ።



ለዝ ነገር ሠራዕኖ ለትውልደ ትውልድ።

ይህን ሥርዓት ከልጅ ልጅ እንዲተላለፍ ብለን አዘናል ጽፈናል ሠርተናል።

ወካዕበ አዘዝክዋ ለእኅትየ ዕሌኒ ንግሥት ወለተ ዳግማዊ ዳዊት ከመ ተሐድስ ሕንፃሃ ለቤተ ክርስቲያን ዘእግዚእትነ ማርያም ውስተ ይእቲ ደብር።

ቀደም ብሎ ፈቃደ ክርስቶስ ተአምራት እያደረገችለት እየተማፀነባት የአመጣትን የእመቤታችንን ታቦት ዓፄ ይኩኖ አምላክ ለነገሥታቱ ሴቶች ልጆች መማፀኛ ሲሉ ለይተው ቤተ ክርስቲያኗን አሠርተው ቦታይቷን ደብረ ነገሥት ብለው ሰይመው ስትኖር በጊዜ ብዛት የተነሣ ቤተ ክርስቲያኑ አርጅቶ ነበርና የዳግማዊ ዳዊት ልጅ እኅቴ ንግሥት ዕሌኒን መንፈሳዊ ቅንዓት አትቀኚምን እኔ ምን ስሠራ ታያለሽ አንችስ በእመቤታችን ስም የታነጸችውን ቤተ ክርስቲያን አታሳድሽምን ብዬ አዘዝኳት።

እንተ ርኅቅት መጠነ መዓልተ ዕብን።

የቦታውም ርቀት እኔ ከሠራሁበት ቦታ አንሥቶ ጐልማሳ ድንጋይ ወርውሮ እንደሚያደርስበት ነው።

| | |
|---|---|
| ወይእቲኒ ሐደሰት ወሐነጸት አሠርጊዋ በወርቅ ወበዕንቊ ወበብሩር። | እሷም ለበጐ ነገር በጣም ቀናተኛ ነበረችና ይህችኑ ቤተ ክርስቲያን በወርቅ በዕንቊ በብር አስጊጻ አድሳ አሠራች። |
| ወአመ ቅዳሴ ቤቱ ለእግዚአብሔር አብ ፲፻ ወ፩፻ ፵ወ፱ ዓመት እምልደተ መድኃኒነ አመ ፳ ወ፩ ለመስከረም። | የእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያንም ታቦቱ በሚገባበት መስከረም ሃያ አንድ ቀን ሺህ አራት መቶ ዐርባ ዘጠኝ ዓመተ ምሕረት |
| መጽአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ሀሎ በሥላሴሁ ዲበ ዘባነ ኪሩቤል። | ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድነት በሦስትነት በዘባነ ኪሩቤል እንዳለ ሁኖ መጣ። |
| ወምስለ እመ ቅድስት ድንግል ማርያም | ንዕድ ክብርት ከምትሆን ከእናቱ ከእመቤታችን ቅድስት ማርያም ጋራ |
| ወአእላፍ መላእክት ይቀውሙ ዐውደ | አእላፋት መላእክት ዙሪያውን ሁነው እያመሰገኑ መጡ |



| | |
|---|---|
| ወእስተርእየነ ለአባ ሚካኤል ወለ አባ ገብርኤል ዘእስክንድርያ | ከእስክንድርያ ለመጡት ለጳጳሳቱ ለአባ ሚካኤልና ለአባ ገብርኤል |
| ወለአባ ዮሐንስ ኤጲስ ቆጰስ ዘደብረ ምጥማቅ | ለኤጲስ ቆጶስ ለአባ ዮሐንስ ዘደብረ ምጥማቅ |
| ወሊተኒ | ለእኔም |
| ወነገረነ እንዘ ይብል | እንዲህ ብሎ ነገረን |
| ጊዜ ስቅለትየ በቀራንዮ ሀገር ቀደሐ ደመ እምገበየ ዑራኤል መልአክ | አይሁድ ቀራንዮ በሚባል ሀገር በሰቀሉኝ ጊዜ ዑራኤል መልአክ ከጎኔ የፈሰሰውን ደሜን በብርሃን ፅዋ ተቀብሎ |
| ወቀደሰ ኵለንታሃ ለዛቲ ደብር። | ይህችን ደብር ሁለመናዋን ቀድሷታል። |
| ወአነሂ ባረክዋ። | እኔም አከብሬያታሁ። |

| | |
|---|---|
| ወይእዜኒ ዳግመ ረሰይክዋ ትኩን ቅድስተ መካነ ከመ ደብረ ታቦር መካነ ምሥጢርየ። | አሁንም ዛሬም ምሥጢረ መንግሥቴን የገለጽኩበትን ደብረ ታቦርን ትሁን ብየ። |
| ወቀራንዮ መካነ ስቅለትየ። | የተሰቀልኩበትን ቀራንዮን ትሁን ብየ። |
| ወጐልጎታ መቃብርየ። | የተቀበርኩባት ጐልጎታን ትሁን ብየ። |
| ወከመ ኢየሩሳሌም ሀገረ እምየ ዘነሣእኩ እምሥጋዚአሃ ንጹሕ። | ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሳቼ ሰው የሆንኩባት በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት የምትሆን እናቴ ተወልዳ የአደገችበትን ኢየሩሳሌምን ትሁን ብየ አከብሬታለሁ። |
| ወለእመ ነገደ ኀቤሃ ይኩን ከመ ዘነገደ ኀበ መቃብርየ ኢየሩሳሌም። | ከዚህችም ቦታ መጥቶ የሳመ ሰው ኢየሩሳሌም ሂዶ እንደ ሳመ እቈጥርለታለሁ፡ |



| | |
|---|---|
| ወለእመ ተመጠወ ሥጋየ ወደምየ ውስተ እሉ አብያተ ክርስቲያን። | እዚህም መጥቶ ስሞ ከእነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች ገብቶ ሥጋዬን ደሜን የተቀበለውን። |
| አነ አድኅኖ እሞተ ኃጢአት ዘውስተ ደይን | ኃጢያቱን ፍቄ በኃጢአቱ ከሚፈረድበት ፍዳና መከራ ከገሃነመ እሳት አድነዋለሁ፡ |
| ወይከውን ከመ ሕፃን እንተ ባቲ ተወልደ | አዲስ እንደተወለደ ሕፃን አደርገዋለሁ ዕለቱን የተወለደ ሕፃን ምንም ርስሐተ ኃጢአት እንደሌለበት እሱንም ጽሩይ አድርጌ መንግሥተ ሰማያት አገባዋለሁ ሲል |
| ወለእመ ነበረ ውስቴታ። | ርስቱን ጉልቱን ትቶ መንኖ መጥቶ ከዚህ የተቀመጠውን። |
| ወተቀበረሂ በጊዜ ሞቱ። | በሞተም ጊዜ አምኖ ከዚህ መጥቶ የተቀበረውን። |

አነ እጸውሮ ዲበ እንግዳየ ወአዓድዎ ባሕረ እሳት ዘሲዖል

እኔ በረድኤት አቅፌ የሲዖል ባሕረ እሳትን አሻግረዋለሁ

ወእኅብሮ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት ዘጽድቅ ወዘሕይወት።

በዚህ ጊዜ ታልፋለች የማትባል የሕይወት የጽድቅ መገኛ በምትሆን ገነት መንግሥተ ሰማያት አገባዋለሁ።

ወለዛቲ መካን ምዕራፈ ታቦት ረሰይክዋ ትኩን ከመ ጽርሐ ጽዮን ዘአግሃድኩ ባቲ ርእስየ ለአርዳእየ ንጹሐን እምድኅረ ትንሣኤየ እሙታን

ይህችንም የምሕረት አደባባይ ከሙታን ተለይቼ ከተነሣሁ በኋላ ንጹሐን ክቡራን ለሚሆኑ ደቀ መዝሙሮቼ እኔ መሆኔን የገለጽኩባትን ጽርሐ ጽዮንን ትሁን ብየ አክብሬአታለሁ።

እስመ ባቲ አግሃድኩ ርእስየ ለክሙ ከመ ፍጹመ ይኩን ፍሥሐክሙ።

ፈጽሞ ደስ ይላችሁ ዘንድ ራሴን በቸርነት ለእናንተ ገልጬባታለሁና።

ወዓዲ ለዛቲ መካን ዘሀለወት ማዕከለ አብሕርት ረሰይክዋ ትኩን ከመ ደብረ ዘይት።

ዳግመኛም ሁለቱን ባሕሮች እንደ መከዳ ግራና ቀኝ አርጋ አጊጣ የምትታየውን ኮረብታ እንደ ደብረ ዘይት ትሁን ብየ አክብሬታለሁ።

ወአንትሙሂ ግብሩ ጸሎተክሙ ዲቤሃ በጊዜ ምሕላሕሙ።

እናንተም በንጽሐ ልብና በፍቅር በአንድነት ሁናችሁ ምሕላ በምትይዙበት ጊዜ ጸሎታችሁን በዚህችው ቦታ ላይ አድርጉ።

ወአነሂ እፌጽም ለክሙ ስእለተክሙ ኩሎ ጊዜ እስከ ሕልቀተ ዓለም።

እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ በፍቅር በአንድነት ሁናችሁ በዚህች ቦታ ላይ የምታቀርቡትን ልመናችሁን እሰማለሁ ምኞታችሁንም ሁሉ እፈጽምላችኋላሁ።

እምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል በቆለት ዲቤሃ አሐቲ ዕፀ ዘይት።

ከጥቂት ቀን በኋላ ከዚህችው ቦታ ላይ አንዲት የወይራ ተክል ዛፍ በቅላ ተገኘች።

| | |
|---|---|
| ወሀለወት እስከ ይእዜ ለተዝካረ ኪዳኑ ለአምላክነ በመጠነ ቆመ ብዕሲ. | ይህችም ወይራ እስከ አሁን ድረስ ጌታችን ለሰጠን ቃል ኪዳን መታሰቢያ እንድትሆን በሰው ቁመት ልክ አለች፡፡ |
| ወለዘሀለወት ባሕር እንተ ምዕራብ ረዕይክዋ ትኩን ከመ ዮርዳኖስ ዘቦቱ ተጠመቁ፡፡ | ከሁለቱም ባሕሮች በምዕራብ በኩል ያለችውን ባሕር እንደተጠመኩበት እንደ ዮርዳኖስ ትሁን ብየ አክብሬአታለሁ፡፡ |
| ወዘሂ ተጠምቀ ባቲ ይረክብ ጥዒና ወይትፌወስ እምደዌ ነፍሱ ወሥጋሁ፡፡ | በዚህችም የተጠመቀ ለደዌ ሥጋው ጤና ለደዌ ነፍሱ ሥርየተ ኃጢአት ያገኛል ብየ እነግራቸውኃለሁ፡፡ |
| ወዘንተ ኪዳነ እምድኅረ ወሀበነ ባረከነ ወባረካ ለዛቲ መካን፡፡[10] | ይህን ቃል ኪዳን ከሰጠን በኋላ እኛንም በዓሉን ለማክበር የመጡትን ሕዝቦች ባረከን ቦታይቱንም ባረካት አከበራት፡፡ |

---

[10] ዓኄ ዘርዓ ያዕቆብ ከዮርዳኖስ ወሀ በአራት ግመል አስጭነው አምጥተው ቀላቅለውበታልና ሕሙማን እስከ አሁን ድረስ ከደዌ ሥጋቸው ይፈቱበታል



| | |
|---|---|
| ወእምድኅረዝ ዓርገ ውስተ ሰማያት በዓቢይ ስብሐት፡፡ | ከዚህ በኋላ በክብር በሥልጣን እንደመጣ በክብር በሥልጣን ወደሰማይ ዓረገ፡፡ |
| ወእምዝ በራብዕ ወርኀ እም አመ ኮነዝ አመ ፳ወ፩ ለጥር ኮነ ቅዳሴሃ ለቤተ | ከዚህ በኋላ ቃል ኪዳን በሰጠን በአራተኛው ወር ጥር ሃያ አንድ ቀን |
| ክርስቲያን ዘእግዝእትነ ማርያም ዘሐነፃታ እሌኒ ንግሥት | እኅቴ ንግሥት ዕሌኒ በእመቤታችን ስም አድሳ የአሠራችት ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤቷ ሆነ፡፡ |
| ወመጽአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በደመና ሰማይ ምስለ እሙ ቅድስት ድንግል፡ | ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባህርየ ክብሩ እንዳለ ሁኖ ንዕድ ክብርት ከምትሆን ከእናቱ ጋር፡፡ |
| ወአዕላፍ መላእክት ይቀውሙ ዓውደ፡፡ | አእላፍ መላእክት ዙሪያውን ሁነው እያመሰገኑት መጣ |

| | |
|---|---|
| ወአስተርአየነ ከመ ቀዳሚ፡፡ | መስከረም ሃያ አንድ ቀን የእግዚአብሔር አብን ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤቱን ባከበርንበት ቀን እንደ ተገለጸልን ሁኖ ታየን፡፡ |
| ወይቤለነ ዛቲ መካነ ምዕራፍየ ይእቲ እስከ ለዓለም፡፡ | ይህች ቦታ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የስሜ መመስገኛ በረድኤት መገለጫየ ናት አለን፡፡ |
| ወእለሂ ይነብሩ ውስቴታ እንዘ ይሰፈው ዐሥራተ እምየ ይከውኑ ከመ መላእክተ እግዚአብሔር፡፡ | የእናቴን አማላጅነቷን አምነው ከዚህች ቦታ ውስጥ የሚኖሩትም እንደ መላእክት አደርጋቸዋለሁ፡፡ |
| ወእለሂ ተመጠው ሥጋየ ወደምየ ውስተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን | በዚህችም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥጋዬን ደሜን የተቀበሉትን |
| ይከውኑ ከመ ሕፃናት ዘቤተልሔም ዘተቀትሉ በእንተ ስምየ፡፡ | በእኔ ስም ደማቸውን እንደ አፈሰሱ የቤተልሔም ሕፃናት ይሆናሉ፡፡ |



| | |
|---|---|
| ወለዛቲ ቤተ ክርስቲያን ረሰይክዋ ትኩን ከመ ጌቴሴማን መቃብረ እምየ፡፡ | ይህችንም ቤተ ክርስቲያን እንደ እናቴ መቃብር እንደ ጌቴሴማኒ ትሁን ብየ አክብሬአታለሁ፡፡ |
| ከመ ትኩንክሙ ሐመረ በዕለተ ምንዳቤክሙ | በችግራችሁ ጊዜ ወደ መንግሥተ ሰማያት መሸጋገሪያ መርከብ እንድትሆናችሁ፡፡ |
| ወዘተማሕፀነ ኀቤሃ ኢይትኃፈር ለዓለም፡፡ | ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ገብቶ የተማፀነም ለዘለዓለም አያፍርም ዋጋውን አያጣም፡፡ |
| ወለኵሉ ዘመጽአ ኀቤሃ በዕለተ በዓለ ዕረፍታ ወዕርገታ ለእምየ ተዘኪሮ ኪዳነ ዘወሀብክዋ፡፡ | ለእናቴ የሰጠኋትን ይህን ቃል ኪዳን አስቦ አምኖ እናቴ ባረፈችበት ጥር ሃያ አንድ ቀን ባረገችበት ነሐሴ ዐሥራ ስድስት ቀን ከዚህች ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ዕጅ የነሣውን በዓሏን ያከበረውን፡፡ |

| | |
|---|---|
| እሬስዮ ዐሥራተ ምሕረት ለእምየ ማርያም። | ለእናቴ ወገን ቤተሰብ አደርገዋለሁ። |
| ወለከሙ፡ሂ እለ ፃመውክሙ በእስተሐምሞ ሕንፃ ቤተ እምየ። | በእናቴ ስም ለታነጸችው ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ኖራ በመለወስ ዕንጨት በመጥረብ ድንጋይ በማቅረብ ለደከማችሁ ለእናንተም። |
| ወበእስተንትኖ ንዋየ ቅዳሴሃ። | ፃሕሉን ጽዋውን ንዋየ ቅድሳቱን መስቀሉን በመሥራት በማሠራት ለደከማችሁ ለእናንተ። |
| እሁበከሙ ዓሰበከሙ ዘዓይን ኢርእየ ወዕዝን ኢሰምዓ ወውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተሐለየ። | በሰው አእምሮ ሊታሰብ የማይቻል ዓይን አይቶ ጆሮ ሰምቶ ሊመረምረው የማይቻለውን ዋጋችሁን እሰጣችኋለሁ። |
| ወእጽሕፍ ስመክሙ ውስተ መጽሐፈ ሕይወት። | ስማችሁን በሕይወት መጽሐፍ እጽፍላችኋለሁ። እለ እገልጸዋለሁ ሲል። |



| | |
|---|---|
| ወዘሂ ይናፍቅ ዘንተ ኪዳነ ዘወሀብኩክሙ በእንተ ክብራ ለቅድስተ እምየ። | ለቅድስት እናቴ ክብር ስል የሰጠኋችሁን ይህን ቃል ኪዳን የሚጠራጠር ቢኖር፡ |
| ወበእንተ ቅዱስ መስቀል ዘቀደስክዎ በክዕወተ ደምየ። | በከበረ ደሜ ፈሳሽነት ላከበርኩት ቅዱስ መስቀል ክብር ስል የሰጠሁትን ቃል ኪዳን ያቃለለ ቢኖር፡ |
| አልቦቱ ክፍል ምስሌየ። | ከእኔ አንድነት የለውም |
| ወምስለ ማርያም እምየ። | በእናቴ ድንግል ማርያም አማላጅነት ከሚገኘው ክብር ልዩ ነው |
| ወዘንተ ተናጊሮ ዓርገ ውስተ ሰማያት። | ይህን ቃል ኪዳን ሰጥቶን በክብር በሥልጣን ወደ ሰማይ ዓረገ። |
| ወእምዝ አመ ፲ወ፫ ለነሐሴ አስተርአዮሙ እግዚአብሔር ለአባ ሚካኤል ወለአባ | ከዚህ በኋላ በዚሁ ዓመት ነሐሴ ዐሥራ ሦስት ቀን እግዚአብሔር ለአባ ሚካኤልና ለአባ ገብርኤል |

| | |
|---|---|
| ገብርኤል። | ተገልጾ ተነጋገራቸው። |
| ወይቤሎሙ። | እንዲህ ብሎ |
| አነ ሐረይክዎ ቀዳሚ ለዛቲ መካን እምኵሉን አድባራት። | አስቀድሜ ከአድባራቱ ሁሉ ይህችን ቦታ መርጬ። |
| ወረሰይክዎ ማኅደረ ስምየ እስከ ለዓለም። | እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የስሜ መመስገኛ የጌትነቴ መገለጫ አደረኳት። |
| ወበከመ ከሠትኩ በዛቲ ዕለት ምሥጢረ ስብሐተ ወልድየ ላዕለ ደብረ ታቦር። | በዛሬው ቀን የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት ብዬ የልጄን የባሕርይ ልጅነቱን በደብረ ታቦር እንደ መሰከርኩለት። |
| ከሠትኩ ለክሙ ምሥጢረ ሂሩትየ ላዕለ ዛቲ መካን በዛቲ ዕለት። | ዛሬም በዚህች ቦታ የቸርነቴንና የርኅራሄዬን ምሥጢር ገለጽኩላችሁ። |
| እንዘ እብል። | እንዲህ ብዬ። |



| | |
|---|---|
| ኵሉ ዘመጽአ ኀበ ዛቲ መካን በዛቲ ዕለት ወተማኅፀነ። | በዛሬው ቀን በየዓመቱ ከዚህ ቦታ መጥቶ ዕጅ የሚነሣ ሁሉ። |
| ኢይትኃጐል ለዓለም። | አይለይም ለዘለዓለም አይጠፋም። |
| ወእነሂ ኢየኃድግ ሐውፆታ ለዛቲ መካን በዛቲ ዕለት ለለወርኅ ወለለዓመቱ እስከ ሕልቀተ ዓለም። | እኔም ይህችን ቦታ በዛሬው ቀን እንደ ዛሬው በየወሩ በየዓመቱ ይህ ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ በረድኤት አልለያትም። |
| ወዘንተ ተናገሮ ተሠውረ እምኔሆሙ። | ይህን ቃል ኪዳን ከሰጣቸው በኋላ ተሠወራቸው። |
| ወዜነውነ ዘንተ በቃለ መሐላ ጽኑዕ። | ይህም ቃል ኪዳን እውነት እንጂ ሐሰት አለመሆኑን ጽኑዕ በሆነ መሐላ ነገሩን። |
| ወበእንተ ዝንቱ ኪዳን | ይህን ቃል ኪዳን ከጌታችን |

| | |
|---|---|
| ሠርዕዋ ለዛቲ ሥርዓት አባ ሚካኤል ወአባ ገብርኤል ወአባ ዮሐንስ ኤጲስ ቆጶስ ብሂሎሙ ትኩን ቀራንዮሃ:: | ከኢየሱስ ክርስቶስ ስለስሙና ስለአገኙ አባ ሚካኤል አባ ገብርኤል ኤጲስ ቆጶሱ አባ ዮሐንስ ቀራንዮን ትሁን ብለው:: |
| ወጐልጎታሃ:: | ጐልጎታን ትሁን ብለው:: |
| ወታቦርሃ:: | ደብረ ታቦርን ትሁን ብለው ይህን ሥርዓት ሠሩ:: |
| እስመ ኢረከብነ ካልዓ ዘይትማሰላ ዘእንበሌሆን እምአድባራት:: | ይህችን ቦታ የሚመስላት በክብር የሚተካከላት ያለነዚህ በቀር ሌላ ቦታ አላገኘንምና:: |
| ለዛቲ መጽሐፈ ሥርዓት ዘአስተቃለላ ወናፈቃ | ይህችን የሥርዓት እና የቃል ኪዳን መጽሐፍ የተጠራጠረ የናቀ ሰው:: |
| ይኩን ክፍሉ ከመ አርዮስ | ዕድል ፈንታው ጽዋ |



| | |
|---|---|
| ዘይቤ ወልድ ፍጡር:: | ተርታው ወልድን ፍጡር ብሎ ክዶ በ፫፻፲፰ ሊቃውንት እንደተለየው እንደ አርዮስ ይሁን:: |
| ወለነሂ በዘኢኮነ ነገር እመ ወደስናሃ ወአዕበይናሃ በዘኢይደልዋ ውዳሴ ወዕበይ ወክብር:: | እኛም ጌታ ቀራንዮ ያላላትን ቀራንዮ ናት፣ ጐልጎታ ያላላትን ጐልጎታ ናት፣ ደብረ ታቦር ያላላትን ደብረ ታቦር ናት፣ ኢየሩሳሌም ያላላትን ኢየሩሳሌም ናት ብለን በማናቸውም ሁሉ ጌታ ያልሰጣትን ክብርና ስም እኛ ሰጥተን፣ የክብር ክብር የሌላትን እንዳላት አድርገን በማይገባት ክብር አክብረናት እንደሆነ:: |
| ይኖልቍነ እግዚአብሔር ምስለ ይሁዳ ሠያጤ እግዚኡ:: | ዕድል ፈንታችን ጸዋዕ ተርታችን ጌታውን ሸጦ ከማኅበረ ሐዋርያት እንደ ይሁዳ ተለየው ይሁን:: |
| ወይኩን ክፍልነ ምስለ አይሁድ ዘሰቀልዎ | ዕድል ፈንታችን ጽዋ ተርታችን ጌታቸውን |

| | |
|---|---|
| ለእግዚእነ | ጸልተው ተመቅኘተው እንደ ሰቀሉት እንደ አይሁድ ይሁን። |
| ወለዝ ነገር ዘያስተቃልሉ አውገዝነ ወአሠርነ በቃልነ ዘኢይትፈታሕ።[11] | ይህን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቃል አግኝተን የተናገርነውን ቃል ኪዳንና የሠራነውን ሥርዓት የናቀ፣ የተለየ ይሁን ብለን አውግዘን ለይተነዋል። |
| በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ | ሥጋውን ደሙን ስለተቀበልን የክርስቶስ |

[11] ስለዚህ ከዚህ ቦታ መጥቶ ኃጢአት አይሠረይም ማለት ከላይ የተነገረው ቃል መርገም ይፈጸምብኝ ማለት ነው እንዲህ ስላልን ግን እንዲህ ያለች ቦታ ካለች ኃጢአት እየሠራን በየዓመቱ እየሄድን እናስተሰርያለን ብሎ ማሰብ የእሪያ ሕጽበት ማለት ነው። እሪያ ቁርበቱ ስስ ሥጋው ትኩስ ነው ዋዕየ ፀሐይ ሲተኩሰው ከጭቃ ይለውሻል ከጭቃ ወጥቶ ከባሕር ከባሕር ወጥቶ ከፀሐይ ሲል ፈርሶ በስብሶ ይቀራል። እንደዚህም ሁሉ ከዚህ ተመልሶ እያወቁ ከኃጢአት መጨመር በፍዳ ላይ ፍዳ የሚያመጣ እንጅ ሥርየተ ኃጢአት ስለማያስገኝ መጠንቀቅ ይገባል። ነገር ግን ሰው ሆኖ ከኃጢአት የሚለይ ስለማይገኝ በስሕተት ስለሚሠራው ኃጢአት በየዓመቱ መጥቶ ንሥሐ ገብቶ ዕጅ መንሣቱ ጠቃሚ ነው ቀደም ብሎ ግን አውቆ በድፍረት ሳያውቅ በስሕተት ስለሠራው ኃጢአት መጀመሪያ ከዚህ ቦታ መጥቶ ንስሃ ገብቶ በመሳለሙ ስለተሠረየለት ለእግዚአብሔር አብ ክብር ምስጋና ይድረሰው።



| | |
|---|---|
| ክርስቶስ አሜን። | አካል ማኅበር ቤተሰብ ስለተባልን ለዘለዓለሙ ይሁን አሜን። |
| ወበእንተዝ ይደልዎሙ ለምእመናን | ለሕዝበ ክርስቲያን ነን ለሚሉ ለምእመናን ሁሉ |
| ለጳጳሳት። | ለጳጳሳቱ፣ |
| ወለካህናት። | ለካህናቱ፣ |
| ለነገሥት ወለመኳንንት። | ለነገሥታቱ ለመኳንንቱ። |
| ለዕድ ወለአንስት ከመ ይምጽኡ በበዓመት ኀበ ዝንቱ መካን ቅዱስ። | ለወንዶቹ ለሴቶቹም ሁሉ በየዓመቱ ከዚህች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ባርኮ በደሙ ቀድሶ ካከበራት ቦታ መጥተው። |
| ወከመ የአምኅዎ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰቅለ ቦቱ ለአድኅኖተ ዓለም። | ይህን ዓለም ለማዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ዕጅ ይነሱ ዘንድ ይገባቸዋል። |

ከመ ይትኃደግ ሎሙ ኃጢአቶሙ በእንተ ክብረ እሙ ወበእንተ ክብረ መስቀሉ ክቡር።

እመቤታችንንና የከበረ መስቀሉን የሚያከበሩ ኃጢአታቸው ይሠረይላቸው ዘንድ። አሜን።

## ምዕራፍ ፬

## ምዕራፍ ፬

ወካዕበ ንጽሕፍ ክታበ ዘተፈነወት እምኀበ ንጉሥነ ዘርዓ ያዕቆብ ዘተሰምየ ቈስጠንጢኖስ።

ዳግመኛም ስመ መንግሥታቸው ቈስጠንጢኖስ ከተባለ ከዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የተላከችውን ክታብ እንጽፋለን።

ኀበ ኵሎሙ ማኅበረ ጽኤል ወኀበ ኵሎሙ ካህናተ ደብተራ ዘመርጡል።[12]

በግሸን ደብረ ከርቤ ለሚኖሩ ማኅበረ እስራኤል ለተባሉ ምእመናንና ካህናተ ደብተራ

ወኀበ እለ ይነብሩ ውስተ ደብረ ከርቤ ማኅደረ እግዚአብሔር አብ።

በእግዚአብሔር አብና በእመቤታችን አብያተ ክርስቲያናት ለሚያገለግሉ ካህናት ትደርስላቸው።

[12] ጽኤል ማለት ሕዝበ እግዚአብሔር ማለት ነው።



እንዘ ይብል።

እንዲህ ብሎ።

ውእቱ አቡነ።

አባታችን እሱ ነው።

ወውእቱ እምነ።

እናታችንም እሱ ነው አለ አስገኛችን እሱ ነው ሲል

ወውእቱ ዓቃቤ ነፍሳቲነ።

የሰውነታችንም ጠባቂ እሱ ነው አንድ የቀን አንድ የሌሊት ሁለት ጠባቂ መላእክት እየሰደደ ያስጠብቀናልና።

ወይእዜኒ ይዕቀብክሙ ወይቀበነ።

አሁንም በመስቀሉ ይጠብቃችሁ ይጠብቀን።

በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ አምላክነ ለዓለመ ዓለም።

ሥጋውን ደሙን ተቀብላችሁ ለክርስቶስ አካል ማኅበር ቤተሰብ ስለተባላችሁ ለዘለዓለሙ ይጠብቃችሁ ይጠብቀን።

| | |
|---|---|
| አሜን:: | በእውነት ይሁንልን ይደረግልን:: |
| አሜን ወአሜን:: | መልሶ መላልሶ አሜን ወአሜን አለ ያለማቋረጥ ይጠብቃችሁ ይጠብቀን ሲል:: |
| ለይኩን ለይኩን:: | ተስፋ መንግሥተ ሰማያት ሥርየተ ኃጢአት ይደረግላችሁ ይሁን ይሁን ይደረግልን:: |
| በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ ለይኩን ለይኩን:: | ስለነፍስ ስለ ሥጋ ስለሕዝብ ስለ አሕዛብ ሲል ሥጋው ደሙ ደገኛ ነገር ነውና ስለ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ሲል ይሁንልን ይደረግልን:: |
| ስምዑ ኵልክሙ ተፈሥሑ ወተሐሰዩ ወአንፈርዕፁ | በዓሉን ለማክበር ከዚህ የተሰበሰባችሁ ወንዶችም |



| | |
|---|---|
| በእግዚአብሔር:: | ሴቶችም ሁላችሁ ስሙ ስምታችሁም ፈጽሞ ደስ ይበላችሁ |
| ወናሁ አምጻእነ ወአንበርነ ለክሙ ዓቢያተ ባሕርያተ ዘኢይትረከብ ሤጠሙ ኢበወርቅ ወኢበዕንቍ ወኢበምንትኒ ንዋያተ ዓለም ዘኢይረከብዎን አምጻእነ ለክሙ መስቀሎ ለወልደ እግዚአብሔር ዘተሰቅለ ቦቱ እግዚእ ሰማያት ወምድር:: | አሁንም በወርቅ በዕንቍ በብር በማናቸውም ዓለማዊ ገንዘብ ያገኙታል የማይባል: ሰማዩን ምድሩን የፈጠረ አምላክ ወልደ እግዚአብሔር የተሰቀለበትን መስቀል አምጥተን አስቀምጠንላችኋልና:: |
| ወከለሜዳሂ ዘአልበስዎ በዕለተ ስቅለቱ ለሊቦሙ አልባሲሁ:: | ልብሱን ገፈው ገርፈው ካበቁ በኋላ ለተሣልቆ ያለበሱትን ከለሜዳውን:: |
| ወሰፍነግሂ ዘአስተይዎ ቦቱ ብሂዓ ዘምስለ ሐሞት ወከርቤ ቴሱሐ | ተጠማሁ ባለ ጊዜ ከርቤውንና ሐሞቱን ቀላቅለው መራራ ሐሞት ያጠጡበት ሰፍነጉን |

| | |
|---|---|
| ወአክሊለ ሶክ | የሾህ አክሊሉን |
| ወሐብለ ማዕሠረ እደዊሁ። | ዕጁን የኃሊት አሥረው የጎተቱበት ገመዱን |
| ወዘተጠብጠበ ቦቱ ዘመጽሉ በማዋዕሊነ። | የተገረፈበት ጅራፉን በእኔ ዘመን የመጡትን ሁሉ አስቀምጠንላችኂልና ፈጽሞ ደስ ይበላችሁ። |
| ወለመስቀለ ክርስቶስሰ ቀዳሚ ሶበ ረከበቶ ዕሌኒ ንግሥት በኢየሩሳሌም ፫፻ወ፱ ፳ወ፯ ዓመተ ሥጋዌ። | የጌታችንን መስቀል ግን አስቀድማ ንግሥት ዕሌኒ በሦስት መቶ ሃያ ሰባት ዓመተ ምሕረት በኢየሩሳሌም ከተቀበረበት አስቆፍራ ባገኘችው ጊዜ። |
| ገብረት ዓቢየ ፍሥሐ። | ታላቅ ደስታ አደረገች። |
| ወለአከት ኀበ ነገሥተ አፍርንግ። | ወደ አፍርንግ ነገሥታት። |
| ወኀበ ፬ ሊቃነ ጳጳሳት። | ለአራቱ ሊቃነ ጳጳሳት በያሉበት። |



| | |
|---|---|
| ወኀበ ኵሎሙ ክርስቲያን። | ወደምእመናኑ ሁሉ መልእክት ላከች። |
| እንዘ ትብል። | እንዲህ ብላ። |
| ተፈሥሑ እስመ ረከብክዎ ለመስቀለ እግዚእየ መድኃኒተ ኵሉ ዓለም በከመ ተመነይኩ። | በልቤ እንደተመኘሁት የዓለም መድኃኒት የሚሆንየጌታየን መስቀል ከተቀበረበት አግኝቻለሁና ደስ ይበላችሁ ብላ ላከች። |
| ወእሙንቱኒ ገብሩ በዓለ በፍሥሐ በበሀገሮሙ | እነሱም ይህን ሰምተው በየአሉበት ሆነው በፍጹም ደስታ የመስቀሉን በዓል አከበሩ። |
| ወምክንያተ ተረክቦቱሰ ለመስቀል ክቡር። | ክቡር የሆነ የጌታችን መስቀል የተገኘበት ምክንያትም ይህ ነው። |
| እምድኅረ ዕርገቱ ለእግዚእነ በ፫ ዓመት። | ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባረገ በሦስተኛው ዓመት |

ሶበ ርእዩ አይሁድ እንዘ ይትገበር ተአምር ወመንክር በመስቀሉ ለክርስቶስ፡

አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ጌታን በሰቀሉበት መስቀል ብዙ ተአምር ሲሠራ በዚህ ምክንያት የክርስቶስ ሃይማኖት እሰፋ እሰፋ የኦሪት ሕግ እጠፋ እጠፋ ሲል ባዩት ጊዜ። እጅግ ፈጽመው ቀኑ።

ተመልዑ ቀንዓተ ዓቢየ።

ክፉ ክፉውን ምክር መከሩ፡

ወመከሩ ምክረ እኩየ።

እንዲህ ብለው።

ወይቤሉ።

ሙሴ የጻፈልን ሕጋችን በዕንጨት ተሰቅሎ የሞተ ርጉም ነው ይላል።

እስመ ሕግነ ይብል ርጉም ውእቱ ዘስቁል ዲበ ዕፅ።

የተሰቀለበትም ዕንጨት ሳይቀር ርጉም ነው።

ወዕፁኒ።

ስለዚህ ከመሬት ልንቀብረው ይገባናል ብለው መከሩ።



በእንተዝ ንድፍኖ ዲበ ምድር።
እምድኅረዝ ከረዩ ዓዘቅተ በምሥራቀ ጎልጎታ ፳ በእመተ ብእሲ።

ከዚህም በኋላ ከጎልጎታ በምሥራቅ በኩል ስድሳ ክንድ የሆነ ጉድጓድ ቆፈሩ፡

ወቀበርዎ ለመስቀል ቅዱስ ምስለ መስቀለ ፈያት እስከ ፻፶ወ፳ወ፯ ዓመተ ሥጋዌ።[13]

ቆፍረውም አልቀሩ የጌታንን መስቀል አብረው ከተሰቀሉት ከሁለቱ ወንበዴዎች መስቀል ጋር ቀበሩት። እስከ ፻፶ወ፳ወ፯ ዓመተ ምሕረትም ተቀብሮ ቆየ ።

ወእምድኅረ እማንቱ ዓመታት መጽአት ዕሌኒ ንግሥት ሀገረ ኢየሩሳሌም።

ከእነዚህ ዓመታት በኋላ ንግሥት ዕሌኒ ወደ ኢየሩሳሌም መጣች።

ወምስሌሃ አውሳብዮስ ወመቃርዮስ ኤጲስ

ከሷም ጋር ኤጲስ ቆጶሱ አውሳብዮስና የኢየሩሳሌሙ

---

13 መስቀሉን ቀብረው ሃያውን ክንድ አፈር ሞልተው ከዚያ በላይ የፈያታዊ ዘየማንን ሃያውን ክንድ አፈር ሞልተው ከዚያ በላይ የጥራጊ መውደቂያ እንዲሆን አወጁ አውጀውም አልቀሩ ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት ዓመት ያህል ታላቅ ተራራ እስኪሆን ድረስ የጥራጊ መውደቂያ ሆኖ ኖረ።

| | |
|---|---|
| ቆጳሳት። | ኤጲስ ቆጶስ መቃርዮስ አብረው ነበሩ። |
| ወሐሠሠት በእንተ መስቀል ክቡር። | ክቡር የሚሆን የጌታ መስቀል የተቀበረበትም የት እንደሆነ ጠየቀች። |
| ወረከበቶ በብዙኅ ፃሕቅ። | ጠይቃም በብዙ ድካም ምርመራ አገኘችው እሱም በተሐድሶ ጸንቶ ኗሪ ነውና ምንም ሳይሆን ተገኝቷል። |
| ወአንበረቶ መካነ ጐልጎታ። | ካገኘችውም በኋላ ልጇ ቈስጠንጢኖስ ባሠራው በጐልጎታ ቤተ ክርስቲያን አኖረችው። |
| ወአሠርገወቶ በወርቅ ወበዕንቍ። | በወርቅ በዕንቁ አስጊጣ አኖረችው። |
| ወእምድኅረዝ በ፮፻ወበ፲ወ፬ ዓመተ ሥጋዌ መጽኡ ነገሥተ ፋርስ ወአመዝበርዋ | ከዚህ በኋላ በስድስት መቶ ዐሥራ አራት ዓመተ ምሕረት የፋርስ ነገሥታት |



| | |
|---|---|
| ለሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌም፡ | መጥተው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን አጠፏት። |
| ወአውዓዩ ኵሎ ቤተ ክርስቲያን ዘእንበለ ቤተልሔም። | የቤተልሔም ቤተ ክርስቲያን ሲቀር የቀሩትን አቢያተ ክርስቲያናት ሁሉ አቃጠሏቸው አጠፏቸው ። |
| ወቀትልዎሙ ለእለ ሀለዉ ውስቴታ። | በውስጧ የሚኖሩትንም ምእመናን ሁሉ በሰይፍ ፈጇቸው ገደሏቸው። |
| ወጼወውዎ ለመስቀል ክቡር ምስለ ካህናት ወዲያቆናት። | ክቡር የሆነ መስቀሉንም ከቤተ መቅደሱ ሀብት ጋር ካህናቱን ጭምር ማርከው ወሰዱ። |
| ወበእንተዝ ሰአልዎ ኵሎሙ ክርስቲያን ለሕርቃል ንጉሠ ሮም ከመ ይሑር ብሔረ ፋርስ። | ምእመናኑን ፈጅተው መስቀሉን ማርከው ስለ ወሰዱባቸው በየቦታው ያሉ ምእመናን ሁሉ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው |

| | |
|---|---|
| | ፋርስ ይዘምትላቸው ዘንድ የሮሙን ንጉሥ ሕርቃልን ለመኑ:: |
| ወከመ ይሚጥ ሎሙ መስቀሎ ለክርስቶስ እምዔዋዌ:: | ዘምቶም መስቀሉን ከምርኮ ይመልስላቸው ዘንድ መላልሰው ለመኑት:: |
| ወሰሚዖ ዘንተ ሕርቃል ንጉሠ ሮም:: | የሮም ንጉሥ ሕርቃልም የመስቀሉን መማረክ ሰምቶ:: |
| ተንሥአ ይሑር ብሔረ ፋርስ ወይፃባዕ ምስሌሆሙ:: | ከፋርስ ነገሥታት ጋር ለመዋጋት ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብሎ ተነሣ:: |
| ወሖረ ብሔረ ፋርስ:: | ተነሥቶም ፋርስ ዘመተ:: |
| ወሞዖሙ ለጸላዕቱ:: | የዘመተባቸውን ጠላቶቹን አሸነፎ:: |



| | |
|---|---|
| ወፆሮ ለዕፀ መስቀል ቅዱስ በልብሰ መንግሥቱ | መስቀሉን በልብሰ መንግሥቱ አጉናጽፎ ተሸክሞ:: |
| ወአብጽሖ ሀገረ ኢየሩሳሌም:: | ኢየሩሳሌም ድረስ አመጣው:: |
| ወአንበሮ መካነ ጐልጎታ:: | አምጥቶም የጐልጎታን ቤተ ክርስቲያን አድሶ ከዚያው አስቀመጠው:: |
| ወበ ፯፻ ፴ወ፰ ዓመተ ሥጋዌ ነሥዕዋ ዓረብ ለሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌም:: | ከዚህ በኋላ በሰባት መቶ ሠላሳ ስምንት ዓመተ ምሕረት ዓረቦች ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ዕጅ አደረጓት:: |
| ዳዕሙ ኢያውዓይዎሙ ለአብያተ ክርስቲያናት | ነገር ግን ግብር ገብሩ ከማለት በስተቀር ቤተ ክርስቲያኖቹን አላቃጠሉም አልዘረፉም:: |
| ወኢቀተሉ ምእመናነ:: | ምእመናንንም አልገደሉም |

| | |
|---|---|
| | አላንገላቷቸውም:: |
| ወ ኢ ሰ ደ ድ ዎ ሙ እመከናቲሆሙ:: | ከበዓታቸው ከቦታቸው አላሳደዷቸውም:: |
| እስመ መኰንን ዓረብ ዑመር ከሊፋ ሳሔር ሠናይ ውእቱ::[14] | የዓረቦች አስተዳዳሪ ሆኖ ያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ተሹሞ የነበረው ዑመር ከሊፋ ለሰው አዛኝና ርኅሩኅ ደግ ሰው ነበርና :: |
| ወለመስቀለ ክርስቶስ አምጽእዎ ሀገረ እስክንድርያ አባ ዮሐንስ ሣልሳይ ሊቀ ጳጳሳት ወኵሎሙ መሃይምናን በ፷፻ወበ፸ወ፰ ዓመተ ሥጋዌ:: | የጌታችንን መስቀል ግን ሥልጣኑ የዓረብ ገዥዎች ስለሆነ ምንም በሃይማኖት ባይተባበሩ፡ ፡ በነገድ አንድ ናቸውና መብታቸው የተጠበቀላቸው በመሆኑ በእስክንድርያ ያሉ ምእመናን ሊቀ ጳጳሱ ሦስተኛ ዮሐንስ በሰባት መቶ ሰባ ስምንት ዓመተ |

14 ከደማኑቱም የተነሣ ከዕለታት በአንድ ቀን ጉልጎታን ለመጎብኘት ሄደ ከዚያ ውስጥ እንዳለ የስግደታቸው ሰዓት ደርሶ ምልክት ሰማ ፈጥኖ ከጉልጎታ ወጥቶ ከቅጽሩ ውጭ ሰገደ ለማሳየት አብሮት የነበረው ከምእመናኑ አንዱ ለምን ወጣህ ይህስ ቅዱስ ቦታ አይደለምን ከዚህ አትሰግድም ነበርን ቢለው ከእኔ ቀጥለው የሚመጡት ባለሥልጣኖች ዑመር ከሊፋ ሰግዶበታል ብለው እኔን ምክንያት አድርገው ቤተ መቅደሳችሁን እንዳይቀሟችሁ ብዬ ነው ብሎ መልሶለታልና እንዲህ አለ።



| | |
|---|---|
| | ምሕረት ከኢየሩሳሌም አምጥተው እስክንድርያ አስቀመጡት:: |
| ወነበረ በእስክንድርያ እስከ መዋዕለ መንግሥተ አቡየ ዳግማዊ ዳዊት:: | አባቴ ዳግማዊ ዳዊት ነግሠው ግብፅ እስከ ዘመቱበት ድረስ በእስክንድርያ ተቀመጠ:: |
| ከለሜዳ[15] | ከለሜዳው |
| ወአክሊለ ሶክ | የሾክ አክሊሉ |
| ወሰፍነግ | ሰፍነጉን |
| ወሐብል | የታሠረበት ገመዱን የተገረፈበት ጅራፉን |
| ኢመጽአ እምቅድመዝ ዘእንበለ ይእዜ በመዋዕልነ | በእኛ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነው እንጅ ከአሁን በፊት አልመጣም |
| ወይእዜኒ ፈነው ለነ | |

15 ይህ ከለሜዳ ግዙፍነት ያለው ዕንደ ማቅ የሚኮሰኰስ እንደ አሸዋት የሚአርግድ ነው ከግርፋቱ ላይ አልብሰው ቢገፉት ሥጋውን ይዞት ተነሥቷል።

| | |
|---|---|
| ውእተ መስቀለ። | አሁንም ይህን መስቀል ሰደዱልን። |
| ወለመስቀለ ክርስቶሰሰ ፈነው ለነ ወዲዮሙ ውስተ ውሣጤ መስቀል ዘወርቅ ዘመንክር ግብረቱ | ጌታችን የተሰቀለበትን መስቀል ግን ክቡር ስለሆነ ብለው አሠራሩ ድንቅ በሚሆን በወርቅ ሣጥን አድርገው ሰደዱልን። |
| ቀፈሎሙ በቀማጥር ዘወርቅ። | በወርቅ መቆለፊያ ቆልፈው። |
| ወሰበ ያቀውምዎ ይቀውም በመከየደ ወርቅ ዘገብሩ ሎቱ ጠቢባነ አፍርንግ። | በሚያቆሙትም ጊዜ ጠቢባን እንደ ሰው እግር አበጅተውለት ነበርና ቀጥ ብሎ ይቆም ነበር። |
| ከለሜዳሂ ወሰፍነገ ፈነው ለነ ወዲዮሙ በአምሳለ ድርሕ ዘወርቅ። | ከለሜዳውንና ስፍነጉን አክሊለ ሦኩን የተገረፈበት ጅራፉን የታሠረበት ገመዱን ወርቁን እንደ ሙዳይ አሠርተው ከዚያ ውስጥ አድርገው |



| | |
|---|---|
| | ሰደዱልን። |
| ወገበዋቲሁ ርቡዕ ወምዕዙን ውእቱ። | የሙዳዩም አሠራር አራት ማዕዘን ነው። |
| ወለመስቀለ ክርስቶስሰ ዘምስለ ሙዳዩ ዘወርቅ ወደይኖ ውስተ ሣፁን ዘዕንቁ ዘክቡር። | መስቀሉን ከተቀበልን በኋላ ከነ ወርቅ ሣጥኑ የዕንቁ ሣጥን መስቀለኛ አድርገን አሠርተን ከዚያ ውስጥ አስቀመጥነው። |
| ለከለሜዳሂ ወለአክሊለ ሦክ ወለሰፍነግ ወለሀብል ዘምስለ ሙዳዮሙ ድርሕ ዘወርቅ ወደይኖሙ ውስተ ሣፁን ዘወርቅ እንተ አግበርና ንሕነ። | ከለሜዳውን አክሊለ ሦኩን ስፍነጉን ጅራፉን ገመዱን ከነሙዳዩ እኛ ባሠራነው በወርቅ ሣጥን ውስጥ አስቀመጥናቸው ። |
| ዘቦ ውስተ ክርሁ መስቀል ዘዕድ ዘወርቅ። | ከዚኸውም ውስጥ እንደ ሥዕለ ስቅለት የተሠራ የዕጅ የወርቅ መስቀል አለበት። |

| | |
|---|---|
| ወሙዳያትሂ ዘወርቅ ብዙኅ ቦቱ። | እንደ ጌጥ አድርገን ያሠራናቸው ብዙ የወርቅ ሙዳዮች አሉበት። |
| ወመክድናሂ ለሣፁን ዘወርቅ ። | ይኸውም የሣጥኑ ግጣም የወርቅ ነው። |
| ወየዓፅውዎ በቅፍሎ ዘወርቅ። | በወርቅ መቆለፊያ ይቆልፉታል። |
| ወለሣፁንሰ ዘወርቅ ዘአግበርናሆ ንሕነ ትልቁ ወርቁ ፴፻ወ፱፻ወ፶ ዲናር። | መስቀሉ የተቀመጠበት እኛ ያሠራነው የወርቅ ሣጥን የተሠራበት የወርቁ ቍጥር ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አምሳ ወቄት ነው። |
| ወለሣፁንሂ ዘዕፅ ዘሥርግው በወርቅ ትልቁ ለሥርጋዌ ዕፅ ፲፻ወ፱፻ ፹ወ፮ ዲናር | በወርቅ የተለበጠው የዕንጨቱ ሣጥን የተለበጠበት የወርቁ ቍጥር አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ስድስት ወቄት ነው። |
| ዘንተ ኵሎ ወሀበነ ለእግዚአብሔር አብ። | ይህን ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ሰጠን። |



| | |
|---|---|
| ወለወልዱ ወለመንፈስ ቅዱስ። | ከባሕርዩ ለተወለደ ለወልድ ለባሕርይ ሕይወቱ ለመንፈስ ቅዱስ ሰጠን በስም በግብር በአካል ሦስት ቢሆኑ በባሕርይ በሕልውና አንድ ናቸውና። |
| አንትሙሂ ኵልክሙ ማኅበረ ጽኤል። | እናተም ሁላችሁ እስራኤል የተባላችሁ ምእመናን ። |
| ወኵልክሙ ካህናት። | እናንተም ከዚህ የተመደባችሁ አገልጋዮች ካህናት። |
| ወኵልክሙ ሕዝበ ክርስቲያን። | እናንተ ምእመናኑም። |
| ዕድ ወአንስት። | ወንዶችም ሴቶችም። |
| ነገሥታት ወመኳንንት። | ነገሥታቱ መኳንንቱም። |
| ግበሩ ተዝካረ መስቀሉ። | የመስቀሉን በዓሉን አክብሩ ዝክሩን ዘክሩ። |

በዘረከብናኖ ወአንበርናኖ አመ ፳ወ፩ ለመስከረም በበዓለ እግዝእትነ ማርያም።

በተቀበልንበትና ከዚህም ቦታ አስገብተን ባስቀመጥንበት መስከረም ሃያ አንድ ቀን የእመቤታችን በዓል በሚከበርበት ቀን በዓሉን አከበሩ።

ወንሕነኒ ንገብር በዓለ መስቀሉ።

እኛም በዚህ ቀን የመስቀሉን በዓል እናከብራለን።

ወዓዲ ግበሩ አመ ፲ ለመጋቢት።

ዳግመኛም በመጋቢት ዐሥር ቀን አክብሩ።

በዘተረከ ቦቱ መስቀል ከመ ቀዳሚ በእደ ዕሌኒ ንግሥት እሙ ለቈስጠንጢኖስ ጻድቅ

መጀመሪያ ንግሥት ዕሌኒ የቈስጠንጢኖስ እናት አስቆፍራ ያስገኘችበት ነውና ።

ወዳግመ በዕደ ሕርቃል ንጉሠ ሮም።

ዳግመኛም የሮም ንጉሥ ሕርቃል ፋርስ ወርዶ ያገኘበት በዚህ ቀን ነውና።

ወዓዲ ግበሩ በዓለ መስቀሉ

ዳግመኛም በነሐሴ ዐሥራ



አመ ፲ወ፬ ለነሐሴ።

አራት ቀን የመስቀሉን በዓል አክብሩ።

መስቀል በዘገብረ ተአምረ በሀገረ እስክንድርያ።

እስክንድርያ በምትባል አገር መስቀል ተአምራት የአደረገበት ቀን ነውና።

ወበእንቲአሁ አምኑ ብዙኃን አይሁድ በዕዴሁ ለቅዱስ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት።

መስቀል ባደረገው ተአምራት ብዙዎች አይሁድ አምነው በቅዱስ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት ዕጅ ተጠምቀዋልና።

በምክንያተ ብእሲ አይሁዳዊ ባዕል ዘስሙ ፊለስኪኖስ እመ ወግአ ክርስቲያናዊ ከሐዲ በይእቲ ዕለት አውሐዘ ደመ ወማየ ድሙረ።

ያ መ ኑ በ ት ም ክ ን ያ ት ም ፊለስኪኖስ የሚባል አይሁዳዊ ክርስቲያናዊው ከዶ ዕንጨት አመሳቅሎ በመስቀል አምሳል ቢሰጠውና በዚህ የተሰቀለውን ክጂዋለሁ ብሎ በጦር ቢወጋው ያ መስቀል ትኩስ ደም ጥሩ ወሀ በአንድ አፍስሷልና።

| | |
|---|---|
| ወነበረ ነዋሃ ሰዓተ እንዘ ይወርድ ዲበ ምድር። | ይኸውም ትኩስ ደም ጥሩ ወሀ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ሳያቋርጥ ሲፈስ ቆይቷል። |
| ወሶበ ቀብዓ ሊቀ አይሁድ እማይ ወደም ዘውሕዘ እመ መስቀል አዕይንቲሃ ለወለቱ ሐይወት ወርእየት ሶቤሃ። | ያም አይሁዳዊ ትኩስ ደም ጽሩ ወሀ ሲፈስ ባየ ጊዜ ከደረቅ ዕንጨት እንዲህ ያለ ተአምራት ይደረጋልን ብሎ ዕውር ልጅ ነበረችውና ከሚፈሰው ከደሙ ከወሀው ዓይኗን ቢቀባው ወዲያው ዓይኗ በራላት ዳነች አየች።[16] |

[16] ታሪክ ይህስ እንደምን ነው በፊለስኪኖስ አጠገብ ሁለት ክርስቲያኖች ነበሩ ዘመኑ ዘመነ ረሀብ ሆነ የሚበሉት የሚለብሱት በማጣታቸው እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ ከዚህ አይሁዳዊ ባለፀጋ ቤት ገብተን ጊዜውን እናሳልፈውም አሉ። ሄደው ፊለስኪኖስን አሽከርና አሳድረን ብለው ጠየቁት እሱም እኔ አይሁዳዊ እናንተ ክርስቲያኖች ናችሁ በእኔ ሃይማኖት ካልገባችሁ አይሆንም አላቸው አንደኛው ሃይማኖቴን ከምክድስ ረሀቡ ይግደለኝ ብሎ ጥሎ ሄደ። አንደኛው ግን እኔ ሃይማኖት ምን ያደርግልኛል ጥርኝ ጥሬ ቁራሽ እንጀራ አይሰጠኝ ከሻለሁ በሃይማኖትህ ገብቻለሁ አለው፡፤ እሱም ከአይሁድ ወገኖቸ ከሚሆኑ ከሲቃውንቱ ፊት ወስዶ ማናቸውንም ዕንጨት አመሳቅሎ እንደ መስቀል አድርጉ በዕለተ ዓርብ በዚህ የተሰቀለውን ክጃዋለሁ ብለህ ምራቅህን ትፋበት በዚህ ጦር ውጋው ብሎ ሰጠው ያም ከሐዲ እንዳለው ምራቁን ተፋበት በጦሩ ወጋው ያን ጊዜ ትኩስ ደም ጥሩ ወሀ አፍስሷል። በዚህ ጊዜ ፊለስኪኖስ እስከ ቤተሰቡ አመነ ተጠመቀ ያ ከሐዲ ግን ወዲያውኑ ድንጋይ ሆኖ መሬት ተከፍታ አስጥማዋለች ሃይማኖቱን የሚክድ ሰው ሁሉ ዕድል ፈንታው ጽዋ ተርታው እንደዚህ ነው ሊቀ ጳጳሱ ቴዎፍሎስም ይህን ተአምራት ባየ ጊዜ ጊዜ ከአይሁድ ወገን ያመኑትን ካጠመቀ በኋላ የፈሰሰውን ደምና ወሀ እንሥቶ ከመስቀሉ ጋር ከቤተ መቅደስ ወስዶ ቀድሶ አቍርቦበታል። በተረፈውም ለምጽ ሲያነጻበት ድውይ ሲፈውስበት ኑሯል።



| | |
|---|---|
| ወአመ ፲ ለመስከረም ግብሩ በዓለ መስቀል። | ዳግመኛም በመስከረም ፲ ቀን የመስቀሉን በዓል አከብሩ። |
| በዘወጽአ መስቀል በመዋዕለ አቡየ ዳዊት በከመ ነገርነ ቀዳሚ። | አስቀድመን እንደ ተናገርነው አባቴ ዓፄ ዳዊት መስቀሉን የተቀበሉበት ቀን ነውና። |
| ወአመ ፲ወ፯ ለመስከረም ግበሩ በዓለ መስቀል | መስከረም ዐሥራ ሰባት ቀን በዓሉን አክብሩ። |
| በከመ ሥሩዕ አምትካት ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑ ለመስቀል። | ንግሥት ዕሌኒ መስቀሉን ያገኘችበት ቤተ ክርስቲያኑን ያሳነጸችበት ሁለተኛም አባ አውደኪስ ይስሐቅ ሣምራዊን በመስቀል ተአምራት ያሳመነበት ነውና። |
| ወይእዜኒ ያጽንዓነ ያጽንዕክሙ እግዚአብሔር በርትዕት ሃይማኖት። | አሁንም እግዚአብሔር በጸናች በቀናች በተዋሕዶ ሃይማኖት ያጽናችሁ |

| | |
|---|---|
| | ያጽናን። |
| በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ። | ሥጋውን ደሙን ስለተቀበላችሁ |
| መጣዌ አሪት ወነቢያት። | ኦሪትን ሠርቶ የሚያስተምሩ ነቢያትን የሰጠ። |
| ወሀቤ ወንጌል ወሐዋርያት። | ወንጌልን ሠርቶ ያኑ የሚያስተምሩ ሐዋርያትን የሰጠ። |
| ለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን። | ለዘለዓለሙ እስከ ትውልድ ድረስ በተዋሕዶ ሃይማኖት ያጽናችሁ አሜን። |
| ለይኩን ለይኩን። | ይሁን ይደረግልን። |
| በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ ለይኩን ለይኩን። | የክርስቶስ አካል ማኅበር ቤተሰብ ስለተባላችሁ ይሁን ይደረግልን። |



| ምዕራፍ ፳ | ምዕራፍ ፳ |
|---|---|
| ወካዕበ አምጻእነ ለክሙ ከመ ትትአምኅዎሙ ወታከብርዎሙ ወትግበሩ ተዝካሮሙ። | ዳግመኛም በዓላቸውን ታከብሩ ዝክራቸውን ትዘክሩ ትማፀኑባቸው ዘንድ። |
| ዘሀለው አዕፅምቲሆሙ በውሣጤሁ ለሣፁን ዘዕፀ ዘሥርግው በወርቅ። | በወርቅ ከተለበጠው ከዕንጨቱ ሣጥን በውስጥ አፅማቸው ያለ። |
| ወውእቱ ይጸውሮሙ ለኵሎሙ። | እሁን የሚቈጥራቸውን ሁሉ የቅዱሳንን ዓፅም ከመስቀሉ ጋር አንድ አድርጎ የሚይዛቸው እሱ ነውና። |
| ሀየ ሀለው ዓፅመ ሐና እመ ማርያም ወላዲተ አምላክ። | ከዚህ ቀጥሎ የመጣውን የቅዱሳንን ዓፅም ተርትሮ ይቈጥሯል ከዚያውም ካለው መጀመሪያ አምላክን የወለደች የእመቤታችን ድንግል ማርያም እናት የሐና ዓፅም። |

| | |
|---|---|
| ወአፅመ በርተሎሜዎስ ሐዋርያ፡፡ | የ ሐ ዋ ር ያ ው የበርተሎሜዎስን ዓፅም፡፡ |
| ወዓፅመ ጊዮርጊስ ዘልዳ፡፡ | የቅዱስ ጊዮርጊስ ዘልዳን ዓፅም፡፡ |
| ወዓፅመ ገላውዴዎስ ሰማዕት ዘአንፆኪያ | የአንፆኪያ ሰማዕት የሆነ የገላውዴዎስን ዓፅም፡፡ |
| ወዓፅመ ሳዊሮስ ወዲዮስቆሮስ ሊቃነ ጳጳሳት፡ | የሊቃነ ጳጳሳቱ የሳዊሮስን የዲዮስቆሮስን ዓፅም፡፡ |
| ወአፅመ ሕፃናት ዘቤተልሔም፡፡ | ሄሮድስ በቤተልሔም ያስፈጃቸው ሕፃናት ዓፅም፡ |
| እሉ ፲፱ ሀለው ውስተ ማፁን ዘዕፀ ዘሥርግው በወርቅ፡፡ | እኒህ የቈጠርናቸው ሰባቱ ሁሉ ካጌጠው በወርቅ ከተለበጠው የእንጨት ማጥን ውስጥ አሉ፡፡ |
| ወታቦተ ማርያም ድንግል በ፪ኤ አምጻእነ ለክሙ፡፡ | ከዚያውም ላይ አምላክን በወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ በጸናች |



| | |
|---|---|
| | እመቤታችን በድንግል ማርያምስም የተቀረጸችውን ታቦት አምጥተንላችኋል፡፡ |
| ከመ ይሠራዕ ወይትቀደስ ባቲ ቍርባን እንቢረክሙ ዲበ ታቦት ወትረ እስከ ለዓለም፡፡ | ሁልጊዜ ሥጋው ደሙ በሚፈተትበት ቦታ ላይ አስቀምጣችሁ ሥጋውን ደሙን ታከብሩባት ትለውጡባት ዘንድ፡፡ |
| ወይእቲ ታቦት ዓባይ ይእቲ ወባቲ ፲ ቃላት | ይህችውም ታቦት ዐሥሩ ቃላት የተጻፉባት ደገኛ ታቦት ናት፡፡ |
| ወኵሉ ታቦት ዘበ ፲ ቃላት ዓቢይ ውእቱ፡፡ | ዐሥሩ ቃላት የተጻፉበት በጻድቃን በሰማዕታት በመላእክት ስም የተቀረጸ ታቦት ሁሉ ደገኛ ነውና፡፡ |
| ወፈድፋደሰ ግበሩ ተዝካራ ለሐና እመ ማርያም፡ | ይልቁንም የእመቤታችን ድንግል ማርያም እናት የሆነች የሐናን በዓሏን አክብሩ ዝክሯን ዘክሩ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ወለኵሎሙ ጻድቃን ወሰማዕት ግበሩ ተዝካሮሙ። | የሁሉንም የጻድቃን የሰማዕታት በዓላቸውን አክብሩ ዝክራቸውንም ዘክሩ። |
| እስመ በሙ ኪዳን እምኀበ አምላክሙ። | ከፈጣሪአቸው ቃል ኪዳን ተቀብለዋልና። |
| ለታቦትሂ ወለሣፁን አምድኅረ አንበርኖሙ በቅድመ እግዚአብሔር አብ ኀበ ይሠራዕ ወትረ። | ታቦቱን እና ሣፁን ሁል ጊዜ ሥጋውና ደሙ ከሚፈተትበት መቅደስ ከእግዚአብሔር አብ አስገብተን ካስቀመጥናቸው በኋላ። |
| ኢያንቀልቅልምሙ ወኢያፍልስምሙ። | ከዚህ እያወጡ ከአንዱ ወደ አንዱ እንወስዳለን ብለው አያናውጿቸው። |
| ከመ ኢይኩን መንሱት ላዕለ ካህናት ወላዕለ ኵሉ ሕዝበ። | በካህናቱም በሕዝቡም የ ጥፋት መቅሠፍት እንዳ ይታዘዝባቸው። |
| ወአልቦ ዘይክል ርእዮቶ ወኢገሢሶቶ ለዝንቱ መስቀል እስከ ጊዜሁ። | ጊዜው እስኪደርስ መስቀሉን ለማውጣት ይቅርና ሊያየው ሊዳስሰው የሚችል የለምና።[17] |
| ወዓዲ አምጻእነ ለክሙ ከመ ትትአምኑምሙ። | ዳግመኛም በዓላቸውን ታከብሩ ዝክራቸውን ትዘክሩ ዘንድ ዓፅመ ቅዱሳንን አምጥተንላችኋል። |
| ዘሀሎ በውሣጤ ማዕዶ ዘብርሃን ኀዋኀው በማዕከለ ህንብርቱ ዓፅመ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ። | ይኸውም የብርሃን ሣንቃ ካለበት ከመካከሉ የጌታችን ወንድም የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የሚሆን የያዕቆብ ዓፅም። |



[17] ይኸውም በዓፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ተደርጓል። ይህስ እንደምነው ቢሉ አቶ ወልደ ተክሌ የሚባሉ ሹም ክቡሩ ዓፄ ምኒሊክ የእግዚአብሔር አብን ቤተ ክርስቲያን አሠራለሁና በታውን አስደልድለህ አጽዳ ብለው አዘዟቸው ይህን ምክንያት አድርገው አርቀው ሲያስቆፍሩ ካህናቱ ሥዕል መስቀል ይዘው አይሆንም አርቀው አያስቆፍሩ ከላይ ይበቃዎታል ብለው ቢለምኗቸው እዚያም ሰው እኔም ሰው አይሆንም ብለው ተጋፍተው ወደታች አምስት ሜትር ያህል አርቀው የታችኛው ቤተ ክርስቲያን ደረጃ እስኪዘልቅ ድረስ አስቆፈሩት ድልድሉ ተተረምሶ ተነፈሰ ያን ጊዜ ሸንበቆ አምጥተው ርሀቀቱን ለመለካት አስገብተው ቢመዙት ጢስ ወጥቶ የሚቆፍሩትን ወዲያው ገደላቸው እሳቸው ግን ሰባት ቀን ታመው በሰባት ቀናቸው ሞተዋልና እንዲህ እንዳይሆን ሲሉ ኢያፍልስምሙ ወኢያንቀልቅልምሙ አሉ።

| | |
|---|---|
| ወዓፅመ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት፡፡ | የሰማዕታት ፊታውራሪአቸው የሚሆን የእስጢፋኖስን ዓፅም፡፡ |
| ወዓፅመ በርናባስ፡፡ | የበርናባስን ዓፅም፡፡ |
| ወርእሰ ዮሐንስ መጥምቅ ፡፡ | መጥመቀ መለኮት የሚሆን የዮሐንስን ራስ፡፡ |
| ወአፅመ አርሴማ ሰማዕት፡፡ | የሰማዕቷ የአርሴማን አፅም፡፡ |
| እሉንተ ፭ተ ዘንተ ኵሎ ወሀብነ ለእግዚአብሔር አብ ፡፡ | እነዚህን አምስቱን ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን አምጥተንም ሰጥተን አስቀመጥን፡፡ |
| ወአንትሙሂ ከመ ትትመሐፀኑ በሙ ወትግበሩ ተዝካሮሙ፡፡ | እናንተም በዓላቸውን ታከብሩ ዝክራቸውን ትዘክሩ ትማፀኑባቸው ዘንድ፡፡ |



| | |
|---|---|
| ይዕቀበነ እግዚአብሔር በጸሎቶሙ ወበኪዳኖሙ ወይዕቀብክሙ፡፡ | እግዚአብሔር በጸሎታቸ ውና በቃል ኪዳናቸው ይጠብቀን ይጠብቃችሁ፡፡ |
| በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን፡፡ | ሥጋውን ደሙን ስለተቀበላችሁ የክርስቶስ አካል ማኅበር ቤተሰብ ስለተባላችሁ ይጠብቃችሁ ይጠብቀን አሜን፡፡ |
| ለይኩን ለይኩን፡፡ | ሕይወተ ልቡና ሀብተ ወልድና ከእግዚአብሔር አብ ከአመቤታችን ከክቡር መስቀሉ ይሁንላችሁ ይሁንልን፡፡ |
| በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ ለይኩን ለይኩን፡፡ | ሥጋው ደሙ ደገኛ ነገር ነውና ይሁንላችሁ ይደረግላችሁ፡፡ |
| ስምዑ ካዕበ ከመ ንንግርክሙ ወከመ ትትቀበልዎ በዓቢይ | አሁንም በፍጹም ደስ እያላችሁ ትቀበሉት ዘንድ ይህን እንነግራችኋለንና |

| | |
|---|---|
| ፍሥሐ። | ስሙ። |
| መቅድመ ካህናት እንዘ ትብሉ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ዘምስለ መሐትው ወማዕጠንት ወመስቀል። | አስቀድማችሁ ካህናቱ መብራት የወርቅ ሻኩራ የወርቅ መስቀል ይዛችሁ በታቦቱ ፊት ሁናችሁ እግዚአብሔር ባወጣለት ስም መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ እያላችሁ፡ |
| ወካዕበ እንዘ ትተልው ኵልክሙ ማኅበራነ ሸኤል ድኅሬሆሙ ለካህናት። | እናንተም ምእመናን ነገሥታቱ መኳንንቱ ከካህናቱ በኋላ ሁናችሁ። |
| እንዘትነጽፉ አልባሲክሙ። | ልብሳችሁን እያነጠፋችሁ |
| ወእንዘ ተሐልዩ በማኅሌት ሐዲስ። | በአዲስ ምሥጋና እያመሰገናችሁ። |
| አብዕዎ ወአንብርዎ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር አብ፡ | ከ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር አ ብ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስገብታችሁ አስቀምጡት፡ |



| | |
|---|---|
| ወዝንቱ ቃለ መልእክት ኢይምሰልክሙ ሐሰተ አላ ነገሩ ርቱዕ ወእሙን ውእቱ። | ይህም መልአክት ሐሰት አይምሰላችሁ የቀና ደስ የሚአሰኝ ዕውነት ነው እንጅ። |
| ወርቱዕ ትትወከፍዎ። | አምናችሁ ልትቀበሉት ይገባል። |
| ያጽንዓነ እግዚአብሔር ወያጽንዕክሙ። | አሁንም በጸናች በቀናች በተዋሕዶ ሃይማኖት ያጽናችሁ ያጽናን። |
| በትምህርተ አሪት ወነቢያት። | አሪት ነቢያት ባስተማሩት ትምህርት። |
| በትምህርተ ወንጌል ወሐዋርያት። | በወንጌል እና ሐዋርያት ባስተማሩት ትምህርት። |
| ለዓለመ ዓለም አሜን። | ለዘለዓለሙ አሜን። |
| ወአሜን። | በዕውነት። |
| ለይኩን ለይኩን። | ይሁንልን ይሁንላችሁ። |

| | |
|---|---|
| በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ ለይኩን ለይኩን፡፡ | ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ስለተቀበላችሁን ይሁን ይደረግላችሁ ክቡር፡፡ |

## ምዕራፍ ፮ | ምዕራፍ ፮

| | |
|---|---|
| ወካዕበ ይቤ ንጉሥነ ዘርዓ ያዕቆብ ርቱዓ ሃይማኖት ዘተሰምየ ቈስጠንጢኖስ፡፡ | ዳግመኛ ሃይማኖታቸው የቀና ቈስጠንጢኖስ የተባሉ ንጉሣችን ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንዲህ አሉ፡፡ |
| ስምዑ ኵልክሙ ማኅበረ ፳ኤል፡፡ | እስራኤል የተባላችሁ ምእመናን ሁሉ፡፡ |
| ወካህናተ ደብተራ ዘመርጡል፡፡ | በዚህ በእግዚአብሔር አብና በእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ተሠርታችሁ የምታገለግሉ ካህናት፡፡ |
| መኳንንት፡፡ | ደጃዝማቹ ቀኛዝማቹ ግራዝማቹ፡፡ |



| | |
|---|---|
| ወአቃምባ፡፡ | የክፍሉ ምስለኔ አበ አስተዳዳሪው፡፡ |
| ዘምስለ ሥዩማን፡፡ | በውስጡ የምትገኙ ሹማምንት፡፡ |
| ዕድ ወአንስት፡፡ | ወንዶችም ሴቶችም ብትሆኑ ስሙ ፡፡ |
| አንሰ ወሀብኩ ለሊቀካህናት ይስሐቅ ዘእግዚአብሔር አብ ኵስኵሰ ዘወርቅ ዘቦ ሥዕል ዘወርቅ፡፡ | ለግሸን አለቃ ሆኖ ቦታውን ይጠብቅ ካህናቱን ያስተዳድር ዘንድ የማዕርግ ስሙን ሊቀካህናት ብየ ለሾምኩት ለሊቀ ካህናት ይስሐቅ የወርቅ ሥዕል ያለበት የአንገት ሀብል፡፡ |
| ወፈቃር ዘወርቅ፡፡ | በወርቅ የተጠለፈ የወርቅ ቀሚስ፡፡ |
| ወክዳነ ዘወርቅ፡፡ | ከወርቅ የተሠራ ካባ፡፡ |
| ወመነሣንስ ዘሐር፡፡ | ከነጭ ሐር የተሠራ ጭራ ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ወድባበ ዘወርቅ። | የወርቅ የየድባብ። |
| ወመስቀለ ዘወርቅ ዘዕድ ዘቦ ሥዕል ላዕሌሁ። | በላዩ ሥዕል የተቀረፀበት የወርቅ የዕጅ መስቀል። |
| ወብርተ ዘወርቅ። | የወርቅ ሰን። |
| ወምስለ ንብቲራ ዘብሩር። | ከብር የተሠራ ብርት ማለት መታጠቢያ ። |
| ዘንተ ኵሎ ወሀብነ ከመ ይኩን ሞገሰ ደብርነ። | ይህን ሁሉ የደብራችን የሹመቱ ማዕርግ መታወቂያ ይሆን ዘንድ ሰጠን። |
| ወሞገሰሙ ለዕብራውያን አበዊነ። | ቀደሞ በዚህ ሥልጣነ ክህነት ለነበሩ አባቶቻችን፡ |
| ወአኃዊነ። | ወደፊትም በዚህ ሥልጣን ለሚተኩ ወንድሞቻችን የሹመታቸው መታወቂያ የሥልጣናቸው መከበሪያ እንዲሆን። |



| | |
|---|---|
| በከመ ነገረ ቀዳሚ ሕግ ዘሌዋውያን። | ቀደም ብሎ የካህናትን ክብር ለማጠየቅ ሲል ካህናቲከ ይለብሱ ጽድቀ ተብሎ እንደ ተናገረ። |
| ዘንተ ሠራዕነ ለትውልደ ትውልድ ዘለዓለም። | ይህን ሥርዓት ለዘለዓለም እስከ ልጅ ልጅ ይተላለፍ ብለን ሠራን። |
| ወካዕበ ወሀብነ ለጃንጠራረ መኰንነ አምባሰል። | የአምባሰል ገዥ አስተዳዳሪ አድርገን ለሾምነው ለጃንጠራሩ። |
| ዳታነ ዘወርቅ። | የእጁ መታጠቢያ የሚሆን የወርቅ ዳታን። |
| ወአራዘ ዘወርቅ። | የወርቅ ቀሚስ። |
| ወከዳነ ዘወርቀ በዓለ አዝራር። | አዝራር ያለው የወርቅ ለምድ። |
| ወፀምረ ለይ ቀይሕ ዘወርቅ ዘይቀንቶ። | የሚታጠቀው የወርቅ ቀይ ግምጃ ሱሪ። |

| | |
|---|---|
| ወቅናተ ዘወርቅ። | የወርቅ ቀሽመሪ (ዝናር) ሰጠን። |
| ወዓዲ ወሀብኖ ሥልጣኖ። | ዳግመኛም። |
| ይስተይ በጽዋዓ ንጉሥ። | በንጉሡ የወርቅ ዋንጫ እንዲጠጣ። |
| ወይጸዓን በቅለ ዘሥርጉት በወርቅ። | በወርቅ መረሻት ባጌጠች በቅሎ እንዲቀመጥ። |
| ወያንፍሕ ቀርኖ እስከ ውሣጤ ጽርሐ ንጉሥ። | ከንጉሡ እልፍኝ ደጃፍ ድረስ ነጋሪቱን እያስመታ እንዲገባ። |
| ወይንበር በፀጋመ ንጉሥ። | ገብቶም በንጉሡ ግራ ተካክሎ እንዲቀመጥ ወይንብር ካህን በየማነ ንጉሥ እንዲል ቀኙ የሊቀ ጳጳሱ መቀመጫ ነውና። |



| | |
|---|---|
| ወይትለዓል ክብሩ እምክብረ መሳፍንት ወመኳንንት። | ክብሩም ከመሳፍንቱ ከመኳንንቱ በላይ እንዲሆን ሥልጣን ሰጠን። |
| እስመ ጃንጥ'ር ብሂል ኃራዩ ወጸዋዒ ወአቅራቢ ንጉሥ እምጅፀወ፺ ውሉደ ነገሥት እለ ይነብሩ ውስተ ዛቲ መካን። | ጃንጠራር ማለት ከዚህች ቦታ ውስጥ ተቀምጠው ከሚማሩት አምስት መቶ ዘጠና የነገሥታት ልጆች ጽኑ ሃይማኖት ሰፊ አእምሮ ያለውን ጠርቶ መርጦ ለንጉሥነት የሚቀርብ ማለት ነው መርጦ አቅራቢው እሱ ነውና። |
| ወለፍትሐ ሊቀ ካህናት ዘደብረ ከርቤ አልቦ ዘይሰምዖ ዘእንበለ ሊቀ ጳጳስ ወንጉሥ። | የግሽን ደብረ ከርቤ አለቃ ሊቀ ካህናቱ የፈረደውን ፍርድ ግን ያለ ሊቀ ጳጳሱና ንጉሡ በቀር የሚሰማ የለም። |

| | |
|---|---|
| ወአብያተ ክርስቲያናት ዘሀገረ አምባሰል ይኀድራ በታሕተ ሊቀ ካህናት ዘደብረ ክርቤ እስከ ለዓለም። | በአምባሰል ያሉ አብያተ ክርስቲያናት እስከ ዘለዓለሙ ድረስ በግሸን ደብረ ክርቤ አለቃ ሥልጣን ውስጥ ይተዳደሩ። |
| እስመ አልቦን ዘእንበሌሁ ዘይቀንዮን ወይሜሕሮን። | ያለእሱ የሚያስተዳድሯቸውና የሚያስተምሯቸው የላቸውምና። |
| ኢይምሰልክሙ ቀሊለ ዝንቱ ደብርነ። | ይህ ደብራችን። (ግሸን ደብረ ክርቤ) |
| ወዝንቱ መቅደስን። | በእግዚአብሔር አብና በእመቤታችን ስም የሠራናቸው መቅደሶቻችን ቀላል አይምሰሏችሁ። |
| ወለዝ ደብር ዘይትማሰሎ ኢረከብነ እምቅድመዝ። ወኢይትረከብ እምድኅረዝ። | ከአሁን በፊት ይህን ደብር የመሰለ በክብር የሚተካከል አላገኘንም። ወደፊትም አይገኝምና። |



| | |
|---|---|
| ወዘንተ ሥርዓተ ዘአጽርዓ። | ይህን ሥርዓት የአፈረሰውን። |
| እመሂ ነገሥት። | ነገሥታቱም ቢሆኑ |
| ወእመሂ ጳጳሳት። | ጳጳሳቱም አስተምረን ይህን አናስፈጽምም ቢሉ፡ |
| አውገዝነ ወአሠርነ በቃልነ ዘኢይትፈታሕ እስከ ለዓለመ ዓለም። | እስከ ዘለዓለሙ ድረስ በማይፈታ ቃላችን አውግዘናቸዋል አሥረናቸዋል አሉ አባ ሚካኤል አባ ገብርኤል ናቸው። |
| አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን። | በውነት ይሁንባቸው ይደረግባቸው። |

## ምዕራፍ ፯

## ምዕራፍ ፯

ዓፀደ እግዚአብሔር አብሂ ወዓፀደ እግዝእትነ ማርያም ይርእዩ ወይሕሥሡ ስለአውራኅ አዘዝነ መኳንንተ ዘተሠይሙ ለሀገረ አምባሰል።

የእግዚአብሔር አብንና የእመቤታችንን ድንግል ማርያምን ክበብ የአምባሰል ጃንጠራሮች በውስጣቸው የተሾሙት ባላምባራሉን ቀኝ አዝማቹን አዘው በየወሩ መጥተው ያጸዱ ያስጠርጉ ዘንድ አዘናቸዋል።

ወእከ ዘንተ ባሕቲቶ አላ ዓውደ መርህባ ሉዓላዊ።

ይህም ብቻ አይደለም ላይኛውን ሜዳውን ጭምር ነው እንጂ።

እስመ ቀጸርነ ሎቱ ቅጽረ ወአውጻእነ ፬ተ አንቀጸ ከመ ይኩን ቅዱስ።

ቦታው የተለየ ይሆን ዘንድ ዙሪያውን አስቀጽረን በአራቱ ማዕዘን በር አውጥተን አክብረነዋልና።

ወባሕረ ዮርዳኖስ ዘአምጻእነ እምፈለገ ዮርዳኖስ በ፬ቱ አግማል ወወደይነ ውስቲቱ በከመ አሰፈወነ እግዚእነ።

ጌታችን በሰጠን ቃል ኪዳን መሠረት ከዮርዳኖስ ውሀ በአራት ግመሎች አስጭነን አምጥተን የቀላቀልንበትን ዮርዳኖስ ብለን የሰየምነውን የጠበሉን ዙሪያ ጭምር እንዲያጸዱ አዘናቸዋል።

ወሠራዕነ ለአሠነዮ ቅጽር።

የፈረሰውን ቅጽር ለማሠራት።

ወጀጉል።

የዙሪያውን የአጥር ዕንጨት እንዲያሳድሱ።

ወለኵስትሮ ነኪረ ኵሉ ኵስሐ አራዊት ወአዕዋፍ።

ከዚህ ጋር አራዊቱ አዕዋፉ የኰሱበትን አዘው ያስጠርጉ ያጸዱ ዘንድ አዘናቸዋል።

ወብዙኅ ዕሤቶሙ በከመ አሰፈወነ እግዚእነ።

ጌታ በሰጠን ቃል ኪዳን መሠረት ይህን ስለ ሠሩ ዋጋቸው ብዙ ነውና።

ወለእመሰ ተሐከዩ ወኢገብሩ ዘአዘዝናሙ።

ነገር ግን ባለሥልጣኖቹ ጃንጠራሮቹ አናዝም

ባላምባራሱ ቀኝ አዝማቹም አንታዘዝም ከፍ ያለ ሥልጣን ይዘን ዕንጨት ድንጋይ ጭቃ ልናሽከም ነው ኩስሐ አራዊት ልናስጠርግ ነው ብለው ትእዛዛችንን ንቀው ግዝቱን አፍርሰው አናሠራም የሚሉ ቢሆን ።

| | |
|---|---|
| እግዚአብሔር ያውርድ ላዕሌሆሙ መቅሠፍተ እሳተ መዓቱ እንበለ ስሣሌ። | እግዚአብሔር ያለማቋረጥ በላያቸው እሳተ መዓቱን ያዝንምባቸው። |
| ወያማስን ነፍሶሙ ወሥጋሆሙ ለዓለም ዓለም። | በዚህ ዓለም በሥጋቸው በወዲያኛው ዓለም በነፍሳቸው መከራ ይታዘዝባቸው። |
| አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን። | ይሁን ይደረግ። |




| | |
|---|---|
| ወካዕበ አውገዙ አባ ሚካኤል ወአባ ገብርኤል ወአነሂ ምስሌሆሙ ከመ ኢይባኣ አንስት ውስተ ቤተ እግዚአብሔር አብ። | ዳግመኛም አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ሴቶች ከእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን አይግቡ አሉ እኔም እንደእነሱ ከለከልኩ። |
| በእንተ ዘኢኮና አንስት ድልዋተ ለፀዊረ ታቦት ወገሚሶቱ። | ሴቶች ታቦት ሊዳስሱ ሊይዙ አግባብ አይደለምና። |
| ታቦትሂ ዘንቤ ዘሀለው ውስቴቱ መስቀል ወከለሜዳ ወአዕፅምቲሆሙ ለቅዱሳን። | ታቦትም ያልናቸው በእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት መስቀሉ ከለሜዳው እና የቅዱሳን አፅም ናቸው። |
| እስመ ሐነጽነ ሎን በስመ እግዝእትነ ማርያም ከመ ይጸልያ ወይትመሐፀና ባቲ በከመ ትቤ አሪት ምቅዋሞን ለአንስት ወምጽላዮን ለባሕቲቶን። | ኦሪት ለሴቶች እንደሚገባ ባዘዘችው መሠረት ይጸልዩባት ይማጸኑባት ዘንድ በእመቤታችን ድንግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን ሠርተንላቸዋልና። |

| | |
|---|---|
| ወኢይሂዳ ዘንተ ትእዛዘ ከመ ኢይረድ መቅሠፍተ እግዚአብሔር ላዕሆን። | ያለ ጊዜአቸው እንዳ ይቀሠፉ ይህን ትእዛ ዝ አይጋፉ አይዳፈሩ። |
| በከመ ወረደ በመዋዕሊነ ላዕለ አሐቲ ብእሲት ምስለ ፪ቲ አዕማቲሃ። | እንዲት ሴት ከሁለት አገልጋዮቿ ጋር በዘመናችን ትእዛዛቱን አፍርሳ በመግባቷ ያለጊዜዋ እንደተቀሠፈች እንዳይቀሠፉ አይደፋፈሩ። |
| ወይእቲኒ ለብስት ልብሰ ዕደው ምስለ አዕማቲሃ ወቦአት በድፍረት ውስተ ቤተ እግዚአብሔር አብ። | ይህች ከሴት አገልጋዮቿ ጋር የወንድ ልብስ ለብሳ ከእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን በድፍረት ገባች። |
| ወወጽአት እምዐፀድ። | ገብታም ውስጡን አይታ ወጥታ ከቅጽሩ ውጭ ስትደርስ። |
| ወትቤ። | እንዲህ አለች። |



| | |
|---|---|
| ናሁ ቦእኩ ወወጻእኩ። | እነሆ አይገባም ሲሉ ገብቼ ወጣሁ። |
| ወምንተ ረሰየኒ። | ምንስ ሆንኩ አለች። |
| ወበጊዜሐ አብቀወት ምድር ወጡህጠታ ምስለ አዕማቲሃ | ያንጊዜ ፍርሐተ በራቀው ድፍረት በተሞላ ልቦናዋ በትእቢት በመናገሯ መሬት ተከፍታ እስከ አገልጋዮቿ አሰጠመቻት። |
| ወኮነ ዓቢይ ፍርሐት ወረአድ | ይህ በመገለፁ በተመልካቹ ዓይን ዘንድ ፍፁም ፍርሐትና ድንጋጤ ሆነ |
| ወአቀምነ ሠለስተ አዕባነ መጠነ ቆመ ብዕሲ ላዕለ ውእቱ መካን ከመ ይኩና ትእምርተ ለዘይመጽ ትውልድ | ይህ በመገለፁ በሌሎች እህቶች ላይ ዳግም እንዳይገለጽ በማሰብ ሦስቱም በሰጠሙበት ቦታ ላይ ምልክት ይሆኑ ዘንድ ሦስት ድንጋዮች በሰው ቁመት ልክ የሚሆኑ አቆምን። |

# ብፁዕ አቡነ ሚካኤል



(ብፁዕ አቡነ ሚካኤል 1878-1952 ዓ.ም)

መምህር ገሪማ ወልደ ኪዳን ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከአባታቸው ከመሪጌታ ወልደ ኪዳንና ከእናታቸው ወ/ሮ /በኋላ እማሆይ/ ደስታ ወልደ ገብርኤል ግንቦት 7 ቀን 1878 ዓ.ም. በደቡብ ወሎ ዞን

በአምባሰል ወረዳ በግሽን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ደብር ተወለዱ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ክርስትና በተነሡባት ግሽን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ማለትም ንባብና የቃል ትምህርት በትጋት አጠናቀቁ። ትምህርታቸውን በመቀጠልም ከአባታቸው ከመርጌታ ወልደ ኪዳን ሥር ሆነው ጸዋትወ ዜማን ተከታተሉ። የእርሳቸው ቀለም የመያዝ ብቃት ከአባታቸው የቅርብ ክትትል ጋር ተዳምሮ መምህር ገሪማ ሁለቱንም የትምህርት ደረጃ በፍጥነት አጠናቀቁ።

ብፁዕነታቸው ከዚህ በኋላ ቅኔ ለመማር ያደጉባትን ደብር ትተው ወደ ቦሩ ሄዱ። በዚያም የቅኔ ትምህርታቸውን አቀላጥፈው ተማሩ። በመምህር ገሪማ የረቀቀውን የማመስጠር፣ የተሰወረውን መርምሮ የማግኘት ብቃት መምህራቸው ይደነቁ ነበር። በሚያስደንቅ ፍጥነት ቅኔን ከነአገባቡና ሞያው የተማሩት መምህር ገሪማ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ለመመርመር በ1898 ዓ.ም. መርጦ ከተባለው ቦታ ሰፊ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ወደ ነበሩት መምህር ደስታ /በኋላ አቡነ አብርሃም/ ሄዱ።



በዚያም መጻሕፍተ ሐዲሳትን ለሦስት ዓመታት አጠኑ። ከመምህር ደስታ የጀመሩትን ትምህርት ሳይጨርሱ ወደ ጎንደር በመሻገር ከአለቃ ዮሐንስ ዘንድ ፍትሐ ነገሥትን አጠኑ። ከዚያም የዐሥራ አራቱን መጻሕፍተ ቅዳሴ ትርጓሜ መካነ ኢየሱስ ላይ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት አለቃ ወልደ ሚካኤልና ከደረስጌው ከአለቃ ብሩ ጠንቅቀው ተማሩ።

ከዚህ በኋላ በ1910 ዓ.ም. ባገኙት የዜማ መምህርነት ማረጋገጫ ጉባኤ ዘርግተው ቅዳሴ ያስተምሩ ጀመር። የመምህር ገሪማን የማስተማር ብቃትና የጉባኤያቸውን መስፋት የሰማው ተማሪ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል እየመጣ ጉባኤያቸው እያደር እየሰፋ ታወቂነታቸውም እየጨመረ ሄደ። በንጽሕናና በድንግልና ተወስነው የማስተማር ተግባራቸውን ለማጠናከር ጉባኤያቸውን ለሌላ መምህር አስረክበው ወደ ደብረ ሊባኖስ በመሄድ ሥርዓተ ገዳምን የበለጠ ካጠኑ በኋላ ጥር 7 ቀን 1916 ዓ.ም. ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ። ብዙም ሳይቆዩ የካቲት 12 ቀን በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ ቅስና ተቀበሉ።

ከዚህም በኋላ መምህር ገሪማ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም በመጋቢት ወር ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሄዱ። እንዳሰቡት በቅድስት ሀገር ለስድስት ወራት ያህል ተዘዋውረው ቅዱሳት መካናቱን ከተሳለሙ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰው በያኔው ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ አዲስ ተተክሎ በነበረው መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍተ ሐዲሳትና መጻሕፍተ ቅዳሴ መምህር ሆኑ።

መምህር ገሪማ በተመደቡበት የመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በትጋት ማስተማር ጀመሩ። ቀድሞ ሥርዓተ ምንኩስና ለመፈጸም ወደ ደብረ ሊባኖስ በሄዱ ጊዜ የተለዩአቸው ተማሪዎቻቸው ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሱ ሲሰሙ ከየነበሩበት መሰባሰብ ጀመሩ። ይህን የመምህሩን የማስተማር ብቃትና ዕውቀት በቅርበት ሆነው ያዩት ግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ዓፄ ኃይለ ሥላሴ መምህር ገሪማን ከማስተማር ጋር ከጉባኤያቸው አልፎ ለሌሎች ጉባኤያትና ትውልድ የሚጠቅም ሥራን እንዲሠሩ አዘዟቸው። ይኸውም ለረጅም ዘመናት በቃል ሲተላለፍ የቆየውን መጽሐፈ ቅዳሴ ነጠላ ንባቡን ከነትርጓሜው እንዲያዘጋጁ ነበር።



የንጉሡን ትእዛዝ የተቀበሉት መምህር ገሪማም በታዘዙት መሠረት የመጽሐፈ ቅዳሴን ነጠላ ንባብ ከነትርጓሜው አዘጋጁ። በሊቁ የተደሰቱት ዓፄ ኃይለ ሥላሴም የመጽሐፉን ኅትመት ወጭ በመሸፈን በ1918 ዓ.ም. እንዲታተም አደረጉ። ይህ መጽሐፍ እስከ ዛሬ ድረስ በተደጋጋሚ እየታተመ በማገልገል ላይ ይገኛል።

ከንጉሡ የተሰጣቸውን ሥራ ከመሥራት ጋር ወደ ጉባኤያቸው የመጡ በርካታ ተማሪዎችን በማስተማር ለአራት ዓመታት የቆዩት መምህር ገሪማ በ1921 ዓ.ም. ተወልደው ባደጉባትና በተማሩባት ግሸን ማርያም ደብር መምህር ሆነው ተላኩ።

በዚያም ለስምንት ዓመታት ያህል በትጋት ሲያገለግሉ፣ በደብሩ የሚገኙ ቅርሶች በአግባቡ እንዲቀመጡና እንዲጠበቁ ፣ የቦታው ታሪክ ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፣ በርካታ ሊቃውንትን አፍርተዋል፣ እንደዚሁም በቦታው ሲቆዩ ለመጀመሪያ ጊዜ የደብሩ አገልጋዮች ወደ ታላቅ ጉባኤ ሄደው እንዲማሩ አድርገዋል፣ በመቀጠልም አንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያንን ባዩት ራዕያዊ ተልዕኮ በገንዘባቸው አሰርተዋል።

እንዲሁም ለቤተክርስቲያኑ አገልጋዮች ከመንግስት በማስፈቀድ ርስት አውጥተዋል። በቀድሞ የዣንጥራር ቦታ ሁዳዱ እየተባለ የሚጠራውን ቦታ ለደብሩ አገልጋይ ካህናቶችና ለልዩ ልዩ ሰራተኞች በላይኛው ቦታ እየኖሩ በታችኛው አትክልት ተክለው እንዲጠቀሙ ከመንግስት በማስፈቀድ አከፋፍለዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት የመሾም ነጻነት ተቀዳጅታ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ ከመሆናቸው በፊት ቤተ ክርስቲያኗም ሆነች የሀገሪቱ መንግሥት በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ያሏትን ገዳማት የሚያስተዳድር አንድ አባት ወደዚያው ሲላክ የሚሰጠው የሹመት ስም "ራእስ /ረኢስ/" የሚባል ነበር።

ምንም እንኳን ቀደም ሲል በራእስነት ወደ ኢየሩሳሌም የተላኩትን ኢትዮጵያዊያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም ዝርዝር ለማግኘት ባየቻልም ከዓፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ወዲህ እስከ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጵጵስና መሾም ድረስ በራእስነት ያገለገሉ አባቶች ስም ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው።



1. መ/ር ወልደ ሰማዕት
2. መ/ር ገብረ ኢየሱስ
3. መ/ር ፈቀደ
4. መ/ር ማኅፀንቱ
5. መ/ር ይርዳው
6. መ/ር ወልደ ሚካኤል /አቡነ ሚካኤል/
7. መ/ር ገብረ ኢየሱስ

በ1928 ዓ.ም. በተደረገው የራእሶች ምርጫ መምህር ገሪማ ተመርጠው በዚያው ዓመት መስከረም 24 ቀን "መ/ር ገሪማ፤ በኢየሩሳሌም ላሉት ለአራቱ የኢትዮጵያ ገዳማት ራእስ" ተብለው ተሹመው ተልከዋል።

መምህር ገሪማ የተሰጣቸውን ሓላፊነት ይዘው ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሄደው ብዙም ሳይቆዩ ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወረረ። ይህን የግፍ ዜና ኢየሩሳሌም ሆነው የሰሙት መምህር ገሪማ ወደ ሀገራቸው መመለስ ባይችሉም ከሌሎች በዚያ ከሚኖሩ ማኅበረ መነኮሳት ጋር በመተባበር የርቀት ትግላቸውን ቀጠሉ።

ከጦርነቱ ሸሽተው ወደ ኢየሩሳሌም የተሰደዱትን ኢትዮጵያውያንን በመቀበልና በማስተናገድ፤ የኢትዮጵያን በግፍ መወረር ለአካባቢው መንግሥታት በማሰማትና በሌሎች መንገዶች ሁሉ ትግላቸውን ያፋፍሙ ጀመር።

ፋሺስት በወረራው ዘመን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ይውለበለቡ የነበሩት የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ወርደው በኢጣሊያ ባንዲራዎች እንዲተኩ እንዳደረገ ሁሉ፤ ይህ ተግባሩ ዓለም ዐቀፋዊ መልክ ይዞ በኢየሩሳሌም ገዳማት ይውለበለቡ የነበሩት የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ወርደው በኢጣሊያ ባንዲራዎች እንዲተኩ አድርጎ ነበር። ይህንን ከልክ ያለፈ የግፍ ተግባር በዓይናቸው ያዩት መምህር ገሪማ በቆራጥነት የኢጣልያን ባንዲራ አውርደው በማቃጠል በቦታው የሀገራቸውን ባንዲራ ሰቅለዋል።

ከመራራ የአምስት ዓመት ትግል በኋላም የኢትዮጵያ ነጻነት በ1933 ዓ.ም.ሲመለስ በመስከረም ወር 1937 ዓ.ም. መምህር ገሪማም ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው መጡ። በመጡ በዓመታቸውም ታኅሣሥ 16 ቀን 1937 ዓ.ም.እንደ ገና በትውልድ ቦታቸው ግሸን ማርያም ተሹመው ወደዚያው ሄዱ። በዚያም ሆነው



ደብራቸውን በመልካም አባትነት እያስተዳደሩ ሳለ ሚያዝያ 19 ቀን 1938 ዓ.ም.አዲስ አበባ በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ ለጵጵስና ተመረጡ።

ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም. ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ ግብፅ ካይሮ ሄደው በወቅቱ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ 2ኛ አንብሮተ እድ መዓርገ ጵጵስናን ተቀብለው "አባ ሚካኤል ጳጳስ ዘጎንደር" ተብለው በቤጌምድርና ስሜን ሀገረ ስብከት ተሾሙ።

ብፁዕነታቸው ሹመቱን በአኰቴት ተቀብለው ወደ ሀገረ ስብከታቸው በመሄድ የተቀበሉትን ታላቅ ሓላፊነት ሲወጡ ቆዩ። ቃለ እግዚአብሔር ለተራበው ምግበ ነፍሱን ፣ ምግበ ሥጋ ለሚሻው ደግሞ ከምግበ ነፍሱ ጋር ምግበ ሥጋውን ከግል ኪሳቸው እያወጡ ሲመግቡ ቆይተዋል።

የሀገረስብከታቸውን ሕዝብ ቀድሞ በተማሪነታቸው ጊዜ ጀምሮ የሚያውቁት በመሆኑ እንግዳ ሳይሆኑ ጋራና ወንዙን በማቋረጥ ሕዝቡን አስተምረዋል፤ ገዳማትን፣ አድባራትንና አብነት ት/ቤቶችን አጠናክረዋል።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ምንም እንኳን ሀገረ ስብከታቸው በጌምድር ቢሆንም በየዓመቱ መስከረም 21 ቀን ተወልደው ባደጉባት ግሼን ደብረ ከርቤ እየተገኙ በዓለ መስቀሉንና በዓለ እግዝእትነ ማርያምን ማክበር ልማዳቸው ነበር። በዚህም መሠረት በ1952 ዓ.ም.መስከረም ወር እንደተለመደው የእመቤታችንን በዓል ለማክበር ወደ ግሸን ሄዱ።

በዓሉንም በሰላም አከበሩ። ነገር ግን የእሳቸው ሐሳብ ወደ ሀገረ ስብከታቸው መመለስ ቢሆንም ሳያስቡት ባደረባቸው ሕመም ለጥቂት ቀናት ከሰነበቱ በኋላ በተወለዱ በ74 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ዜና ዕረፍታቸው እንደ ተሰማም ብፁዕ አቡነ ገብርኤል በወቅቱ የወሎ ሊቀ ጳጳስ ከደሴ፣ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ፣ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብና ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በተገኙበት ስርዓተ ቀብራቸው ጥቅምት 5 ቀን 1952 ዓ.ም. ተወለወደው ባደጉበትና ባስተማሩበት በግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ደብር ተፈጽሟል።

ዕረፍታቸውን በማስመልከትም ጥቅምት 7 ቀን 1952 ዓ.ም. ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ግርማዊት እቴጌ መነን እንዲሁም ንጉሣውያን ቤተሰቦች በተገኙበት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ



ክርስቲያን በመገኘት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከተ ካህናትና የደብር አስተዳዳሪዎች ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎላቸዋል።

ከሥርዓተ ፍትሐቱና ቅዳሴው በኋላም ብፁዕ ወቅዱስ አቡ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ስለ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ማንነት ሰፋ ያለ ንግግርና የኃዘን መግለጫ አሰምተው የጸሎተ ፍትሐቱ ፍጻሜ ሆኗል።

የብፁዕነታቸውን አገልግሎት በተለይ ጣሊያን ሀገራችንን በግፍ በወረረ ጊዜ ያደረጉትን የአርበኝነት ሥራ ትውልድ ሲያዘክረው ይኖር ዘንድም በንጉሠ ነገሥቱ፣ ግርማዊት እቴጌ መነን፣ የንጉሣውያን ቤተሰብና በአምስቱ የመከራ ዘመናት የስደት ተካፋዮቻቸው በነበሩት ኢትዮጵያውያን የገንዘብ ርዳታ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅጽር ግቢ የመታሰቢያ ሐውልት ቆሞላቸዋል። ይኸው ሐውልት ዛሬም በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ ቆሞ ይገኛል።

የግሽን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ሰበካ ጉባኤም ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቅድስት ቤተክርስቲያናቸውን በትጋት ሲያገለግሉ በመኖራቸው፣ ለግሽን ደብረ ከርቤ ቤተክርስቲያንና ሊቃውንት በተለይም መጽሐፈ ጤፉት በክብር ተጠብቃ ለዚህ ጊዜ እንድትደርስ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ የብፁዕነታቸውን ውለታ ለማስታወስ በዚህ በመጽሐፈ ጤፉት ውስጥ የሕይወት ታሪካቸው ተካቶ ምዕመናን ያገኙት ዘንድና የብፁዕነታቸውን በረከት ያገኙ ዘንድ ወደድን። የብፁዕነታቸው ረድኤት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።